

‹‹አገርን የሚያሳድገው የመንግስታት መለዋወጥ ሳይሆን የሕዝብ አዕምሮ መለወጥ ነው››

- አርቲስት ተስፋዬ ሲማ

ገጽ 6

የመድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አምራቾችን ማነቆ ለመፍታት

ገጽ 8


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 253 ግንቦት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


## ‹‹ዳያስፖራው በአሜሪካ ምርጫ ድምፁን ተጠቅሞ ኢትዮጵያ ላይ የሚደረገውን ጫና ለማስቆም እየሰራ ነው››

- አርቲስት ተስፋዬ ሲማ

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ፡- በቅርቡ በሚካሄደው የአሜሪካ የሴናተሮች ምርጫ ዳያስፖራው ድምፁን በመጠቀም ኢትዮጵያ ላይ የሚደረገውን ጫና ለማስቆም አፅንኦት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን አርቲስት ተስፋዬ ሲማ አስታወቀ።

ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ ኑሮውን በአሜሪካ ያደረገው አርቲስት ተስፋዬ ሲማ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቀው፤ በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በቅርቡ በሚካሄደው የአሜሪካ ሴናተሮች ምርጫ የአሜሪካን መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ያለውን አመለካከት ለመቀየርና ፖለቲከኞችን አቋም ለማለዘብ የሚያስችሉ የቅስቀሳ ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ።

በአሜሪካ ፅንፈኛ ፖለቲከኞችና የሕወሓት ተላላኪ በሆኑ ግለሰቦች ግፊት ኢትዮጵያ ላይ ለመጣል የታቀደው ኤች.አር 6600 የተሰኘውን አደገኛ ሰነድ ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካ ጫናዎችን

‹‹ዳያስፖራው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ


ጐመጁ ኦይል ኢትዮጵያ

gomeju OIL ETHIOPIA

the prime powerhouse

+251-1 1 6501010

+251-1 1 6501717

www.gomejuoil.com

EFDA

ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY


## አሸባሪው ህወሓት በወረራ በያዘው አበርገሌ ወረዳ በተቀሰቀሰ ወረርሽኝ ህፃናት ለሞት እየተዳረጉ መሆኑ ተነገረ

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ህወሓት በወረራ በያዘው የዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን አበርገሌ ወረዳ ከግንቦት 7/ 2014 ዓ.ም ጀምሮ በተቀሰቀሰ ወረርሽኝ ህፃናት ለሞት እየተዳረጉ መሆኑን የብሔረሰብ አስተዳደሩ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አስታወቀ፡፡

የብሔረሰብ አስተዳደሩ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ከፍያለው ደባሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት አሸባሪ ቡድኑ ዞኑን በወረራ ከተቆጣጠራቸው አካባቢዎች አንዱ በሆነው አበርገሌ ወረዳ ለጊዜው ምንነቱ ያልታወቀ ወረርሽ በመቀስቀሱ ዘጠኝ የሚደርሱ ህጻናት ህይወት አልፏል፡፡

ከአካባቢው ተፈናቅለው ወደ ብሔረሰብ አስተዳደሩ ከሚፈልሱ ሰዎች እንዲሁም በአንድ አንድ አካባቢዎች በስልክ በሚደርሱ መረጃዎች ችግሩ መከሰቱን ያረጋገጠው የብሔረሰብ አስተዳደሩ፣ ችግሩ በአፋጣኝ ካልተቀረፈ በሰዎችና በእንስሳት ላይ የሚደርሰው ጉዳት አስከፊ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

አካባቢው እስከ አሁን ድረስ በአሸባሪው ህወሓት ቡድን እጅ ከመገኘቱ ጋር ተያይዞ ለተጎጂዎች አስፈላጊውን የጤና ባለሙያ እገዛ መስጠት አለመቻሉን ኃላፊው ገልፀው፣ መንግሥት ከዓለም አቀፍ ድንበር የለሽ የህክምና ተቋማት ወይም ገለልተኛ ከሆነ ተቋም ጋር በመሆን ለዜጎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ሕይወታቸውን ሊታደግ እንደሚገባ ጠይቀዋል፡፡

በተያያዘ በአሸባሪው ቡድኑ ወረራ ምክንያት የብሔረሰብ አስተዳደሩ ዜጎች ለረሃብ፣ እርዛት እንዲሁም ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እየተዳረጉ ይገኛሉ፡፡ ከአበርገሌ፣ ጻግብጂ፣ ዛታ እንዲሁም ዝቋላና ከሌሎች በርካታ ወረዳዎች የተፈናቀሉ ዜጎች ቁጥር 88ሺህ

አሸባሪው ህወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ከፍያለው ደባሽ

## ኮቪድ 19 የመቀነስ አዝማሚያ ቢያሳይም አሁንም ስርጭቱ ስላልቆመ መጠንቀቅ እንደሚገባ ተጠቆመ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ኮቪድ 19 በአገር አቀፍ ደረጃ የመቀነስ ሁኔታ ቢያሳይም አሁንም ስርጭቱ በህብረተሰብ ደረጃ በሁሉም ክልሎች ስለሚገኝ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ በጤና ሚኒስቴር የኮቪድ 19 መከላከል ግብረ ኃይል አሳሰበ፡፡ እስካሁን ድረስ ከ25 ሚሊዮን በላይ ዜጎች መከተባቸውንና እስከዓመቱ መጨረሻ ክትባቱን የወሰዱ ዜጎችን ቁጥር 45 ሚሊዮን ለማድረስ እየተሠራ መሆኑም ተገልጿል፡፡

የግብረ ኃይሉ ሰብሳቢ ዶክተር መብራቱ ማሴቦ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮቪድ 19 በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ እንደ አገርም የመቀነስ ሁኔታ በማሳየቱ ከሁለት ወራት በላይ ለሚሆን ጊዜ በቀን ከሚመረመሩ ሰዎች ውስጥ በሽታው የሚገኝባቸው ሰዎች

ኮቪድ 19 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ

ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር

የበረንዳ ታይልስ ኤ ... መደበኛ ክላም

0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


ገጽ 13

ከማህበረሰቡ ወጥቶ ማህበረሰብን ማገልገል ያስገኘው እርካታ



ዜና

# የመጪውን ክረምት የጎርፍ አደጋ ስጋት ለመቋቋም ዝግጅት እንደሚያስፈልግ ተጠቆመ



ዶክተር አሳምነው ተሾመ

አዲስ አበባ:- የመጪውን ክረምት የጎርፍ አደጋ ስጋት ለመቋቋም ዝግጅት እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አሳሰበ።

ኢንስቲትዩቱ ከሁሉም ክልሎች ከተውጣጡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሴክተር አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር መወሰድ ባለባቸው እርምጃዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በአዳማ ከተማ እየመከረ ነው።

የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የአየር ጠባይ አገልግሎት ተመራማሪ ዶክተር አሳምነው ተሾመ ፣ የመጪው ክረምት የአየር ሁኔታ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች እንዳይፈትን ተገቢውን የቅድመ ጥንቃቄ ሥራ መስራት ይገባል ብለዋል።

በመጪው ክረምት ሊኖር የሚችለውን የጎርፍ አደጋ ስጋት ለመከላከልና ተፅዕኖውን ለመቋቋም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄና የቅድመ ዝግጅት ሥራ ላይ ለመምከር የተዘጋጀ መድረክ መሆኑ ተገልጿል።

በመጪው ክረምት ወቅት የአየር ሁኔታ መረጃን በትክክል እንዲረዱ ከማድረግ ባለፈ ተጋላጭ የሆኑ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሴክተሮች የጋራ አቅጣጫ በማስቀመጥ ርብርብ ለማድረግ ነውም ተብሏል፡፡

በተለይ ግብርና፣ ጤና፣ ውሃ፣ አደጋ መከላከል እና ስራ አመራር ተቋማትን ጨምሮ ሌሎች ሴክተሮች በቅንጅትና በትብብር በጉዳዩ ላይ ትኩረት ያስፈልጋል ነው የተባለው።

የፓስፊክ ውቅያኖስ ከመጠን በላይ እየቀዘቀዘ በመምጣቱ የመጪው ክረምት ዝናብ ሁኔታ ከፍተኛ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ 85 በመቶ የሀገሪቷ አካባቢ የሚሸፍን ስርጭት እንደሚኖርም መጠቀሱን ኢዜአ ዘግቧል።

የክረምት ወቅትን ተከትሎ ከጤና ስጋት ጋር በተያያዘ ተገቢው ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ጥሪ ቀርቧል።







# በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ

## በ10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ የተገነቡ 2 ሺህ 700 ቤቶች ተመረቁ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ በ10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ የተገነቡና 2 ሺህ 700 ሰራተኞችን የሚያስተናግዱ የመኖሪያ ሕንፃዎች ተመረቁ፡፡

በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከሚገኙ አምራች ኩባንያዎች መካከል ሺንትስ የተሰኘው የደቡብ ኮሪያ ኩባንያ በ10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ የገነባቸውና 2 ሺህ 700 ሰራተኞችን የሚያስተናግዱት የመኖሪያ ህንፃዎች በዛሬው ዕለት ተመርቀዋል።

በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሳንዶካን ደበበ፣ መንግሥት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው አምስት ዋና ዋና ሴክተሮች አንዱ አምራች ኢንዱስትሪው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በ2030 በአምራች ኢንዱስትሪው ሴክተር ላይ የ20 ነጥብ 6 በመቶ እድገት እንዲመዘገብ እንደሚጠበቅ ያስታወሱት ዋና ሥራ አስፈፃሚው በዚህም አማካኝነት ከ1ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ የሥራ እድል በየዓመቱ ለመፍጠርም እየተሰራ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ኩባንያው ያከናወነው ስራ ለሌሎች መሰል ኩባንያዎች ምሳሌ እና አርዓያ ሆኖ መጠቀስ የሚችል ነው ያሉት አቶ ሳንዶካን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የአጭር ጊዜ ታሪክ ውስጥ ሺንትስ ለሰራተኞቹ የመኖሪያ ቤት የገነባ የመጀመሪያው ኩባንያ ነው፤ ይህንንም ሌሎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያሉ ኩባንያዎች በአርዓያነት ሊከተሉ እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተዋል።

# በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሶስት ሺህ አራት መቶ በላይ ቤቶች እንደሚታደሱ ተገለጸ

**ዳግማዊት ግርማ**



አዲስ አበባ፡- በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሶስት ሺህ አራት መቶ በላይ ቤቶች እንደሚታደሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ኮሚሽን ገለፀ፡፡

የተቋሙ ምክትል ኮሚሽን አቶ ሙሰማ ጀማል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የ2014/2015 ዓ.ም የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት በሰባት መርሐግብሮችና በ14 ንዑሳን መርሐግብሮች የተለያዩ ተግባራት የሚከወ ኑበት ሲሆን፤ በዚህም ከሶስት ሺህ 400 በላይ ቤቶች እንዲታደሱ ይደረጋል፡፡

እንደ አቶ ሙሰማ ገለፃ፤ በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎቱ የሚታደሱት ቤቶች የአቅመ ደካሞች፣ የአረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የሐገር ባለውለታዎችን እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ነው፡፡

አቶ ሙሰማ በገለፃቸው፤ እስከ ሰኔ 30 የሚጠናቀቁ የቤት እድሳት ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው እስከ አዲስ ዓመት ድረስ ተግባሩ ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገበር ይሆናልም ብለዋል፡፡

በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎቱ ከ20 ሺህ የሚልቁ ሰዎች ነጻ የህክምና ድጋፍ እንደሚያገኙ ምክትል ኮሚሽነሩ አመላክተዋል፡፡

እንደ አቶ ሙሰማ ገለፃ፤ በመዲናዋ የሚገኙ የግል የጥርስ ህክምና ተቋማትን በማስተባበር 3 ሺህ ህሙማን ነጻ የጥርስ ህክምና እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን፤ በዓይን ህክምና ዘርፍ የተሰማሩ የጤና ተቋማትን በበጎፈቃደኝነትበማስተባበር ለ6 ሺህ የዓይን ህሙማን ነጻ ህክምና ያገኛሉ፡፡

አምስት የህክምና ቡድኖችን በማስተባበር ለስምንት ሺህ 800 አረጋውያን ፣ አካል ጉዳተኞች ነፃ ቅድመ ጤና ምርመራ ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል ያሉት አቶ ሙሰማ፤ በ40 ጤናጣቢያዎች 100 በጎ ፍቃደኛሐኪሞችን በማጋበዝ ሁለት ሺህ 200 ህሙማን ነፃ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋልም ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን የሚገመት የመንግሥት ወጪን ለመታደግ እንቅስቃሴዎች እንደሚደረጉ የገለፁት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ለ294 ሺህ 800 የህብረተሰብ ክፍሎች የአረፋ በዓልን ፣ አዲስ ዓመትን ፣ መስቀልን በዓላትን እንዲሁም የኢሬቻ welcoming ceremony ምክንያት በማድረግ የማዕድ ማጋራት መርሐ ግብር እንደሚከናወንም ገልጸዋል፡፡

በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በጎፈቃደኞችን በተዘጋጁ ፕሮግራሞች በማሳተፍ 570 ሺህ የከተማዋን ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ማከናወን የሚያስችል ግብ ቀርፀው ወደ ሥራ መግባታቸውንም አመላክተዋል፡፡

አጠቃላይ ለመርሐግብሩ ስኬታማነት ሁሉም ባለድርሻ አካል እንዲሁም በጎፈቃደኞች፣ ባለሐብቶች፣ የሙያ ማህበራትና የመንግሥት ሰራተኞች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት ፣ሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች ለበጎነት የሚሰሩ አካላት ለዚህ እቅድ ተግባራዊነት ድጋፍ እንደሚያደርጉም ጥሪ ቀርቧል፡፡

# “የመዲናዋ ህንፃዎች ግራጫ ቀለም ሊቀቡ ነው በሚል የሚናፈሰው መረጃ ከዕውነት የራቀ ነው”

\- ዮናስ ዘውዴ
የአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ



**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ህንፃዎች ሁሉ ግራጫ ቀለም ሊቀቡ ነው በሚል ከሰሞኑ በማህበራዊ ትስስር ገጾች የሚናፈሰው መረጃ ከዕውነት የራቀ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ዮናስ ዘውዴ አስታወቁ።

የቢሮ ኃላፊው በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብና ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ የህንፃ ስታንዳርድና የውጭ ማስታወቂያ ስታንዳርድ እየተዘጋጀ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህን መነሻ አድርጎ በማህበራዊ ትስስር ገጾች አዲስ ከተማ ግራጫ ቀለም ልትቀባ ነው በሚል በስፋት ሲዘዋወር የታየው መረጃ የተሳሳተ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ የከተማዋ ህንጻዎች ቀለም ምን አይነት ይሁን የሚለው ጉዳይ ለውይይት ቀረበ እንጂ የከተማ አስተዳደሩ በጉዳዩ ላይ ምንም አይነት ውሳኔ እንዳላሳለፈ አመልክተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይም ከዚህ ቀደም «ከተማችን ቡራቡሬ ሆና ባለቤት አልባ መስላለች» ማለታቸውን ያስታወሱት የቢሮ ኃላፊው፤ ይህን ችግር ማንኛውም የመዲናዋ ነዋሪም ሊታዘብ ይችላል። የከተማ አስተዳደሩም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቷል ብለዋል።

ችግሩን ለመፍታት የውጭ ማስታወቂያውና የከተማዋ ቀለም ሁኔታ የሚመራበት ስታንዳርድ ዝግጅት ተደረገ እንጂ ውሳኔ ላይ አለመድረሱን ጠቁመዋል።

በቅርቡ በጉዳዩ ላይ ከባለሀብቶች ጋር ውይይት ተደርጎ እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው፤ ይህን መነሻ አድርገው አንዳንድ ግለሰቦች ለግራጫ ቀለም የመሰላቸውን ትርጓሜ ሲሰጡ ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩ በማህበራዊ ትስስር ገጾች እንደሚዘዋወረው ተግባር ላይ የዋለ ሳይሆን ገና ለምክክር የቀረበ መሆኑን መገንዘብ ይገባል ብለዋል።

ከተማዋ ላይ አንድ አይነት ቀለም ብቻ ለቀለም ቅብ ሥራ ያስፈልጋል የሚል እሳቤ መያዝ እንደሌለበት የተናገሩት ኃላፊ፤ ለአስፈላጊው ህንጻና አካባቢ የሚመጥን ዝብርቅርቅ ያልሆነና ለዓይን የሚማርኩ ቀለማትን የያዘ ስታንዳርድ እንደሚኖረን ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

በዚህ ረገድ በተከታታይ በምናደርጋቸው ውይይቶችና የሕዝብ ተሳትፎ መድረኮች ላይ የሚገኙ ግብዓቶችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረግ መሆኑን የከተማዋ ነዋሪ ማወቅ አለበት ብለዋል።

የከተማዋ ቀለም ስታንዳርዱን የጠበቀ መሆን አለበት የሚለው ሀሳብ ሁላችንንም ሊያስማማ የሚችል ጉዳይ ነው ያሉት ዮናስ ዘውዴ፤ የከተማው ነዋሪ ያልመከረበትና ስምምነት ላይ ያልደረሰበት ምንም ነገር ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ጠቁመዋል።

በቀጣይነት በሂደቱ ላይ በርካታ ባለድርሻ አካላት እንደሚሳተፉና ተወያይቶ መግባባት ላይ መድረስን እንደሚጠይቅ የጠቆሙት ቢሮ ኃላፊው፤ ሥራው ካለው ስፋት አንጻር ስታንዳርዱ በዚህ ጊዜ ተጠናቆ ወደ ትግበራ ይገባል የሚለውን ለመግለጽ እንደሚቸገሩ ጨምረው ገልጸዋል፡፡



# በሆልቲካልቸር ዘርፍ ከ4 መቶ 99 ሚሊዮን ዶላር በላይ መገኘቱ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በ10 ወራት ውስጥ ከሆልቲካልቸር ዘርፍ ከ4 መቶ 99 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሆልቲ ካልቸር ኢንቨስትመንትና የኤክስፖርት ድጋፍ ዳይሬክተር አቶ መኮንን ሰለሞን በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በጉምሩክ ኮሚሽን የውጭ ንግድ መረጃ መሰረት በ10 ወራት ውስጥ ከአበባ፣ ከአትክልትና ከፍራፍሬ በአጠቃላይ ከሆልቲካልቸር ዘርፍ የተገኘው ገቢ 4 መቶ 99 ሚሊዮን 4 መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዶላር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ከዚህ ውስጥ 4 መቶ 21 ሚሊዮን ብር የተገኘው ከአበባ ምርት ሲሆን ከፍተኛ ድርሻን እንደሚይዝ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከአትክልት ምርት ከ61 ነጥብ 9 ሚሊዮን በላይ የውጭ ገቢ የተገኘ ሲሆን ከፍራፍሬ ከ16 ሚሊዮን ዶላር በላይ መገኘቱን አስረድተዋል፡፡

ከእቅዱ አንጻር በሆልቲካልቸር ዘርፍ የእቅዱን 102 ነጥብ 4 በመቶ ማሳካት ተችሏል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ15 ነጥብ 3 በመቶ እድገት አሳይቷል፡፡ ከሆልቲካልቸር ምርት በ2013 ዓ.ም ተመሳሳይ ጊዜ የተገኘው ገቢ 4 መቶ 33 ሚሊዮን ዶላር እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ ካለፈው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር የአበባ ምርት በ9 ነጥብ 4 በመቶ፣ የአትክልት በ68 ነጥብ 2 በመቶ እና የፍራፍሬ ዘርፍ በ45 በመቶ እድገት ማሳየቱን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ የአበባ ምርትን በስፋት ከምትልክባቸው ሀገራት መካከል ኔዘርላንድ፣ሳውዲአረቢያ፣ እንግሊዝ፣ ኖርዌ፣አሜሪካ፣ ጃፓን፣ጣልያን፣ካናዳ እና ጀርመን መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ሶማሊያ፣ጅቡቲና ሳውዲ አረቢያ ከፍተኛ የአትክልት ምርት ተቀባይ ሀገሮች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

# በበጀት ዓመቱ የገቢ ኮንትሮባንድ ንግድ ጭማሪ ማሳየቱ ተገለፀ

**ውብሸት ሰንደቁ**



አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት የኮንትሮባንድ ንግድ ከአለፈው ዓመት ተመሳ ሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የወጪ ኮንትሮባንድ ቀንሶ የገቢ ኮንትሮባንድ የመጨመር አዝማሚያ ማሳየቱን የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ከኮንትሮባንዲስቶች ጋር በተደረገ ትንቅንቅ በዘንድሮው ዓመት አራት፣ ባለፈው ዓመት ደግሞ ስድስት የኮንትሮባንድ ንግድ ተቆጣጣሪዎች ሕይወታቸውን ማጣታቸውም ተነግሯል፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር በያዝነው ሳምንት አጋማሽ የበጀት ዓመቱን የአሥር ወራት አፈፃፀም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቧል፡፡ የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው እንደገለፁት፤ በ2014 በጀት ዓመት የኮንትሮባንድ ንግድ ከአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የወጪ ኮንትሮባንድ ቀንሶ የገቢ ኮንትሮባንድ የመጨመር አዝማሚያ አሳይቷል፡፡

በዘንድሮው ዓመት አሥር ወራት ውስጥ የታየው የኮንትሮባንድ ንግድ ከአለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የገቢ ኮንትሮባንድ ንግድ በ54 ነጥብ 26 የጨመረ ሲሆን የወጪ የኮንትሮባንድ ንግድ ደግሞ በ12 ነጥብ 15 በመቶ መቀነሱን ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡

ከሀገር ውስጥ በሕገ ወጥ መንገድ ወጥተው የሚሸጡ ቁሳቁሶች የወጭ ኮንትሮባንድ ሲባሉ፤ ከሀገር ውጪ ወደ ሀገር ውስጥ በሕገወጥ መንገድ ገብተው የሚያዙት ደግሞ የገቢ ኮንትሮባንድ ይባላሉ፡፡

የገቢና የወጪ ኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር የተደረገው መከላከል ከፍተኛ እንደነበር የጠቀሱት አቶ ላቀ፤ በአሥር ወራት ውስጥ 3 ነጥብ 5 ቢሊየን የሚገመቱ የገቢ ኮንትሮባንድ ዕቃዎች፤ 492 ነጥብ 9 ሚሊየን ብር የሚገመቱ የወጪ ኮንትሮባንድ ዕቃዎች በድምሩ 4 ነጥብ 04 ቢሊየን ብር የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ቁሳቁሶችን በቁጥጥር ሥር መዋሉን ተናግረዋል፡፡

የኮንትሮባንድ ንግድ የፍትሕ ሥርዓቱን የሚያዛባ እና ጤናማ ማሕበረሰብ ለመገንባት ተግዳሮት በመሆኑ ማሕበራዊ ተፅዕኖው ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ላቀ አያሌው፤ በበጀት ዓመቱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ከመያዝ ጎን ለጎን ኮንትሮባንዲስቶችንም ለመያዝ በተደረገው ጥረት 613 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ውለው በምርመራ ሂደት ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

በዚህ ሥራ ውስጥ አስተዋፅዖ የነበራቸው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮች እና ሠራተኞች፤ የሀገር መከላከያ ሠራዊት፤ የፌዴራል ፖሊስ፤ የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች፣ እንዲሁም የሀገሪቱ ሕዝቦች በሠሩት የመጠቆምና የማጋለጥ ሥራ ምሥጋና እንደሚገባቸውም ጠቁመዋል፡፡

የኮንትሮባንድ ንግድን የመቆጣጠር ሥራ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ሥራ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር በአለፈው ዓመት አራት ሰዎች በዘንድሮው አሥር ወራት ውስጥ ደግሞ ስድስት ሰዎች በድምሩ አሥር ሰዎች ሕግ ሲያስከብሩ መስዋዕትነት መክፈላቸውንና ሌሎች አካላትም ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ገልፀዋል፡፡

ዜና

# በኦሮሚያ ክልል ከምርትና ገበያ ውጪ የሆኑ 30 ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ ተመለሱ

ሙሳ ሙሐመድ

ሱሉልታ፡- በፀጥታ ችግር፣ በኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ አቅርቦትና ሌሎች ምክንያቶች ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙት 130 በላይ ከምርትና ገበያ ውጪ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች መካከል 30ዎቹ ወደ ሥራ መመለሳቸውን የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ አስታወቀ።

የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ኃላፊ ኢንጅነር ግርማ ረጋሳ ከጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት የመስክ ምልከታ እንደገለጹት፤ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙትና በተለያዩ ምክንያቶች ከምርትና ከገበያ ውጪ ከነበሩት 130 በላይ ኢንዱስትሪዎች መካከል 30ዎቹ ወደ ሥራ ተመልሰዋል።

ኢንዱስትሪዎቹ ከምርትና ከገበያ ውጪ ሆነው የነበሩበት ምክንያት በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ፣ በኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር፣ በውጭ ምንዛሪ እጥረት እና በመሰረተ ልማት ችግር መሆኑን አስታውሰዋል።

የአሰራር አለመናበብ፣ አስተዳደራዊ ችግር እና በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተው የፀጥታ ችግርም ከምርትና ገበያ እንዲወጡ ምክንያት እንደነበረም ነው ኢንጅነር ግርማ የተናገሩት።

ከምርት እና ከገበያ ውጪ ሆነው የቆዩ ኢንዱስትሪዎችም በ ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ችግሮችን በመቋቋም በቅንጅት በመስራት በመተባበር ወደ ሥራ ለመመለስ በተደረገ ጥረት ወደ ሥራ እየተመለሱ መሆናቸውን ነው ኢንጅነር ግርማ የተናገሩት።

በዚህ ንቀናቄ ወደ ሥራ ከገቡት መካከልም በሱሉልታ የሚገኙት ላቭግራስ ኢትዮጵያ፣ በላያ ኢንዱስትሪያል የውሃ ማምረቻ ኩባንያ፣ አሌልቱ ወተት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ እንደሚገኙበትም ጠቁመዋል።

በሰንዳፋ አካባቢም የአፍራን ግሎባል ቢዝነስ የጁስ ማምረቻ ኢንዱስትሪና ገላን የምግብ ምርቶች ፋብሪካም ሥራ ከጀመሩት ኢንዱስትሪዎች መካከል መሆናቸውን ገልጸዋል።

የላቭግራስ ኢትዮጵያ ፋብሪካ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሰናይት ታደለ እንደተናገሩት፣ ፋብሪካው ከኮሊስትሮል ነፃ አልሚ ምግብ በማምረት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንደሚያቀርብ አስታውሰዋል።

ፋብሪካው በሊዝ ክፍያ፣ በፋይናንስ እጥረት፣ እንደ መብራትና መሰል የመሰረት ልማት ችግሮች ሳቢያ ማምረት አቋርጦ እንደነበርም አስታውሰዋል። በቀጣይነት ፋብሪካው የተሻለ ጥራት ያለው ምርት ለማምረትና በገበያ ላይም ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀጥል እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

ከአካባቢው አምራቾች ጋር ያለውን የገበያ ትስስር ለማጠናከር እንዲረዳው የፋይናንስ ተቋማትን ድጋፍ



የአፍራን ግሎባል ቢዝነስ የጁስ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የማምረት ሂደት




ወይዘሮ ሰናይት ታደለ





ኢንጅነር ግርማ ረጋሳ

እንደሚሻ የጠቆሙት ወይዘሮ ሰናይት፤ በተደረገላቸው ድጋፍ ወደ ሥራ መመለሳቸውን ተናግረዋል።

በሰንዳፋ የሚገኘው የአፍራን ግሎባል ቢዝነስ የጁስ ማምረቻ ኢንዱስትሪ አስተዳደር አቶ ጋሻው ኃይለሚካኤል በበኩላቸው፤ ፋብሪካው በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ለዘጠኝ ወራት ከምርት እና ገበያ ውጪ ሆኖ እንደነበር ገልጸዋል። በ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ወደ ሥራ መግባቱንና ምርት መጀመሩን አስታውቀዋል።

አቶ ጋሻው አክለውም፣ ኢንዱስትሪዎቹ ያጋጠማቸውን ችግር በመፍታት ወደ ሥራ እንዲመለሱ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጀምሮ በክልሉና በአካባቢው ኢንቨስትመንት ቢሮ በኩል የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን አመልክተዋል። ተግባሩ የዘመቻ ሥራ ሆኖ እንዳይቀር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል ሲሉ ጠይቀዋል።



## ኮቪድ 19 የመቀነስ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ከአንድ በመቶ ያለፉ አይደሉም፡፡ አሁንም ስርጭቱ በህብረተሰብ ደረጃ በሁሉም ክልሎች ስለሚገኝ በበሽታው የሚያዙ፣ የሚታመሙና ወደ ጽኑ ህክምና የሚገቡ ሰዎች አሉ ብለዋል፡፡

አሁን ካለው የስርጭት ሁኔታ አንጻር የኮቪድ 19 መከላከያ መመሪያዎች በተወሰነ ደረጃ መሻሻላቸውን ያስታወሱት ዶክተር መብራቱ፤

የኮቪድ 19 አገልግሎትን ብቻ ሲሰጡ የነበሩ ተቋማት መደበኛውን አገልግሎት ጨምረው በተቀናጀ መልኩ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ ከ600 በላይ ተቋማት የተቀናጀ ህክምና መስጠት የሚችሉበትን አቅም እየተፈጠረ ነው ያሉት ዶክተር መብራቱ፤ በቀጣይነትም እስከ አንድ ሺ 400 የሚደርሱ የጤና ተቋማት የኮቪድ ህክምናን ለህብረተሰቡ እንዲሰጡ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አስተባባሪው ገለጻ፤ አሁን ላይ የኮቪድ 19 ስርጭት ቀነሰ ማለት ቫይረሱ የለም ማለት አይደለም፡፡ አሜሪካ ስርጭቱ በመቀነሱ ማስክ መጠቀም ቆሞ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ ግን በቀን 100ሺ ሰው በቫይረሱ እየተያዘ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እኛም ጋር ጊዜውን ጠብቆ በማዕበል ደረጃ ሊመጣ የሚችልበት እድል ስላለ የህክምና እቃዎችንና ግብዓቶችን ከውጭ እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ክትባት ከመገኘቱም በፊት በቫይረሱ በቀላሉ ሊያዙና ሕይወታቸው ሊያልፍ የሚችሉ ዜጎች ትኩረት ተሰጥቷቸው ክትባት እንዲያገኙ በመደረጉ ስርጭቱንና የሚሞቱ ሰዎችን ቁጥር በመቀነስ በኩል ጉልህ ሚና ነበረው፡፡ በግንቦት መጨረሻ አካባቢ ክትባቱን እንደገና በዘመቻ ለመስጠትም ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

እስካሁን ድረስ ከ25 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ክትባት እንዲያገኙ መደረጉን አስታውሰው፤ እስከያዝነው ዓመት መጨረሻ ክትባት የወሰዱ ዜጎችን ቁጥር 45 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዷል፡፡ ከክትባቱ ጎን ለጎንም እስካሁን ተግባራዊ ያልተደረጉ ሙሉ ለሙሉ ፈውስ ባይሰጡም ኮቪድ 19ኝ ለማከም የሚረዱ የዓለም ጤና ድርጅት እውቅና የሰጣቸው መድሃኒቶችን ለማስገባትም ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

## ‹‹ዳያስፖራው በአሜሪካ ምርጫ ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ለማስቆም የሚያስችሉ ሥራዎችን መላው ዲያስፖራ ተቀናጅቶ እየሰራ ይገኛል። በተለይም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት በአሜሪካ ፖለቲካ ወሳኝ ሚና ያላቸውን ሴናተሮችን፤ የሙብት ተሚጋቾችንና የማህረሰብ አንቂዎች የኢትዮጵያን እውነታ እንዲገነዘቡና የእንቅስቃሴው አካል እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው።

‹‹አንዳንድ በመንግሥት ላይ ያኮረፉ ሰዎች ለጊዜውም ቢሆን ቢደግፉትም አሁን ላይ ግን አብዛኛው ዳያስፖራ እውነታውን ስለተገነዘበ ማዕቀቡ እንዳይፀድቅ ብዙ ታግሷል፤ እየታገለም ይገኛል›› ያለው አርቲስት ተስፋዬ ቀደም ሲል ማዕቀቡን ሲደግፉ የነበሩትም ከመንግሥት በላይ ህዝብን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ መሆኑን መገንዘባቸውን ተናግሯል። ‹‹ማዕቀቡን ደግፈው አቋማቸውን ያሳዩ አንዳንድ ሰዎች ባለማወቅ ነው ይህንን ሲያደርጉ የነበሩት የዚህን ሰነድ አደገኛነት ካስረዳናቸውና በአገር ሊኮረፍ እንደማይቻል ከተገነዘቡ በኋላ ብዙዎቹ አቋማቸውን ቀይረዋል›› ብሏል። በመሆኑም በያሉበት የሙያ መስክ የአሜሪካ መንግሥት ላይ ጫና የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ መሆኑን አስረድቷል። ፓርኪንግ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያኖች ሳይቀሩ መረጃ በመሰብሰብና በማቀበል ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን ጠቁሟል።

‹‹በቅርቡ እኛ በምንኖርበት ከተማ ላይ የአሜሪካ መንግሥት ሶስተኛ ሰውና አፈጉባኤ የሆነችው ናንሲ ፔሎሲ በመጣችበት ወቅት መረጃው አስቀድሞ ስለነበረን በቀጥታ ደብዳቤያችን እንዲደርሳት አድርገናል። ከዚህም ባሻገር ሬቬረንድ ብራውን የተባለው ጥቁር የማህበረሰብ አንቂ ይዘነው በመሄድ እንቅስቃሴያችን መላው የአሜሪካ ህዝብ እንዲደግፈው እየተደረገ ይገኛል›› በማለት አብራርቷል።

በተለይም በአሁኑ ወቅት የትግራይ ተወላጅ የሆኑና ቁልፉ ቦታ ላይ የተቀመጡ ግለሰቦች ከስልጣናቸው እየተነሱ መሆኑን ዳያስፖራው ለሚያደርገው እንቅ ስቃሴ መሳካት ወሳኝ ሚና እንዳለው አርቲስቱ ተናግ ሯል። ‹‹የቴድሮስ አድህኖም ነገርም ወደ ውድቀት የሚሄድ በመሆኑ አሁን ለኢትዮጵያ ጥሩ በር የሚከፈት ይመስለኛል። በመሆኑም ምርጫው እስከሚገባደድ ድረስ ሁላችንም በርትተን ለሃገራችን ዘብ መቆም አለብን›› በማለት አስገንዝቧል። በተለይም ነዋሪነታቸውን አሜሪካ ያደረጉና አሜሪካዊ ዝግነት ያላቸው ኢትዮጵያውያን በሙሉ በምርጫው የነቃ ተሳትፎ በማድረግና ኢትዮጵያን የሚደግፉ ሴናተሮችን በመምረጥ ለአገራቸው ታሪካዊ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝቧል።

## አሸባሪው ህወሓት በወረራ በያዘው...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መድረሱም ተነግሯል፡፡

መንግሥት ዜጎችን ለመታደግ እያደረገ ባለው ርብርብ ለአንድ ተፈናቃይ በወር 15 ኪ/ግ የምግብ እህል ቢያደርስም የመብራት፣ የውሃና ሌሎች አስፈላጊ መገልገያዎች ባለመኖራቸው ተፈናቃዮች የሚሰጣቸውን እህል በመሸጥ ምግብ በመግዛት ላይ መሆናቸውን አቶ ከፍያለው አስታውቀዋል፡፡

በሌላ በኩል የክረምት ወቅት እየደረሰ በመሆኑና አብዛኛው ነዋሪ የሴፍቲኔት ተጠቃሚ ማህበረሰብ እንደመሆኑ መጠን በአሸባሪው ህወሓት ቁጥጥር ስር የሚገኙ አካባቢዎችና ሌሎች የዞኑ ወረዳዎች በሽብር ቡድኑ ጥቃት ምክንያት ውድመት የደረሰባቸው በመሆኑ ዜጎች ይበልጥ ለጉዳት እንዳይዳረጉ የሚመለከተው አካል ሁሉ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ጠይቀዋል፡፡

በክረምት ወቅት በመጠለያ ውስጥ የሚቆዩ ዜጎች ለተለያየ የወረርሽኝ አደጋ ሊጋለጡ ስለሚችሉ አሁን ባለው ሁኔታ የመጠለያ ድንኳን ውስጥ የሚገኙ ዜጎች በክረምት ወቅት በዝናብና በወረርሽኝ እንዳይጋለጡ በቂና የተጠናከረ ድንኳን በማዘጋጀት ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትና ይህም ከብሔረሰብ አስተዳደሩ አቅም በላይ በመሆኑ መንግሥት ተገቢውን ሥራ በወቅቱ ማከናወን እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

በበጎ አድራጎት ተቋማትና በመንግሥት የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ያነሱት አቶ ከፍያለው፣ ለተረጂዎች የሚቀርበው እርዳታና የተረጂዎች ቁጥር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ አስከፊ ረሃብ ሊከሰት እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

ብሔረሰብ አስተዳደሩ ከመንግሥትም ሆነ ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች የሚቀርቡትን እርዳታዎች በፍትሐዊነት ከማድረስና በአካባቢው የሚስተዋሉ ችግሮችን ከማሳየት በዘለለ በዚህ ረገድ የጎላ አቅም እንደሌለው አስታውቀዋል፡፡

አሁን የተከሰቱ የወረርሽኝ በሽታዎችና ሌሎች ሰፋፊ ተግባራት በክልሉ እንዲሁም በፌዴራሉ መንግሥት የሚፈቱ ጉልህ ችግሮች በመሆናቸው መንግሥት ይህን ችግር በመገንዘብ አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ ዜጎች ላይ ከዚህ በላይ ችግር እንዳይደርስ የበኩሉን ሚና መጫወት እንደሚገባው ኃላፊው ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል


## ከማህበረሰቡ ወጥቶ ማህበረሰብን ማገልገል ያስገኘው እርካታ

ገጽ 13



## ‹‹አገርን የሚያሳድገው የመንግስታት መለዋወጥ ሳይሆን የሕዝብ አዕምሮ መለወጥ ነው››

- አርቲስት ተስፋዬ ሲማ

ገጽ 6



## በፈተናዎች የጸና- በጥንካሬ የበረታ ማንነት

ገጽ 16

### ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የቦታና ቤት ግብር ለማስጀመር ቅድመ እንቅስቃሴ

**ሶሎሞን በየነ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ትኩረት ከሰጣቸው ቅልፍ ፕሮግራሞች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት፣ የቤቶች ልማት ፕሮግራም፣ የጤናና የትምህርት ልማት ዘርፎች፣ የመንገድ ልማት ዘርፍ፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን ማሳደግና ሌሎች ቁልፍ የኅብረተሰቡ መሰረታዊ ፍላጎቶች ይገኙበታል። ይህንን ለማሳካት ደግሞ አስተማማኝ የበጀት ምንጭ ያስፈልጋል።

ከዚህ አኳያ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ከተማዋ ወጪዋን በራሷ ገቢ ለመሸፈን ያነገበችውን ራዕይ ዕውን ለማድረግ የከተማዋ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ከነዚህም አዳዲስ ግብር ከፋዮችን ወደታክስ መረቡ በማስገባት እና በግብር ስርዓቱ ያልተካተቱትን በጥናት በማስደገፍ ወደ ታክስ ሥርዓቱ በማስገባት የታክስ መሠረቱን የማስፋት ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ከዚህ አንጻር ቢሮው የቦታና ቤት ግብር በተመረጡ 11 ፓይለት ወረዳዎች ለመጀመር የሚያስችል ኦረንቴሽን ከሰሞኑ ሰጥቷል፡፡

ኦረንቴሽን በተሰጠበት ምድረክ ላይ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ውዴ ቴሶ፤ ባሳለፍነው የግብር ዘመን የኢ-ቲ-ታክስን በሁሉም ወረዳዎች ተግባራዊ በመደረጉ በግብር አሰባሰቡም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ውጤት መታየቱን በመግለጽ፤ ይህንን ውጤት በቦታና ቤት መረጃ ማጥራትም ልንደግመው ይገባል ብለዋል፡፡

በተመረጡት ወረዳዎች ላይ አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ በሙከራ ሥራ ላይ መሆኑን ወይዘሮ ውዴ ጠቁመው፤ የቦታና ቤት ወቅታዊ የሆነ



**ወይዘሮ ውዴ ቴሶ፤**

ባክ አፕ ወይም መረጃ በመውሰድ እስከግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ.ም በኢ-ቲ-ታክስ ላይ እንደሚገባና የቦታና ቤት አጠቃላይ ሥራዎች በአዲሱ ሲስተም ላይ በይፋ ይጀምራል ብለዋል።

አያይዘውም የ2015 ዓ.ም የግብር ማስከፈያ ወቅት እየተቃረበ በመሆኑ ያልጠሩ ቀሪ መረጃዎችን በመረጃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ባወጣው መስፈርት መሰረት ሁሉንም ወረዳዎች የተጠቃለለ የዳታቤዝና ኤክስኤል መረጃዎችን አደራጅቶ እስከ ግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ብቻ መላክ አለበት፡፡ በየደረጃው የሚገኘው አመራርና ባለሙያ በተላለፈው አቅጣጫ መሰረት በኃላፊነት ስሜት መረጃዎቹን “ባክ አፕ” እያያዙና እያረጋገጡ አላስፈላጊ ምልልስን ሊያስቀር በሚችል መልኩ እንዲፈጸሙ፤ ቢዘገይ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ ለሥራው ትኩረት እንዲሰጡት





መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በኦረንቴሽኑ ወቅት በመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬትና በከስተር አጠቃላይ የትግበራው ሂደት፣ ትግበራው ስኬታማ እንዲሆን የተከተሏቸው ሂደቶች እና በኢ-ቲ-ታክስ ሲስተም ላይ ለቦታና ቤት የተጨመሩ ለውጦችን ገለፃ ተደርጓል። በመረጃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ በኩል አጠቃላይ የወረዳዎች መረጃ ማጥራት ሂደት ያለበትን ሂደት ቀርቦ በመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር መሪነት ውይይት ተካሂዶ ከተሳታፊዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች በመረጃ ማጥራት አብይ ኮሚቴ አባላት፣ በከስተር እና በዳይሬክቶሬቱ ምላሽ የተሰጠባቸው ሲሆን፤ የተወሰኑ የበላይ አመራር ውሳኔ የሚፈልጉትን ደግሞ ለሚመለከተው ለማቅረብ መግባባት ላይ ተደርሷል።

እንዲሁም በኦረንቴሽኑ የቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች መረጃ ቴክኖሎጂ ቡድን አስተባባሪዎች፣ በፓይለት የተመረጡ ወረዳዎች ተወካዮችና የዋ ናው መስሪያቤት የመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች እና የአልሚው ከስተር ድርጅት ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡


**አድራሻ፡-**

ስልክ የቢሮ ኃላፊ 0115575790
የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741
የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608

የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O. Box 27400 code 1000


**የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹አገርን የሚያሳድገው የመንግስታት መለዋወጥ ሳይሆን የሕዝብ አዕምሮ መለወጥ ነው››

- አርቲስት ተስፋዬ ሲማ

ማህሌት አብዱል

የዛሬው የዘመን እንግዳችን አንጋፋ ከሚባሉት የኪነ-ጥበብ ሰዎች አንዱ ነው። በርካታ ደራሲያን የፈጠራ ችሎታቸውን ጨምቀው የከተቧቸውን ድርሰቶች በመድረክ ላይ ሁለንተናዊ ህይወት በመስጠት አንቱ ወደሚሰኝበት ከፍታ የደረሰ የጥበብ ሰው ነው። በተለይም በፀጋዬ ገብረመድህን «ሀሁ ወይም ፐፑ» ሥራ የተመልካቹን መንፈስ በመግዛት ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል። ይህ የኪነ-ጥበብ ሰው ተስፋዬ ሲማ ይባላል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቲያትር ጥበባት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። እንደተመረቀ የቲያትር ክፍል ኃላፊ በመሆን አርሲ ክፍለሀገር ሰርቷል። አልቆየም እንጂ የባህል መምሪያ ኃላፊ በመሆንም ቦረና ነገሌ ሄዶ የጥበብ አዝመራውን ጀባ ብሏል። በአዲስ አበባ ባህልና ስፖርት ቢሮ የኪነ-ጥበብ ዋና ክፍል ኃላፊ በመሆንም ከአገር እስከሚወጣ ድረስ የወጣትነት ጉልበትና ላቡን አንጠፍጥፎ አገልግሏል።

ለአምስት ተከታታይ ዓመታት በቲያትርና በስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ትምህርት ቤት በመክፈት የቲያትር አፃፃፍ አዘገጃጀት እንዲሁም የአተዋወን ብቃትን በማስተማር ዛሬ በየቴአትር ቤቱ፣ በፊልም ኢንዱስትሪው ስም ያላቸውን በርካታ የጥበብ ሰዎች አፍርቷል። በአዲስ አበባ ከተማ የቲያትርና የሙዚቃ ክበቦች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ በማድረግም ሞያዊ አሻራውን አስቀምጧል። በብሔራዊ፣ በአገርፍቅር፣ በአዲስ አበባ የቲያትርና ባህል አዳራሽ፣ በራስ ቲያትር በትወና እና በአዘጋጅነት ምርጥ ስራዎቹን ለተመልካች አቅርቧል። በሬዲዮ ድራማና በቴሌቪዥን በፊልም ስራዎቹም ብቃት ያለው ችሎታውን አሳይቶናል። በኋላም በእነዚህ ምርጥ ስራዎቹ የተመልካችን ቀልብ በመሳቡ በፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ የተፃፈውን "ፍቅር በአሜሪካ" ቲያትርን በመያዝ አሜሪካን ገባ።

ዓላማው ያዘጋጀውን ቲያትር አቅርቦ እንደጨረሰ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ቢሆንም በወቅቱ ከፍተኛ የፖለቲካ ውዝግብ ያስነሳውን €€ሀሁ ወይም ፐፑ« የተሰኘው የፀጋዬ ገብረመድህን ድርሰት በመተወንና በማዘጋጀት በማቅረቡ በወያኔ መንግስት ጥርስ ውስጥ ገባ። እንዲሁም በባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን የተመሰረተውን ቅዳሜ ቅኔ የጥበብ ማህበር መሪ በመሆኑ በሚሰራበትም ሆነ በማንኛውም ቲያትር ቤት ምንም አይነት ስራ እንዳይሰራ እገዳ ተጣለበት። በዚህ ምክንያት የሚወደውን ሙያ በመተው ለስራ በሄደባት አሜሪካ ጥገኝነት ጠይቆ ወደአገሩ ሳይመለስ እንደወጣ ቀረ። ይሁንና በስደት በቆየባቸው ዓመታት በተለይም ባለፉት 22 ዓመታት ከጣይቱ የኪነ-ጥበብና የትምህርት ማዕከል ጋር በመሆን በርካታ ቲያትሮችን በመፃፍ፣ በማዘጋጀትና በመተወን መላውን አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውሮፓ፣ደቡብ አፍሪካ እንዲሁም ከሌሎች በርካታ አንጋፋና ወጣት ባለሙያዎች ጋር በመሆን የጥበብ ስራዎችን ለህዝብ ያቀረበ ብርቱ የኪነ ጥበብ ባለሙያ ነው።

በትምህርት ቤቱ "ሰቃዩ " እየተባለ የሚቆላመጠው ተስፋዬ በአሜሪካ ቆይታው ከጥበቡ ጎን በፋርማሲ ሙያ ተምሮ ላለፉት 19 ዓመታት ሳሚት በተሰኘ ኦክላንድ ከተማ በሚገኝ ሆስፒታል አገልግሏል። ነገርግን የወያኔ ወኪሎች ከግብፃዊ አለቃው ጋር ተመሳጥረው ለኢትዮጵያ በተባለ ጉዳይ ፈጥኖ የሚደርሰውን ተስፋዬ ሲማን ከስራው አፈናቀሉት። ይህ የጥበብ ሰው ይህ ሁሉ ችግር ሲደርስበት ከዓላማው ሸብረክ ሳይል የኢትዮጵያን ህልውና የደፈረውን ወያኔ ኢትዮጵያን በጦርነት ሲያምስ በሰሜኑ መከላከያ ላይ አሰቃቂ ድንገተኛ ጥቃት ሲፈፅም "እኔም መከላከያ ነኝ" በማለት የወታደራዊ ልብሱን ለብሶ በዓለም አደባባይ ላይ ለለሃገሩ ክብር ሞግቷል።

ዓለም አቀፍ ወረርሽኙ ኮቪድ 19 በወገን ላይ ብዙ እልቂት እንዳያስከትል በተደረገው ዘመቻና የህዳሴ ግድቡን በአስቸኳይ ጨርሶ ለውጤት እንዲበቃ ለማድረግም ሲያስተባብርና ገንዘብ በማሰባሰብ አገራዊና ጥበባዊ ግዴታውን የተወጣ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ ከ39 በላይ የዙም ገንዘብ ማሰባሰብ ላይ በመሳተፍ፣ ፕሮግራሙን በመምራት ጥበባዊና ታሪካዊ ዝግጅት በማቅረብ፣ ወገንን በመለመንና በማስተባበር ለኮቪድ፣ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ፣ ለአገር መከላከያና ለተፈናቀሉ ወገኖች ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመሆን በሚሊዮኖች የሚገመት ገንዘብ አሰባስቧል::

ይህ ብቻ ሳይሆን ከአምባሳደር ፍፁም አረጋና አምባሳደር ታዬ አፅቀ ሥላሴ ጋር በመሆን ባለፉት አራት ወራት ብቻ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር እንዲሰበሰብና ለወገን ፈጥኖ ለመድረስ ከጦር ሜዳው ያልተናነሰ ብርቱ ጥረት አድርጓል። €€አርበኛው የጥበብ ሰው« በሚል መጠሪያ በዳያስፖራው የሚሞገሰው ይህ የጥበብ ሰው አሁንም ለወገኑ ለመድረስ ከሰሞኑ ወደ እናት አገሩ ብቅ ብሏል። አዲስ ዘመን ጋዜጣም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የዛሬው እንግዳ በማድረግ እንደሚከተለው ይዞላችሁ ቀርቧል።



ፎቶ:-ፀሐይ ንጉሴ

**አዲስ ዘመን፡- ወደ ኪነ-ጥበቡ ዓለም የገባህበትን አጋጣሚ አስታውሰንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** ከልጅነቴ ጀምሮ ለኪነ-ጥበብ ልዩ የሆነ ፍቅርና ክብር ነበረኝ። ሆኖም ግን ተመልካችና አድማጭ እንጂ ተሳታፊ እሆናለሁ የሚል ሃሳብ አልነበረኝም። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለሁም የሳይንስ ተማሪ ነበርኩኝ። ከፍተኛ ትምህርት ስገባም አንደኛ ምርጫዬ የነበረው የተፈጥሮ ሳይንስ ነበር። ይሁንና ጋዜጣ ላይ ስሜ ተመድቦ ያገኘሁት ማህበራዊ ሳይንስ ላይ ነው። በመሆኑም በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ከነበሩት ትምህርት ክፍሎች የተሻለ ነው ብዬ ስላሰብኩኝ ቲያትር ለመማር አመለከትኩት። እናም በዚያ መንገድ ገባሁ በኋላ ግን ሙያውን ይበልጥ እየወደድኩት መጣሁ፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ በኪነ-ጥበቡ ዓለም ከፍተኛ ስም በነበራቸው በእነ መንግስቱ ለማ፣ ደበበ ሰይፉ፣ አቦነህ አሻግሬ እና ፕሮፌሰር ተስፋዬ ገሰሰ እጅ በመማሬ ራሴን እንደዕድለኛ ነው የምቆጥረው። ምክንያቱም በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ የሚቻለኝን ያህል በጥበብ ጎልብቼ እንድወጣ የእነዚህ ሰዎች ድርሻ ከፍተኛ ነበርና።

በነገራችን ላይ ገና የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለሁ ነው ራስ ቲያትር ሥራዎቼን ማቅረብ የጀመርኩት። የሶስተኛ ዓመት ተማሪ ሆኜ ደግሞ የቴሌቪዥን ድራማ አቀረብኩ። ከዚያ በኋላ ደግሞ አምስት ኪሎ ግቢ በሚታየው የቲያትር አዳራሽ በርካታ ቲያትሮችን አቅርቤያለሁ። የደራሲ ፍሰሃ በላይ እና የሌሎች በርካታ አንጋፋ ደራሲያንን ስራዎችንም እሰራ ነበር። በትምህርት ቤት ቆይታዬ በተግባርናም በንድፈ ሃሳብም ጥሩ ተማሪ ስለነበርኩ በማዕረግ ነው የተመረኩት፤ ዲግሪዬንም ከፕሬዚዳንት መንግስቱ ሃይለማርያም እጅ የመቀበል እድሉን አግኝቻለሁ። ከዩኒቨርሲቲ ከወጣሁኝ በኋላ የትነው የምንገባው? የሚል ጭንቀት አልነበረብንም። በዚህም ሳይማር ያስተማረኝን ወገን ላመሰግን እወዳለሁ። ምክንያቱም በነፃ ተምረን እንደጨረስን ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ነው የተቀበለን። እኔ የደረሰኝ አርሲ ክፍለሃገር አሰላ ከተማ ውስጥ ነበር፤ እዚያም ለአንድ ዓመት ያህል የቲያትር ኤክሰፐርት ሆኜ ሰርቻለሁ። ከአንድ ዓመት በኋላ ዝውውር ስጠይቅ በመምሪያ ኃላፊነት ወደ ቦረና ነገሌ ነው የተላኩት። ይሁንና ለአንድ ቀን ብቻ ቆይቼ ነው ወደ አዲስ አበባ በቀጥታ የመጣሁት።

**አዲስ ዘመን፡- የቲያትር ባለሙያዎችን ወደ ማሰልጠን ሥራውስ እንዴት ገባህ?**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** ቦረና እያለሁ በአጋጣሚ አሞኝ ስለነበር የአዲስ አበባ ዝውውሩ ተሳካልኝ። እናም የአዲስ አበባ አስተዳደር የባህልና ስፖርት ቢሮ የኪነ-ጥበባት ዋና ክፍል ኃላፊ ሆኜ ተመደብኩኝ። እዚያ እንደተመደብኩኝ መጀመሪያ ያደረኩት ነገር ወደ ትምህርት ቤቶች መሄድ እና የሚኒሚዲያ ክበቦችን ማደራጀትና ማጠናከር ነው። በመቀጠልም ከክቡር ዶክተር ተስፋዬ አበበ ጋር በመሆን አማተሮችን በስፋት አሰልጥነናል። ይህም ስራ ከፍተኛ ቅቡልነት በማግኘቱ በክረምት በርካታ ፍላጎት የነበራቸውን ወጣቶችን ማሰልጠን ጀመርን። እነ ቴድሮስ ተክለአረጋይና ሱራፌል ወንድሙ ከመጀመሪያዎቹ ተማሪዎቼ መካከል ናቸው። ሁለተኛው ዙር ላይ ደግሞ እነ ሽመልስ አበራ፣ ቴዎድሮስ ለገሰ፣ ሀረገወይን አሰፋ፣ እመቤት ወልደገብርኤልንና አዜብ ወርቁን የመሳሳሉ ታላላቅ አርቲስቶችን ማፍራት ችለናል። እስከ አራተኛ ዙር በዚህ መልኩ ነው የቀጠለው። በተለይ ሁለተኛ ዙር ካስተማርኩኝ በኋላ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋዜጠኞችን በማምጣት የሬዲዮ ባለሙያዎችን፤ የቲያትር ባለሙያዎችን ደራሲያንንና የተለያዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ታላላቅ ሰዎች በመጋበዝ የተለያዩ ስልጠናዎችን ይሰጥዋቸው ነበር።

በዚያን ወቅት ስንሰራቸው የነበሩ አብዛኞቹ ስራዎች የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሥራዎችን ነበር። ያም ሆኖ ግን «ሎሬት ፀጋዬ ተማሪዎችን አይቀበልም» የሚል ነገር ይነሳ ነበር፤ ስለሆነም ለምን አልጋብዘውም ብዬ አሰብኩኝ። በወቅቱ የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስትሩ አማካሪ ነበረ። በቀጥታ ቢሮው አንኳኩቼ ገባሁና ተማሪዎቼ የሰሩትን ስራ እንዲያይልን ጋበዝኩት። ቀና ብሎ በመገረም አየኝና ለመምጣት ተስማማ። በቃሉ መሰረት ዝግጅታችን ላይ ታደመ። ያ ትልቅ ሰው የአማተር ልጆችን ስራ ለማየት መምጣቱ ለብዙዎች ግርምት ነው የፈጠረው። በዚህ ብቻ አልበቃም፤ በልጆቹ ስራ በመደነቁ እገዛ እንድናገኝና ሚኒስትሩ ባሉበት በብሔራዊ ቲያትር ሥራችን እንዲታይልን አደረገ። ልጆቹም በየቲያትር ቤቱ የመቀጠር ዕድል ተፈጠረላቸው። በእንዲህ አይነት መልኩ አራት ዙር ካስተማርን በኋላ ግን የመምሪያ ኃላፊው ተነስቶ ሌላ ሰው ሲመጣ ያኔ ሁሉንም ነገር ዘጋብኝ። ምክንያቱን በውል ባላውቀውም አንድም ከጋሽ ፀጋዬ ጋር ግኑኝነታችን በጣም ስለጠነከረ ሥልጠናው እንዲቆም ተደረገ።

ያም ቢሆን ግን ዘርፉን የሚረከብ ትውልድ የማስቀጠል ሥራችንን ተስፋ ቆርጠን አልተውነውም። አሁን ላይ ጦቢያ ጃዝ እንደሚያዘጋጀው ሁሉ በዚያ ወቅት እኛም ቅዳሜ ቅኔ ብለን የተለያዩ ጥበባዊ ሥራዎችን እናቀርብ ነበር። በንግድ ስራ ትምህርት ቤት የግጥም ጉባኤ ካካሄድን በኋላ ግን ያኔ ትንሽ ችግር ተፈጠረና መንግስትም ከለከለን። ከዚያ በኋላ የመጠመድ ነገር እየጎላ መጣ። አምስተኛው ዙር ያስተማርኩት በግል ትምህርት ቤት ውስጥ ነው። በዚያም ጊዜ እነ ግሩም ዘነበንና ቢኒያም ወርቁን የመሳሳሉ ድንቅ ሙያተኞችን ማውጣት ችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- ለኪነ-ጥበብ ካለህ ጥልቅ ፍቅር የተነሳ በርካታ ባለሙያዎችን ለማፍራት ብዙ ዋጋ ከፍለህ ከስኬት ደርሰሃል፤ እንዲያው የስኬት ሚስጥር ምን እንደሆነ ብትነግረን?**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** በግሌ ያለኝንና ያገኘሁትን ነገር መስጠት እወዳለሁ። አገርን የመውደድ ስሜትና ወገኖችን መርዳት በእኛ ጊዜ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው። በዚያ ላይ ደግሞ በአስተዳደጌም አገሬን እንድወድ ተደርጌ የተቀረፅኩኝ በመሆኑ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው መምህራን የሰጡኝ ትምህርት ለእኔ እንደ አዲስ ተቀብዬው የተጓዝኩበት በመሆኑ ነው ውጤታማ መሆን የቻልኩት ብዬ አምናለሁ። በተለይም ከነ ሎሬት ፀጋዬ ሥር እንደልጅ ቁጭ ብዬ ተሞክሮ መቅሰሜ አሁን ለደረስኩበት ደረጃ ትልቅ አቅም ሰጥቶኛል ብዬ አምናለሁ። ከዚህም ባሻገር የወጣትነት ጉልበትና እውቀት አፍኜ መቀመጥ የለብኝም ብዬ አምን ስለነበር ልክ እንደእኔ ሁሉ ሌሎች ተሰጥኦ ያላቸው ልጆች እድሉን እንዲያገኙና እንዲወጡ የበኩሌን ጥረት በማድረግም ጭምር ነው።

እንዳልሽው ለቲያትር ባለኝ ጥልቅ ፍቅር ሰዎች ቀዳዳውን አግኝተው መውጣት እንዲችሉ የሰራሁት ስራ በአብዛኛው ስኬታማ ነበር ማለት እችላለሁ። በእርግጥ በርካታ ተግዳሮቶች ነበሩብን፤ ሆኖም የማሰለጥናቸው ልጆች ለጥበቡ ያላቸው ፍቅርና ተገዢነት፤ ትጋት ያለኝን እውቀትና አቅም በአግባቡ እንዳወጣው እረድቶኛል ብዬ አስባለሁ። ይሁንና የነገውን ወጣት ለማፍራት ከወዲሁ

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ



ስለታየኝ ነው እንደዚያ ዋጋ የከፈልኩት አልልሽም፤ ግን ደግሞ የእኔን ስሜት ወይም የእኔን ኃላፊነት መወጣቴን ብቻ ነው የማስበው። በዚህም የኢትዮጵያን ኪነ-ጥበብ የሚሸከሙ ትላልቅ ሰዎችን ማፍራት ችያለሁ። አሁን ላይ ብዙዎቹ ከፍተኛ ሥፍራ ላይ ነው ያሉት።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ቲያትር እየተዳከመ ስለመምጣቱ ይነሳል፤ ለዚህ ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? ዘርፉንስ ለማሳደግ ምን መሰራት አለበት?**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** ወደፖለቲካው መስመር ካልገፋሽኝ በስተቀር በአንድ አገር ውስጥ የጥበብ መኖር የሕዝብን ስነልቦና እንደሚቀይር ግልፅ ነው። ምክንያቱም ኪነ-ጥበብ ብቻውን የህዝብ አዕምሮ ለመቀየር ከፍተኛ ኃይል ነው ያለው። አንድ ሺ ካድሬ ተሰብስቦ ከሚሰብከው ፕሮፖጋንዳ በላይ አንድ ቲያትር ትልቅ ኃይል አለው። አገርን የሚያሳድገው የመንግስታት መለዋወጥ ሳይሆን የህዝብ አዕምሮ መለወጥ ነው። አንድ መሪ የሚያደርጋቸው ነገሮች በኪነ-ጥበብ እስካልታገዘ ድረስ ህዝብና መንግስት መገናኘት ሲገባቸው አይገናኙም ማለት ነው። ኪነ-ጥበብ በማገናኘት የሚኖረው ሚና እጅግ በጣም ትልቅ ነው። ባለፉት 27 ዓመታት ዘርፉን ወደ አንድ ደረጃ ማሻገር ያልተቻለው ኢትዮጵያዊነት እንዲሞት ሲደረግ ጥበብም አብሮ እንዲሞት ተደርጓል። ጥበብ ከኢትዮጵያ መፍረስ ጋር አብሮ እየዘቀጠ እንዲሄድ ተሰርቷል። ለዚህ ነው በተቻለ መጠን መቶኛው በዓል ሲከበር ቲያትር ደግሞ እንዲያንሰራራ ሁላችንም መብታችንን ጮኸን ማስከበር አለብን ብለን በአንድ ድምፅ የተስማማነው።

በነገራችን ላይ በንጉሱም ሆነ በደርግ ዘመን ቲያትር ቤቶች እንዲስፋፉ ተደርገው እንደነበር ይታወቃል። ለዚህም ነው እነዚያን የመሳሰሉ ትልልቅ ሰዎችን ማፍራት የተቻለው። ያ ጊዜ ወርቃማው ጊዜ ነው የሚባለው። ከዚያ በኋላ ግን እየተዳከመ ነው የመጣው። እኔ ልጆቼን አስተምሬ ስጨርስ ጠርተውኝ «አንተ የምታስተምረው በኢህአዴግ ላይ ሰልፍ ልታስነሳ ነው ያሉኝ» እንደዚህ እያደረጉ ነው እያጠላለፉ እነሎሬት ፀጋዬን የመሳሳሉ ታላላቅ ባለሙያዎች ላይ ችግር ሲፈጥሩ የነበሩት። በሌላ በኩል ራስ ቲያትር ይሰራል ተባለ ግን እስካሁን አልተሰራም፤ ብሔራዊ ቲያትር ህንፃው በአዲስ መልክ ይገነባል ተባለ ግን አልተገነባም። አሁን ደግሞ ማዘጋጃ ቤት እንዲሁ ቅሬታ የሚያስነሳ ነገር ተከስቶ ነበር። ያንን ተከትሎ ነው አርቲስት ደበበ እሸቱ ቲያትር ቤቱ ከዚህ በኋላ ለባለሙያዎቹ የማይሰጥ ከሆነ ከሙያው እንደሚወጣ የተናገረው።

ከዚያ በኋላ ግን መንግስትም ጥሩና የሚያስደስት ምላሽ ሰጥቷል። እኔ በበኩሌ ውስጥ ያለውን ፖለቲካ ባላውቅም በጣም ነው የተደሰትኩት። አሁን ለባለሙያዎቹ የቲያትር ቤቱ ባለሙያዎቹ ቁልፉ ተሰጥቷቸው «ሜዳውም፤ፈረሱም ይኸው» ተብለዋል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያን በፊት ወደነበረችበት ከፍታ እናደርሳታለን ከተባለ ጥበቡን ማሳደግ ያስፈልጋል። ባለሙያውም መታገል አለበት። የመንግስት አመራሩም ለጥበቡ ማደግ በሩን መክፈት ይገባዋል። ያ ሲሆን ነው ችግሮቻችን በጥበብ የምንሻገረው፤ በመተሳሰብ አገርንና ዘርፉን የምናሳድገው።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ የኪነ-ጥበብ ሰዎች ከአገር ከወጡ በኋላ ጥበቡን እርግፍ አድርገው ይተውታል፤ አንተ ግን በአሜሪካ ቆይታ ከኪነ-ጥበቡ ሳትርቅ የመቆየትህ ሚስጥር ምንድን ነው?**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** እንደነገርኩሽ እኔ ከዚህ ስሄድም ቲያትር ለማሳየት ነው። ሆኖም ግን አልተሳካልኝም፤ ሙሉ ቡድኑም አልሄደም። እኔ በነበረብኝ ችግር ምክንያት ቀድሜ መውጣት ነበረብኝ። እዛ እንደሄድኩኝ የፖለቲካ ጥገኝነት ነው የጠየኩት። ወቅቱ ደግሞ ከመስከረም 11ዱ የአሜሪካ ሽብር ጥቃት በፊት ስለነበር ወዲያውኑ ነው ጥያቄዬ ተቀባይነት ያገኘው። በእርግጥም እዚህ ስራዬን እንዳልሰራ ታግቼ ነበር። በቀን አራት ጊዜ እንድፈርም፤ ግን ምንም ስራ እንዳልሰራ አግደውኝ ነበር። የትኛውም አይነት ፋይል እኔ ጋር አይመጣም፤ ማሰልጠንም ተከልክዬ ነበር። በቲያትር ቤቶችም ላይ አፈና ይካሄድ ጀመር። አንድ ቀን ግን አንድ የኢህአዴግ ባለስልጣን የሚሰራ ቲያትር ስላለ እንዳዘጋጅ ጠየቀኝ፤ እኔ ግን በመስሪያ ቤቴ መታገዴን ብነግረውም ዝም ብዬ እንድመጣ አዘዘኝ። እውነትም እሱ ጋር ሄጄ ዳይሬክት ካደረኩኝ ከሶስት ቀን በኋላ ስመለስ ሁሉም ዝቅ ብሎ ሰላም አለኝ። አንዳንዶቹ እንዳውም ሊያቅፉኝ ሁሉ ፈለጉ። በመሰረቱ እንደዚህ አይነት ነገር እጅግ በጣም ያበሽቀኛል። እኔ ከዩኒቨርሲቲ ወጥቼ ለሰባት ዓመታት የሰራሁት ስራና ግልጋሎት ከምንም ሳይቆጠር ሲያስጠምደኝ፤ አንድ ካድሬ ስለጠራኝና ልቀቁት ስላለ ብቻ የዚህን ያህል ሊያከብሩኝ አይገባም። ከዚያ በኋላ እንዳውም ጠርተውኝ ከጋሽ ፀጋዬ ጋር ያለህን ግንኙነት አቁም አሉኝ። በአጋጣሚ ደግሞ ቪዛ ሳገኝ እዚህ አገር ተመልሼ ብመጣም የማያሰራኝ ባለመኖሩ እዛው ለመቅረት ወሰንኩኝ። ምክንያቱም ማስተማር እወዳለሁ። እንዳልኩሽ የመኖሪያ ፍቃዴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተስተካከለለኝ።

የምኖረው ካሊፎርኒያ ኦክላንድ ከተማ ውስጥ ነበር፤ እዛ ጥቂት እንደሰራሁ ወዲያውኑ ዋሽንግተን ዲሲ ሄጄ ከተሾመ ምትኩ ጋር የመስራት እድሉ ገጠመኝ። በመቀጠልም የፕሮፌሰር አስራት ገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ላይ ተሳተፍኩኝ። በተመሳሳይ ለጋሽ ፀጋዬ በተዘጋጀ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃ ግብር ላይ ከነ አለምፀሃይ ወዳጆ እና ከነ ተመስገን አፈወርቅ ጋር መስራት ጀመርን። በኋላም የጣይቱ የባህል ማዕከል ተቋቋመ። ከ250 በላይ የሚሆኑ ቲያትሮችን በመላው አሜሪካ በመዘዋወር አቅርበናል። በቅርቡም «የቲዎድሮስ ራዕይ» የተሰኘው የጌትነት እንየው ቲያትርን ከጣይቱ ማዕከል ጋር እየተዘዋወርን እየሰራን ነበር። መላውን አሜሪካና አውሮፓ በአውሮፕላን፤ በመርከብ፤ በአውቶብስ እየተዘዋወርን አሳይተናል።

ላለፉት 19ኛ ዓመታት በዚህ ሙያ ሰርቻለሁ። አገራዊ ጥሪው ከመምጣቱ በፊት በታላቁ ህዳሴ ግድቡ ላይ ከፍተኛ የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ በዙምና በአካልም በመገኘት ሰርቻለሁ። ኮቪድ ሲከሰትም ለቲያትር ባለሙያዎች ገንዘብ አሰባስበን ልከናል። ከዚያ በኋላ ጦርነቱ መከሰቱን ተከትሎ የህዝቦች መፈናቀል እጅግ በጣም ስሜቴን ስለነካውና እድሉንም ስላገኘሁ ከአምባሳደር ፍፁም አረጋ እና ከአምባሳደር ታዬ አፅቀ ሥላሤ ጋር በመሆን ከ25 ስቴት ያላነሰ ሥራዬን ሙሉ ለሙሉ አቁሜ እየተጓዝኩኝ ገንዘብ የማሰባሰቡን ስራ በመስራት ላይ እገኛለሁ።

በሳምንት ሁለት ቀን በአውሮፕላን ከቦታ ቦታ እየተጓጓዝኩ ቅስቀሳ አደርጋለሁ፤ በዙም ውይይቶችን አደርጋለሁ። እስካሁን ወደ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር የማሰባሰብ እድሉ ገጥሞኛል። ህዝብ በማንቀሳቀስ ሰልፎችን በመምራት፤ ንግግሮችን በማድረግ የኪነ-ጥበብ ስራዎችን በመስራት የበኩሌን ሚና ለመጫወት ሞክሪያለሁ። በተለይም የሎሬት ፀጋዬን ስራዎችን በማቅረብ መላው ኢትዮጵያዊ ለአገሩና ለወገኑ እንዲደርስ ከፍተኛ ስራ ሰርቻለሁ። አሜሪካ የሚኖረው ደጉ ኢትዮጵያዊም እጅ ከምን ስለው አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ያለውን ሁሉ ሳይሰስት ነው የሚለግሰው። በተለይ ከገና በፊት በነበረው የገንዘብ ማሰባሰቢያ መድረኮች ዲያስፖራው በከፍተኛ ደረጃ ነበር ሲንቀሳቀስ የነበረው። ከአምባሳደር ፍፁም ጋር ጠዋት ለሶስት ሰዓታት ብዙ ገንዘብ ሰብስበን ከሰዓት ሌላ ከተማ በአውሮፕላን እንሄዳለን። አንድ ጊዜ እንዳውም ቨርጂኒያ የአስር ደቂቃ ልዩነት ባለው ቦታ ላይ በሁለት አዳራሽ ስብሰባ አካሂደን ከፍተኛ ገንዘብ አሰባስበናል፤ ጨረታም አጫርተን ድጋፍ አግኝተናል። እዚህ ከመምጣቴ በፊትም ካሊፎርኒያና ዲሲ ላይ ዝግጅቶች ነበሩ።

በአጠቃላይ በዚህ ደረጃ ቁርጠኛ ሆኜ እንድሰራ ያረገኝ አንድ የኪነ-ጥበብ ሰው ለአገርና ለወገኑ ያለው ከበሬታ ትልቅ በመሆኑ ነው። «የጥበብ ሰው ነኝ» ማለት ራስን አሳልፎ ለሌሎች መስጠት ማለት ነው። ይህንን ነገር ስለተረዳሁ ነው። አስቀድሜ እንዳልኩሽ እኛ ዘርፉን የተቀላቀልንበት ወቅት ጥሩ ዘመን ነበር። ዩኒቨርሲቲ ስንማር መንግስት አላስከፈለንም። ተመርቀን ስራ ከጀመርንም በኋላ የሚከፈለን ብዙ አልነበረም፤ ግን ብዙ የህዝብ ፍቅር ነበረን። ስለዚህ ብዙዎቻችን የዚህች አገር ውለታ ያለብን በመሆኑ «አገሬ ምን አደረገችልኝ» ሳይሆን «እኔ ለአገሬ ምን ላድርግላት ይገባል» ልንል ነው የሚገባን። በተለይ በእድሜ እየበሰልሽ ስትሄጂ ህሊናሽ የሚፈተነው በዚህ አይነቱ ጉዳይ ላይ ነው። ራስን ብቻ ለማሳደግ የሚደረግ ሩጫ የንፉጎች ኑሮ ነው። ከዚህ አልፎ ተርፎ ለአገርና ለወገን የሚጠቅም ስራ መስራት ያስፈልጋል። አሜሪካ የሚኖረው ዳያስፖራ ከገንዘብ ባለፈ በቁሳቁስም በጦርነቱ ለተጎዱ ወገኖች ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል። በቅርቡም ቆቦ ለሚገኙና ባሎቻቸው በጦርነቱ ለሞቱባቸው 140 ለሚሆኑ ሴቶች ትልቅ ትራክተርና ሁለት መካከለኛ ትራክተሮች ተጭነው ተልከዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ውጭ ከሄድክ በኋላ በአገሪቱ የነበረውን የፖለቲካ ችግር በሥራዎችህ ስትታገል ነበር። በተለይ «ጀምበር ጠልቆብሃል» የሚለው መነባነብህ በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ ውጥረት በገሃድ የሚያሳይ ነው። ከዚህ አንፃር ታደርገው የነበረው ትግል ምንያህል ውጤት አምጥቷል ብለህ ታምናለህ?**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** እንደአንድ ፖለቲከኛ ሳይሆን እንደአንድ የጥበብ ሰው የበኩሌን አስተዋፅኦ እንዳደረኩ ነው የሚሰማኝ። ልክ በፍቅርና በመሰል ጉዳዮች ላይ እንደምሰራው ሁሉ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ መስራት እንዳለብኝ አምናለሁ። ኢትዮጵያ ለእኔ ሁሉንም ነገሬ ናት። ኢትዮጵያ ለእኔ በምናብ አለም የምትታይ የሕዝቦች ስብስብ ናት። እጅግ በጣም ታላቅ የሆነች አገር ናት። በተለይ በጥልቀት ለመረመረና ታሪክን ላወቀና ለተገነዘበ ከማንም አገር የምትበልጥ እጅግ ትልቅ አገር ናት። አሁን ያለው ትውልድ የውጭ ጸሐፍያን ሳይቀሩ የፃፏቸውን መጽሐፍት ሲመለከቱ ኢትዮጵያዊ ለመሆን ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን ይገነዘባሉ ብዬ ነው የማስበው። አንድ ቀን ግን ወደነበርንበት የከፍታ ማማ እንደምንደርስ ተስፋ አለኝ። አገሬ ላይ የማኩረፍ ፍላጎት የለኝም፤ በቅርቡ እስረኞች ተፈቱ ተብሎ ብዙዎች ሲያኮርፉ እኔ አላኮረፍኩም። ምክንያቱም መንግስት የራሱ ድርሻ አለው። እሱ በሚመለከተው መንገድ ባንመለከትም ስራውን እንዲሰራ መተው አለብን።

አንቺ ያነሳሽው ጀምበር ጠልቆብሃል በሚለው ስራዬ የኮረኔል ደመቀን ጀግንነት ለማንሳት ነው የሞከርኩት። እሱ ያኔ የከፈለው መስዋዕትነት ከፍተኛ ነው። ለእኔ ይህ ሰው ጀግና ብቻ ሳይሆን ዳግማዊ ቲዎድሮስ ነበር። አሁንም ለመጣው ለውጥ በተለይ አማራ ክልል የነበረውን ብርቱ ተጋድሎ የመራው ይህ ሰው ነው። በዚያ ፕሮግራም እሱን ለማወደስ ነው በሰው አገር ባንዲራችንን እያውለበለብን የዘከርነው። እኔም የወታደር ልብስ ለብሼ መነባንቡን በማቅረብ ለእሱ ያለኝን ፍቅርና አክብሮት ለመግለፅ የሞከርኩት። አሁን እንደተከሰተው ችግር አይነት አጋጣሚው ሲገኝ ለአገሬና ለወገኔ ያለኝን ፍቅር በተግባር ለመግለፅ ነው የምሞክረው።

በቅርቡ እንዳውም ላስቬጋስ ላይ ገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም አዘጋጅተን ዝግጅቱ ሊጀመር ጥቂት ሰዓታት ሲቀረው የሆቴሉ ሰዎች ፕሮግራሙን ማካሄድ እንዳማንችል ነገሩን። ምክንያቱም ጁንታዎቹ ለአገሬው ሰዎች እኛ ገንዘብ የምንሰበስበው ለጦርነት እንደሆነ አሳምነዋቸው ይመስለኛል። ለእኛ ግን ምክንያቱ አልተነገረንም። ይህንን ሁኔታ ለመላው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ መልዕክቱ እንዲደርሰው ተደረገ። ያን ጊዜ ስራ ለመሄድ ያሰበው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በቁጭት ስራ ቀርቶ ወዲያውኑ ትልቅ መጋዘን ተከራይቶ፤ አፅድቶና አስውቦ እንዳውም ከታሰበው በላይ የሞቀና የደመቀ ፕሮግራም ነው ያካሄድነው። በግምት ከ1ሺ200 ሰዎች በላይ ነው የታደሙበት። በአንድ ቀን ገንዘብ ለመስጠት ሲባል ብቻ ያንን ያህል ሽሚያ ሲካሄድ አላየሁም። በእርግጥ ሎስአንጀለስ በአንድ ሌሊት ብቻ 640ሺ ብር ነው መሰብሰብ የቻልነው። ከኩርፊያውም በኋላም እንደመጀመሪያውም ባይሆን ዳያስፖራው ለአገሩ የተጠየቀውን ሁሉ እያደረገ ነው ያለው። አሁንም የሚቀበለኝ አጣሁ እንጂ በግምት 500ሺ ብር የሚያወጣ ሁለት ሻንጣ መድሃኒት ይዤ ነው የመጣሁት።

**አዲስ ዘመን፡- የአሜሪካ መንግስት ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ ለመጣል የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ለማስቆም ዳያስፖራው ምን እያከናወነ ነው?**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** እርግጥ ነው ኤች.አር 6600 እጅግ በጣም አደገኛ ሰነድ ነው። አንዳንድ በመንግስት ላይ ያኮረፉ ሰዎች ለጊዜውም ቢሆን ቢደግፉትም አሁን ላይ ግን አብዛኛው ዳያስፖራ እውነታው ስለተገነዘበ ማዕቀቡ እንዳይፀድቅ ብዙ ታግሏል። እየታገለም ይገኛል። እንደግፋለን የሚሉትም ቢሆን መንግስትን የሚጥል ስለመሰላቸው ነው እንጂ ከመንግስት በላይ ህዝብን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ መሆኑን ተገንዝበዋል። ኢትዮጵያ ለሚገኙ ወላጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ገንዘብ መላክ እና እዚያ እናት አባት ማስመጣት አይቻልም። ከዚህ ቀደምም ለግድቡ ገንዘብ እንዳይሰበሰብ ታግዶ በነበረበት ጊዜ ዳያስፖራው ቦንድ እንዳይገዛ ተደርጓል። አሁንም በተመሳሳይ ዳያስፖራው አገሩንና ወገኑን እንዳይደግፍ ነው የሚያደርገው። እንዳልኩሽ ማዕቀፉን ደግፈው አቋማቸውን ያሳዩ አንዳንድ ሰዎች ባለማወቅ ነው ይህንን ሲያደርጉ የነበሩት። የዚህን ሰነድ አደገኛነት ካስረዳናቸውና በአገር ሊኮረፍ እንደማይቻል ከተገነዘቡ በኋላ ብዙዎቹ አቋማቸውን ቀይረዋል።

በቅርቡ እኛ በምንኖርበት ከተማ ላይ የአሜሪካ መንግስት ሶስተኛ ሰውና አፈጉባኤ የሆነችው ናንሲ ፔሎሲ በመጣችበት ወቅት መረጃው አስቀድሞ ስለነበረን በቀጥታ ደብዳቤያችን እንዲደርሳት አድርገናል። ከዚህም ባሻገር ሬቬረንድ ብራውን የተባለው ጥቁር የማህበረሰብ አንቂን ይዘነው ነው የሄድነው። የሚገርምሽ ፓርኪንግ ስራ ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያኖች ሳይቀሩ መረጃ በመሰብሰብና በማቀበል ረገድ ከፍተኛ ሚና ነው እየተጫወቱ ያሉት። አሁን ላይ በተለይ የትግራይ ተወላጅ የሆነው የቺፍ ስታፉ መነሳት ብዙ ለውጥ ይመጣል ብዬ አስባለሁ። የቴዎድሮስ አድሃኖም ነገርም ወደ ውድቀት የሚሄድ በመሆኑ አሁን ለኢትዮጵያ ጥሩ በር የሚከፍት ይመስለኛል። ሁላችንም በርትተን ለአገራችን ዘብ መቆም አለብን። ምክንያቱም በአገር ኩርፊያ የለም። አሁን ላይ በእርግጥ አብዛኛው ዲያስፖራ እየነቃ ነው ያለው። አሁንም ስለአገራቸው የሚያለቅሱ የሚጮሁ አሉ። በየስራ ድርሻቸው ሆነው ለአገራቸው ዘብ የቆሙ የሚሞግቱ አንቂዎች አሉን። ወደፊትም እንቅስቃሴው እየተጠናከረ ሲመጣ ጫናውን ለማስቆም እንችላለን። በቅርቡ በሚካደው በአሜሪካ ምርጫ ዳያስፖራ ድምፁን ተጠቅሞ ኢትዮጵያ ላይ የሚደረገውን ጫና ለማስቆም እየሰራ ነው። ደግሞም ዲያስፖራዎቻችን የምርጫውን ውጤት የማስቀየር አቅም ስላላቸው የአሜሪካ መንግስት ላይ ጫና ለማሳደር ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥርልናል። ስለዚህ ያኮረፉትን ብቻ ሳይሆን የሚዋዥቁትንም ሳይቀር በማሳመን እንደቀድሞው ጫናውን እንዲታገሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አርቲስት ተስፋዬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# የመድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አምራቾችን ማነቆ ለመፍታት



አስናቀ ፀጋዬ

ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት 60 ከመቶ የሚሆነውን የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ፍላጎቷን በአገር ውስጥ አምራቾች ለማሟላት አቅዳ እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች። ሆኖም ከዚህ በተቃራኒ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ አሁንም ድረስ መድኃኒቶችንና የህክምና መሳሪያዎችን በአገር ውስጥ የሚያመርቱ ኩባንያዎች እያሉ አገሪቱ በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ምርቶቹን አገር ውስጥ ታስገባለች።

አምራቾች ደግሞ ‹‹አንዳንድ መድኃኒቶችንና የህክምና መሳሪያዎችን በአገር ውስጥ እያመረትን ቢሆንም መንግስት ትኩረት የሚሰጠው ለውጪው ገበያ ነው።›› ሲሉ ይደመጣሉ። ለአገር ውስጥ አምራቾች መንግስት የሰጠው ትኩረትም አነስተኛ ነው ሲሉ ይደመጣሉ።

አቶ ተሾመ በየነ የዘኒው ሚሊኒየም ሜዲካል ዎርልድ ሜዲካል ዲቫይስ ማኑፋክቸሪንግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ናቸው። ድርጅታቸው ካለፈው ሁለት አመት ወዲህ በቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ገብቶ የበሽታ መመርመሪያ ኪቶችን እያመረተ ይገኛል። በአሁኑ ግዜም አምስት አይነት የበሽታ መመርመሪያ ኪቶችን ያመርታል።

ድርጅቱ ምርቱን እንደጀመረ በመጀመሪያው የምርት ሂደት ውስጥ መጠነኛ መንገራገጭ አጋጥሞት ነበር። ሆኖም ግን ባለፈው 2013 ዓ.ም ላይ እንደሌሎቹ ከውጪ አገር የበሽታ መመርመሪያ ኪት አስመጪ ድርጅቶች ጨረታ ተወዳድሮና አሸንፎ ለኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት በግዜውና ባለው መጠን ማቅረቡን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ይናገራሉ። ይሁንና ድርጅቱ ጨረታውን ካሸነፈ በኋላ ጨረታው ከውጪ ለሚያስመጡ እንደተሰጠ ያስረዳሉ። ከዚህ አንፃር ገዢው አካል ቅድሚያ ሰጥቶ ከአገር ውስጥ አምራቾች ምርቶችን መግዛት እንዳለበት ያሳስባሉ። ይህም እንደግዴታ መቀመጥ እንዳለበት ይጠቁማሉ።

መንግስት የእርሳቸውን ድርጅት ጨምሮ ሌሎች የአገር ውስጥ መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አምራቾችን በተለያየ መንገድ በተግባር ማገዝ እንዳለበት ይጠይቃሉ። አምራቾች የፋይናንስና የቴክኖሎጂ አቅም ሲያነሳቸው መንግስት ተመሳሳይ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበትም ይገልፃሉ። የብድር አገልግሎት ሊመቻችና ሊተገበር እንደሚገባም ይጠቁማሉ። በፋርማሲቲዩካል ዘርፍ ያሉ ፖሊሲዎችም ወደ መሬት ወርደው ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸውም ይጠቅሳሉ።

የመድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ንጉሴ እንደሚሉት 60 ከመቶ የሚሆነውን የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ፍላጎት በአገር ውስጥ አምራቾች ለመሸፈን የአጭር ግዜ እቅድ ተይዟል። በቀጣይ አስር አመት ደግሞ ይህን ፍላጎት ወደ 80 ከመቶ ለማድረስ እቅድ ተቀምጧል። ይህ እቅድ ግን በተቋሙ ብቻ ሊሳካ አይችልም። እንዲያም ሆኖ ታዲያ መድኃኒት በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ተመርቶ ለዜጎች መቅረብ አለበት። ለዚህም ከውጪ የሚመጡና በአገር ውስጥ ያሉ ባለሃብቶችን ማገዝና ማበረታታት ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን የአገር ውስጥ አምራቾች በአገር ውስጥ ቢያመርቱም ጥሬ ዕቃዎችን የሚያስመጡት ከውጪ አገራት ነው። እነዚህን ጥሬ ዕቃዎችን ከውጪ አገር ለማስመጣት ደግሞ የውጪ ምንዛሬ ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ አንፃር የፋይናንስ ተቋም ድጋፍ አስፈላጊ ይሆናል። ከዚህ በፊት የነበረው የኢንቨስትመንት ፖሊሲም መድኃኒት ወደአገር ውስጥ እንዲገባ የሚያበረታታ እንጂ በአገር ውስጥ እንዲመረት የሚያስችል ባለመሆኑ ፖሊሲውን መቀየር ያስፈልጋል። ለዚህም የባለድርሻ አካላት በጋራ መሥራትን ይጠይቃል። በተለይ ደግሞ የቁጥጥርና የፋይናንስ አካላት ርብርብ ያስፈልጋል። አምራቾች ጥሬ ዕቃዎችን በውጪ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ሲፈልጉም መድኃኒትና የህክምና መሥሪያዎች ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ጉዳዩ የሚመለከተው አካል የውጪ ምንዛሬ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል የሚል እምነት አላቸው።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ እንደገዢ ተቋም አንድ መድኃኒት ከተፈለገ በአገር ውስጥ የሚያመርት ካለ ያመርታል፤ በአገር ውስጥ ካልተመረተ ግን ተቋሙ መድኃኒቱን ከውጪ አገራት ያስመጣል። በሌላ በኩል ደግሞ ተቋሙ የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ ይችላል። ለአብነትም፤ በግዢ የኢንሴንቲቭ ፓኬጅ አሰራር በመዘርጋት የሚወጣውን የውጪ ምንዛሬ በአገር ውስጥ ምርት ላይ እንዲውል ማድረግ።

በሁሉም ባለድርሻ አካላት በአገር ውስጥ አምራቾች የሚመረቱ መድኃኒቶችንና የህክምና መሳሪያዎችን ለማጠናከር በሁሉም ባለድርሻ አካላት በኩል ፍላጎቱ ያለ ቢሆንም በዚህ ልክ ወደ አንድ አምጥቶ በመሥራት ረገድ ክፍተቶች ታይተዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚገልፁትም፤ በተቋሙ በኩል ጨረታዎች በአብዛኛው የሚወጡት ለውጪ አገር አምራቾች ነው። ይህም የሆነው የሀገር ውስጥ አምራቾች በበቂ ሁኔታ ስለማያመርቱ ነው። በተቋሙ አሰራር መሰረት ለአገር ውስጥ መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አምራቾች ቅድሚያ ይሰጣል። በአሰራሩ መሰረትም ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር አምራቾች የሚወጡ ሁለት አይነት ጨረታዎች አሉ።

በሀገር ውስጥ ጨረታ የውጪዎቹ አምራቾች ስለማይወዳደሩ ቅድሚያ ለአገር ውስጥ አምራቾች ይሰጣል። ለአገር ውስጥ አምራቾች ዝቅተኛ የጨረታ መስፈርትም ዋጋና የማስረከቢያ ግዜ ሲሆን ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ አምራች አሸናፊ ይሆናል። በሁለተኛው የዓለም አቀፍ ጨረታ፤ የአገር ውስጥ አምራቾችም የሚሳተፉ ሲሆን እስከ 25 ከመቶ ዋጋቸውን ከፍ ቢያደርጉ የሚያሸንፉበት እድል ይኖራል። ጨረታውን ሲያሸንፉ 30 ከመቶ ቅድሚያ ክፍያ እንዲፈፅሙም የግዥ መመሪያው ይፈቅድላቸዋል።

የጤና ሚንስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ የመድሃኒት አቅርቦትን በአገር ውስጥ ለማሻሻልና ለአምራች ኢንዱስትሪውም አንዱና እንደአገር ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ብሎም እየተሰራበት ያለው የአገር ውስጥ የመድኃኒትና የመድኃኒት መገልገያዎችን ምርት የማሳደግ ሥራ ነው። በአሁኑ ግዜም ከሚፈለጉት የመድኃኒት ምርቶችና የመድኃኒት ግብዓቶች መካከል በአገር ውስጥ የሚመረቱት ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ በመሆኑ በአብዛኛው ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው ከውጪ ይገባል።

በአገር ውስጥ አምራቾች የሚመረቱ መድኃኒቶችንና የህክምና መሳሪያዎችን ለማሳደግና ትልቅ ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማድረግ አገራዊ ስትራቴጂ ተቀርፆ ወደ ሥራ ከተገባ አምስት አመት ተሻግሯል። ይሁንና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በተፈለገው ዕቅድ መሰረት የአምራቾችን ቁጥር መጨመርና በአገር ውስጥ ያሉት አምራቾች ደግሞ በሙሉ አቅማቸው አምርተው ወደ ገበያ እንዲያስገቡ ማድረግ እስካሁን ድረስ አልተቻለም።

**ለመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ግብዓት አብዛኛው ጥሬ ዕቃ ከውጪ አገር የሚመጣ በመሆኑና ጥሬ ዕቃዎቹን ለማምጣት ያለው የውጪ ምንዛሬ እጥረትም የአገር ውስጥ አምራቾች በሙሉ አቅማቸው እንዳያመርቱ እና በሚሰጣቸው ኮንትራት መሰረት እንዳያቀርቡ እንቅፋት ፈጥሮባቸዋል**

እነዚህም በሀገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ያሉ በተለይ ደግሞ ባለፉት ሁለት አመታት የነበረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ጨምሮ የተለያዩ ችግሮች የአገር ውስጥ አምራቾችን ቁጥር በመጨመርና አምርተው ወደገበያ እንዲወጡ አቅማቸውን መገንባት ላይ ብዙ መሥራት አልተቻለም። ይሁንና ይህን ማድረግ እንደአገር ትልቅ ገበያ ያለ በመሆኑና የሕዝብ ቁጥሩም ከፍተኛ በመሆኑ በአገር ውስጥ ላለው የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አምራቾች ትልቅ እድል ነው። ለቀጠናውም ጭምር ትልቅ ገበያ የሚፈጥርና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽዖም ያለው በመሆኑ ይህን አቅም ማጠናከር ያስፈልጋል።

ይህን አቅም ከማጠናከር አንፃር እስካሁን በተለያዩ ዘርፎች እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች አሉ። መንግስት ያስቀመጣቸው ማበረታቻዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥም ከግብር ጀምሮ ለተወሰኑ አመታት አምራቾች በሚቀጥሩት ሰው፣ በሚያመርቱት ግብዓትና በሚያስገቡት ጥሬ ዕቃ ላይ የተለያዩ የግብር ማበረታቻዎችን መንግስት አድርጓል። ከግብር ነፃ የማድረግ ማበረታቻዎችም አሉ።

ከዚህ ባለፈ በአገር ውስጥ የሚያመርቱ ወይም ምርትን የሚያቀርቡ በአገር ውስጥ በሚደረጉ ጨረታዎች ላይ ከሌሎች ከውጪ አገር ከሚያስመጡ አስመጪዎች ጋር ሲወዳደሩ እስከ 25 በመቶ የጨረታ ዋጋ ከፍም ቢል ለእነርሱ ቅድሚያ የሚሰጥበት ሁኔታ ተቀምጧል፤ በዛ መሰረትም ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

ይሁንና ባሉት ተግዳሮቶች ምክንያት፤ በተለይ ደግሞ የአገር ውስጥ አምራቾች ቁጥራቸው አነስተኛም ቢሆንም ከዚህ ቀደም ሲያቀርቡት ከነበረው ምርታቸው የቀነሰበት ሁኔታ ታይቷል። ለመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ግብዓት አብዛኛው ጥሬ ዕቃ ከውጪ አገር የሚመጣ በመሆኑና ጥሬ ዕቃዎቹን ለማምጣት ያለው የውጪ ምንዛሬ እጥረትም የአገር ውስጥ አምራቾች በሙሉ አቅማቸው እንዳያመርቱና በሚሰጣቸው ኮንትራት መሰረት እንዳያቀርቡ እንቅፋት ፈጥሮባቸዋል።

እነዚህን ችግሮች ከመፍታት አኳያ አንዳንድ የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውን ሚንስትሯ ይናገራሉ። ውስን የውጪ ምንዛሬ ቢኖርም ባለው ሀብት የአገር ውስጥ አምራቾች ቅድሚያ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራም እየተሰራ ሲሆን በቅርቡ የገንዘብ ሚንስቴር ይህን መሻሻያ አውጥቶ እየተገበረ ይገኛል። እነዚህንና ሌሎች ሥራዎችን በመሥራት፣ የቁጥጥር ስርዓቱን በመገንባት፣ የአቅርቦት ስርዓቱን በማሻሻል እንዲሁም ጥሬ ዕቃው በራሱ በአገር ውስጥ የሚመረትበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በመንግስት በኩል ሰፊ ቁርጠኝነት አለ።

ከዚህ አኳያ የፋርማሲዩቲካል ዘርፉን በአደረጃጀት ደረጃ ከዚህ በፊት ሲደግፍ የነበረው በኢንዱስትሪ ሚንስቴር ሥር ያለው የምግብ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ነበር። በኢንስቲትዩቱ ስር የነበሩ ሥራዎች በዘርፍ ቢደገፉ የተሻለ መሆኑን በማመንም በጤና ሚንስቴር ስር ባለው የአርሞር ሀንሰን ምርምር ኢንቲትዩት የኢንዱስትሪው ልማትና ምርምሩ ተቀናጅቶ እንዲደገፍ ለማድረግ ተወስኗል።

በዚህ አደረጃጀት ደግሞ ጤና ሚንስቴር የጀመረውን ሥራ ከምርምር ኢንስቲትዩቱ ጋር በማቀናጀት ከሚመለከታቸው ሴክተሮች ጋር በተለይ ደግሞ ከኢንዱስትሪ ሚንስቴር፣ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከገንዘብ ሚንስቴር፣ ከብሄራዊ ባንክ፣ ከአገር ውስጥ የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አምራች ማህበራትና መሰል ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል።

በዚሁ ዘርፍ ውስጥ ደግሞ የመድኃኒት አቅርቦት አገልግሎትና የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ያላቸውን አስተዋጽዖ በዚህ ውስጥ ለማጠናከርም ጤና ሚንስቴር በጋራ እየሰራ ነው። ይህን የሚያጠናክሩ ግብረሃይሎችም ተቋቁመው የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። አምራቾችንም ሆነ የአገር ውስጥ አቅምን ለማጠናከርም ከአለም ባንክ፣ አለም ጤና ድርጅትና ከተለያዩ አጋር ድርጅቶችም ጋር ይህንኑ ለማጠናከር ከፍተኛ ሥራዎች እየተሰሩ ነው።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የጠብ ሱሰኞች - "የሃሳብ መስመር!?"

**ለእውቀትም ለመንደርደሪያም፤**

ዩጋንዳዊያን አገራቸውን የሚጠሩት "የአፍሪካ ዕንቁ - Perl of Africa" እያሉ ነው። በዕንቁ የተመሰለችውን ይህቺን አገር ይህ ጸሐፊ ለመጎብኘት ዕድሉ ገጥሞት ነበር። የሌሎች የአፍሪካ አገራት የጋራ ችግሮች የዚህች አገርም ችግሮች መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በርግጥም "ዕንቁ" ሊያሰኟት የሚችሉ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች እንዳሏት ግን አፍ ሞልቶ መመስከር ይቻላል።

የአገሬ ስደተኞችም ሆኑ በሕጋዊ መንገድ ምድሯን የረገጡ ወገኖቻችን ተደላድለውና እፎይ ብለው የሚኖሩባት የቀጣናችን እህት አገር መሆኗን ያለመግለጽ ንፉግነት ነው። አንዳንድ በዚያች አገር የሚኖሩና ኑሮው የተሳካላቸው የአገሬ ልጆች "እምዬ" የሚለውን የባህላችንን የፍቅር መግለጫ ቃል ተውሰው ብቻ ሳይሆን ስለሚገባት ጭምር ዕንቁዬዋን ዩጋንዳ የሚጠሯት "እምዬ ዩጋንዳ" እያሉ መሆኑን በዚያች ለምለም አገር ከምትኖረው የቀድሞ ተማሪዬ አንደበት ሰምቼያለሁ። ተጨማሪውን አክለውበት፣ የጎደለውን ሞልተውበት በዚያች ለምለም ምድር እየኖሩ ሕይወትን በማጣጣም ላይ ያሉ ዜጎቻችን የልባቸውን ደስታ ቢመሰክሩ የተሻለ ብቻ ሳይሆን የጸሐፊውን የወፍ በረር ዕውቀት ለማጠናከር ስለሚበጅ ጭምር ድምጻቸውን ቢያሰሙ መልካም ይሆናል።

ዩጋንዳን ለጽሑፌ መንደርደሪያነት የጠቀስኩት በአገሪቱን ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ ገለጻ ለመስጠት ሳይሆን ተፈጥሮ በምድሯ ውስጥ የምትፈጽመውን አንድ አስደናቂ ክስተት ለማስታወስ በመፈለግ ነው። ከካምፓላ ከተማ 72 ኪሎ ሜትሮች ያህል ርቃ በምትገኘውና ኬያብዌ (Kayabwe) በመባል በምትታወቀው አነስተኛ ከተማ ውስጥ Uganda Equator በመባል የሚታወቅና ምሥጢሩ በተመራማሪዎች ዘንድ በምልዓት ያልተፈታ አንድ ታላቅ የምድራችን የተፈጥሮ የሃሳብ መስመር ከተማዋን አቋርጦ ያልፋል። ይህ የኢኩዌተር መስመር ከዩጋንዳ ሌላ በርካታ የላቲን አገራትንና ሁለቱን ኮንጎዎች፣ ጋቦንን፣ ኬኒያንና ሱማሊያን የመሳሰሉ አገራትንም እያቆራረጠ እንደሚያልፍ ልብ ይሏል።

ኢኩዌተር እያልን የምንጠራው ይህ የሃሳብ መስመር የምድር ሰቅ (ቀበቶ) ተብሎ እንደሚጠራ የተማርነው ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ስለመሆኑ ማስታወሱም አግባብ ይሆናል። በአጭሩ ለመከለስ ያህል ኢኩዌተር (የምድር ሰቅ) የሚባለው የሃሳብ መስመር የዓለማችንን የሰሜኑንና የደቡቡን ንፍቀ ክበባት እኩል ለእኩል ለሁለት እየገመሰ በዜሮ ዲግሪ ላቲቲዩድ ላይ የሚያልፍ መስመር ነው። አንድን ብርቱካን እኩል ለእኩል ወገቡ ላይ ከመክፈል ጋር ማስተያየት ይቻላል።

በ40 ሺህ 075 ኪሎ ሜትሮች በምድር ወገብ ላይ የተጠመጠመው ይህ የሃሳብ መስመር በዐይን የማይታይ፣ በእጅ የማይዳሰስና የማይጨበጥ ሲሆን የሚገለጸው በልዩ ተዓምራዊና ትንግርታዊ ባህርይው ነው። አንዳንድ ክስተቶችን እናስታውስ፡ - በዚያ መስመር አካባቢ ፀሐይ የምትወጣውና የምትጠልቀው በተለመደው ዝግመታዊ ጉዞዋ ሳይሆን ክስተቱ የሚፈጸመው ፈጠን ብሎ ነው።

ሃምሳ ሴንቲ ሜትር ያህል እግራችንን አንፈራጠን በዚህ የሃሳብ መስመር ላይ ብንቆም በተፈጥሯዊ የምድር ስበት ምክንያት ከክብደታችን ላይ የተወሰነ ኪሎ እንቀንሳለን። እዚያው እግራችንን አንፈራጠን በቆምንበት ቦታ የውሃ መያዣያ ገበቴ ወይንም የእጅ ማስታጠቢያ ውሃ ይዘን ብንቆምና አንድ ሌላ ሰው ውሃ በጆግ እያንቆረቆረ ወደ ሰሜኑ ንፍቀ ክበብ ብንዞር ውሃው የሚሽከረከረው ልክ በእጅ ሰዓታችን የዞረት አቅጣጫ መሰረት ከግራ ወደ ቀኝ Clockwise አካሄድን ተከትሎ ነው። ገበቴውን ወደ ደቡብ አዙረን ውሃ ብናንቆረቁር ደግሞ በተቃራኒው ውሃው ከቀኝ ወደ ግራ Anticlockwise ሊሽከረከር ይችላል።

ከዚህ እውነታ እንደምንረዳው የዩጋንዳው ኢኩዌተር ሃምሳ ሳንቲ ሜትር በማይሞላ የንፍቀ ክበባቱ አካፋይ ድንበር ላይ ተፈጥሮ እንደምን በተዓምራት አድራጊነቷ እንደምትራቀቅ ጥሩ ማሳያ ነው። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ የሃሳብ መስመሩ ለሰዎች የስሜት መለዋወጥ ምክንያት እንደሚሆንም ግምት አላቸው። የዩጋንዳው ኢኩዌተር ይህንን ያህል ካጨዋወተን ዘንዳ ወደ መነሻ ጉዳያችን እንመለስና በአገራችን ጉዳይ እንደተለመደው ቁዘማችንን እንቀጥል።

**የጠብ ሱሰኛ የዶሮ ሻኛ አቅርቡልኝ ይሳል፤**

የግለሰቦችም ሆነ የቡድኖች አንዳንድ የጠብ መቆስቆሻ ምክንያቶች ከዩጋንዳ የሃሳብ መስመር ባህርይ ጋር በሱስም ቢሆን ይመሳሰላል። የሃሳባቸውና የዓላማቸው ስርና መሠረት በግልጥ አይታወቅም፣ ምክንያታቸውም በሚገባ አይጨበጥም። ተግባራቸው ሁልጊዜ ሰላምን በማናጋት የከፋፋይነት ተግባር መፈጸም ነው። አንዳንዴ የሚያነሱት ሃሳብ ልክ እንደ Clochwise አቅጣጫ የያዘ ቢመስልም ወዲያው አላዋጣ ሲላቸው ጊዜ ሳይሰጡ ዞር ብለው ተቃራኒ ሃሳብ በመምዘዝ የAnticlockwise አቅጣጫ ሲመርጡ ይስተዋላል። በኢኩዌተር የሃሳብ መስመር ላይ ስንቆም ተፈጥራዊ ክብደታችን እንደሚቀንሰው ሁሉ በጠብ ሱሰኞች ንፍቀ ክበብ ውስጥ መገኘትም እንዲሁ በራሱ የሰብእናን ክብደት ያሳንሳል። የባህርያቸው ተገለባባጭነትም ያስገምታል።

የኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች እንደ ሰሜኑና ደቡባዊ ንፍቀ ክበባት ፋታ ነስተውን ወዲህ ስንል Clockwise አቅጣጫ የተከተለ ሲመስለን፤ ወዲያው ፋታ ሳይሰጠን ነገሮች ሁሉ Anticlockwise እየተጠማዘዙ የሚያተረማምሱን ትንፋሽ እየነሱ በማጣደፍ ነው። ዋነኛው ምክንያት ደግሞ በጠብ ሱሰኞች የሚቀነባበር የረቀቀ ሴራ እንደሆነ እያረጋገጥን ነው። እነዚህን መሰል በጠብ አራራ የናወዙ የአገርና የሕዝብ ጠንቆች ሌትና ቀን ሲቃዡ ውለው የሚያድሩት ሰላም እንዲደፈርስና መከራችን እንዲያስገብረን ነው። ሲያሻቸው የሃይማኖት ካባ ደርበው በሕዝብ መካከል ሰይጣናዊ ተግባር ይፈጽማሉ። ይህን መሰሉ እቅዳቸው ሲከሽፍባቸው ደግሞ በፖለቲካ በርኖስ ተጀቡነው የጨለማ ትጋታቸውን በመቀጠል አገር እንዳትረጋጋ ይፍጨረጨራሉ።

ሱስ ያቅበዘብዛል፤ እረፍትም አይሰጥም። አራራው እስካልሰከነና ማፋሸኩ እስካልተገታ ድረስ የሱሰኞቹ ውሎ አዳር በመቅበዝበዝ የተሞላ እንደሚሆን የዘወትር ገጠመኞችን ነው። የሲጋራ፣ የቡና፣ የመጠጥ ወይንም የዕፅ ሱሰኞች እውነታውን እንዲያረጋግጡልን ለምስክርነት ብንጠራ "የሱስን አቅበዝባዥ" ውጤት ምን እንደሚመስል ሊያብራሩልን ይችላሉ።

"ጠብ ያለሽ በዳቦ" እያሉ በሕዝብ መካከል የሚቅበዘበዙ "የደም ሱሰኞች" ባህርይ ግን፤ ምንም እንኳን ማወዳደሩ ተገቢነት ባይኖረውም፤ ከላይኞቹ ሱሶች መቶ እጥፍ የከፋና የከረፋ እንደሆነ ውጤቱ ምስክር ነው። ቆሌያቸው የንጹሐንን ደም ካላሸተተ በስተቀር አይሰክኑም፤ አይረጋጉም። ግጭትና ማተረማመስ፣ ማፈናቀልና ማሳደድ፣ ውድመትና ፍጅት የጠብ ሱሰኞቹ የተገለጡ የሱስ ማርኪያ ተግባራት ናቸው።

እነዚህ የጠብ ሱሰኞች ፀረ ሰላም መሆናቸው ብቻም ሳይሆን የፀረ ሰብዓዊ ክብር ጌቶችም ጭምር ናቸው። የረከሰው ሰብእናቸው ሁሌም የሚናፍቀው የሕዝብ ዕልልታን ሳይሆን የአገር ልቅሶና ዋይታን ነው። "በቀኝ አውለኝ" የሚለው የሰርክ ተለምዷዊ የማለዳ ጸሎት በእነርሱ አፍ አይዞርም፤ የተለመደም አይደለም። የሚመቻቸውና የሚኖሩለት የሕይወት ፍልስፍናቸው ጤና ነስቶ ጤና የሚያሳጣ "ግራ አዋዋል" ነው።

ለጠበኛ ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች ፀሐይ ደምቃ መውጣቷ ያበሳጫቸዋል። የጨረቃ ድምቀትም ያስከፋቸዋል። የአገር ስኬት እንደ ቅንቅን ይኮሰኩሳቸዋል። የሕዝብ እረፍት ጤና ይነሳቸዋል። ስለዚህም ኑሮ ብለው "የሚሞቱለት የነፍሳቸው ጥሪ" ማፍረስና መናድ፣ መቃወምና ማጥላላት ብቻ ነው። ሰሜን ንፍቀ ክበብ ሲሏቸው ደቡብ፣ ደቡብ ሲሏቸው ምሥራቅ፣ ምሥራቅ ሲሏቸው ምዕራብ እያሉ መቅበዝበዝ ልማዳቸው ነው።

ለጠብ ሱስ መገለጫነት ከሚጠቀሱት መካከል አሸባሪው ሕወሓትና መጋለቢያ ጌኛዎቹ ተቀዳሚዎች ናቸው። ለምን የሰሜን ዕዝን ተዳፈሩ? በምን ምክንያትስ በአገሪቱ ላይ ጦርነት ለማወጅ ተደፋፈሩ? ለምንስ የሰላማችንን ርግብ አቆሰሉ? እኮ ለምን የትግራይን ሕዝብ በጋሻነት መመከቻ አድርገው በርሃብና በችግር እንዲቀጣ ፈረዱበት? መንግሥት ስለ ሰላም ሲናገር ለምን ሽብርን የሙጥኝ አሉ? ሲያሻቸው እንደ Clockwise አቋማቸውን ከግራ ወደ ቀኝ ይቀይራሉ፣ ሲፈልጉ በAnticlockwise አቋማቸው እየተሽከረከሩ የዓለም ማኅበረሰብን ግራ ያጋባሉ።

በዚህ አቋማቸው ምን ያህል ኀሊናቸው "በጥቁር ትዕቢት" እንደተሸፈነ ማረጋገጥ አይከብድም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በውስጣቸው ያረገዙት የጸብ ሽል "ግፋ በለው!" እያለ ስለሚያስገዝፋቸው ነው። አገር በማሸበር ላይ ያሉ መልከ ብዙ ቡድኖችም ቢሆኑ "ሰላምን ሸጠው" ጠብ ለመሸመት በጌቶቻቸው አማካይነት ስምሪት ስለሚሰጣቸው ከነፍሳቸው ጋር እየመከሩ በራሳቸው የሚወስኑት ምንም ዓይነት አቋም አይኖራቸውም።

የጠብ ሱሰኞችን በሌሊት ወፍ መመሰልም ይቻላል። የሌሊት ወፎች በበራሪዎች ዝርያ ውስጥ ይመደቡ እንጂ በሌላ ባህርያቸውም ከእንስሳት ወገን የሚመደቡ አጥቢዎችም ጭምር ናቸው። የሌሊት ወፎች ደምና ጥምብ ሥጋ እንደ ነፍሳቸው የሚወዱት ምግባቸው ነው። በሰዎች አእምሮ ውስጥ ከቫምፓየሮች ጋር የተቆራኙትም ስለዚሁ ነው። የሌሊት ወፎች አፈጣጠር እጅግ የተወሳሰበ ነው። አብዛኛው መኖሪያቸውም ምድረበዳና በዋሻ ውስጥ ነው። ብርሃን ለሌሊት ወፎች ፀር ስለሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርጉት በድቅድቅ ጨለማ ነው። ስለ እነዚህ ግራ አጋቢ እንስሳት ብዙ ማለት ይቻላል።

የጠብ ሱሰኞች ሁሌም ቆሌያቸው የሚያፋሽከው ለሕዝብ እልቂትና ለአገር ማፍረስ ሴራ ነው። ባህሪያቸው፣ አኗኗራቸውና ሕይወታቸው ልክ እንደ ሌሊት ወፍ ግራ የተጋባ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በማኅበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጩትን ጽሑፎች፣ ምስሎችና ድምጾች ልብ ብሎ በማጤን ብቻ ባህርያቸውን በሚገባ ማየት ይቻላል። ገድለው ወይንም አስገድለው ራሳቸው ድራማ ሲሰሩ አያፍሩም፤ አይጸጸቱም።

ከዚህ በላይ ምን ማለት ይቻላል። ሕዝብ ለማባላት ሴራቸውን እየሸመኑ ያሉት በእኛው መካከል ተቀምጠው ነው። አገር ለማፈራረስ ወጥመድ የሚዘረጉትም እኛው መሃል ሆነው የክፋት እንክርዳድ በመዝራት ነው። አገሬ ሆይ! ያጥናሽ ብለን አንደመድምም። ምክራችን፡- "መንግሥታችን ሆይ! ጥያቄ አለን? በማሳ ላይ ከበቀለው አዝመራ ውስጥ ተመሳስሎ የሚበቅለውን አረም ለመለየትና ለማስወገድ እጅግም አይቸግርም። እንደነዚህ ዓይነቶቹን የጠብ ሱሰኞች የምትለይበትና ለፍትሕ የምታቀርብበት ሥርዓት የላላ አይመስልህም? ዛሬም የጽሑፋችን ማሳረጊያ "ልብ ያለው ልብ ይበል" የሚለው ይሆናል። ሰላም ይሁን!

# ተናጋሪው ዶሴ

# ወደ ሰበር ያመራው የፍትሐብሄር ጉዳይ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር



እንደ መግቢያ

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቅፅ 15 ላይ ካሳለፋቸው ውሳኔዎች በዛሬው ዕትማችን አንዱን ይዘን ቀርበናል። የሰነድ መለያ ቁጥር 79189 መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ለበርካታ ጊዜ ክርክር ሲደረግበት የነበረው ጉዳይ የመጨረሻውን እልባት ለማግኘት ተቃርቧል። ዳኞች የመጨረሻ ውሳኔ ከማሳለፋቸው በፊት ሁሉን ነገር በአንክሮ ተመልክተዋል።**

ባለጉዳዮች

**አመልካች፡-** የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ባለስልጣን - ነገረ ፈጅ ወይዘሮ ሕይወት ደምሰው የቀረቡ ሲሆን፤ ተጠሪዎች፡- ጂ.ኤም.ቲ ኢንዱስትሪያል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ገብሩ በችሎቱ ፊት ቀርበዋል። ዳኞችም ለረጅም ጊዜ ሲመረምሩ በነበረው ጉዳይ ፍርድ ተሰጥቷል።

**የክርክሩ ሂደትና ፍርድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር በተጀመረበት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ እና አመልካች እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን፤ 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የነበሩት ደግሞ የሰበር ክርክሩ አካል ያልሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የማረሻ፣ የወገልና የቢላዋ ስ/አ/ህብረት ስራ ማህበር ናቸው። በ06/07/02 ተሻሽሎ የቀረበው ክስ ይዘትም ከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ስር ከሚገኘው የፍትህ አስተዳደር መምሪያ የ3ኛ ተከሳሽ ንብረት የነበረ ድርጅት በጨረታ ገዝቶ መረከቡን፣ ይሁን እንጂ ከ3ኛ ተከሳሽ የሚፈለግ የካፒታል ዕድገት ግብር ካለ እንዲገለፅ ከአንደኛ ተከሳሽ ለተፃፈለት ደብዳቤ ሁለተኛ ተከሳሽ በወቅቱ ምላሽ አልሰጠም።

1ኛ ተከሳሽም የ2ኛ ተከሳሽን መልስ ሳይጠብቅ እና ግብሩን ሳይቀንስ ተራፊውን ገንዘብ በሙሉ ለ3ኛ ተከሳሽ በመመለሱ እና የ3ኛ ተከሳሽ ካርታ ሳይቀርብ ከሳሽ በንብረቱ እንዲበደር ለባንክ ማረጋገጫ በመስጠቱ 3ኛ ተከሳሽ ከግብር ነፃ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃና ካርታ ሳያቀርብ ሙሉ ገንዘብ በመቀበሉ በአጠቃላይ ተከሳሾቹ በአንድነትና በመመሳጠር በፈጸሙት ተግባር ከሳሽ ስሙን አዛውሮ በንብረቱ ለመጠቀምና ብድሩን ለመክፈል አለመቻሉን የሚገልጽ ሆኖ በከሳሽ ላይ የታሰበውን የብድር ወለድ ብር 1ሚሊዮን785ሺ539ብር ከ20 ሳንቲም ተከሳሾቹ ለከሳሽ እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ክስ የቀረበበትን የወለድ ገንዘብ ለመክፈል ተከሳሾቹ የሕግም ሆነ የውል ግዴታ የለባቸውም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቷል ይላል ከችሎቱ የተገኘው መረጃ።

**ወደ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍርድ ባለመብት አሰፋ አርጋው እና የፍ/ባለዕዳ በነበረው 3ኛ መልስ ሰጪ መካከል በነበረው አፈፃፀም ይግባኝ ባይ የ3ኛ መልስ ሰጪ ንብረት የነበረውን ድርጅት በ22/03/99 ዓ/ም በብር 6,700,000 በጨረታ ገዝቶ ገንዘቡን አጠቃሎ ገቢ በማድረግ ድርጅቱን እንደተረከበ ድርጅቱን ለመግዛት ይ/ባይ ከወጋገን ባንክ ጎፋ ቅርንጫፍ ብር 4,265,100 ሲበደር የስም ዝውውሩ ወደ ይግባኝ ባይፈፀም ካርታውን በቀጥታ ለባንኩ እንዲልክ ለ2ኛ መልስ ሰጪ በደብዳቤ የሚያሳውቅ መሆኑን በመግለፅ የፍትህ አስተዳደር መምሪያ ለባንኩ ማረጋገጫ እንደሰጠ፣ ከ3ኛ ተከሳሽ የሚፈለግ የካፒታል ዕድገት ግብር እንዲገለጽለት 1ኛ መልስ ሰጪ ለ2ኛ መልስ ሰጪ ደብዳቤ የፃፈው በ09/09/99 ዓ.ም ሆኖ 2ኛ መልስ ሰጪ ብር 803,997.33 የካፒታል ዕድገት ተቀንሶ እንዲሰጠው በመጠየቅ ምላሽ የሰጠው ከዘጠኝ ወራት በኋላ በ06/06/2000 ዓ.ም እንደሆነ፣ በዚህ ጊዜ መሀል 3ኛ መ/ሰጪ የተራፊውን ገንዘብ በሙሉ እንደወሰደ፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37 መሰረት የካፒታል ዕድገት ግብር የመክፈል ግዴታ የሻጭ በመሆኑ ግብሩ እንደሚፈለግብኝ አላውቅም ነበር በማለት 3ኛ መልስ ሰጪ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም የሚል ተከራክረዋል።

1ኛ. መልስ ሰጪ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አይገባውም ወይም ግብሩ ሊኖር እንደሚችል መገመት የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም ባይባልም ግድፈቱ ሚዛን የሚደፋ እንዳልሆነ በፍርድ ቤቶች የሚፈፀም ስህተት በይግባኝ ከሚታረም በስተቀር ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው የሚባል ከሆነ በሀገሪቱ ምስቅልቅል የሚፈጠር እንደሆነ፣ 2ኛ. ከዘጠኝ ወር በኋላ ግብሩ ገቢ እንዲደረግለት ጠይቆ ገንዘቡ ለ3ኛ መልስ ሰጪ መለቀቁ ሊገለጽለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ደብዳቤ መፃፉ የራሱን ስህተት ግምት ውስጥ እንዳያስገባ ስህተቱን ሌሎች መልስ ሰጪዎች እንደፈፀሙት በማድረግ መሯሯጡ ተገቢነት አልነበረውም።

ይህንን በዝርዝር ከገለፀ በኋላ ይግባኝ ባይ ድርጅቱን የተረከበው በመሆኑ መ/ሰጪዎች የባንክ ብድር ወለድ ይክፈሉኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው ይሁን እንጂ ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ይግባኝ ባይ ግዴታውን ሙሉ በሙሉ ተወጥቶ እያለ ስሙ እስካሁን ያልተዛወረለት በመሆኑ 2ኛ መልስ ሰጪ የድርጅቱን ባለቤት ስም ወደ ይግባኝ ባይ ያዘውር የካፒታል ዕድገት ግብሩን ብር 803ሺ.997 ብር ከ33 ገንዘቡን ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር 3ኛ መልስ ሰጪ ለ2ኛ መልስ ሰጪ ገቢ ያደርግ 2ኛ መልስ ሰጪም ተከታትሎ ገቢ ያስደርግ ይግባኝ ባይ ለዳኝነት የከፈለውን ገንዘብ 2ኛ እና 3ኛ መልስ ሰጪዎች በታሪፉ መሰረት ግማሽ ይከፈሉት፣ ቀሪውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የጠቅላይ ፍር ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን፤ በ24/08/04 ዓ.ም አዘጋጅቶ ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በጨረታ አሸንፎ የተረከበውን ድርጅት በአመልካችና በሌሎች የስር ተከሳሾች ጥፋት ወደስሙ ማዛወር ባለመቻሉ ከባንክ ለወሰደው ብድር ለብር 1,785,539.20 የወለድ ክፍያ የተዳረገ በመሆኑ ወለዱ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ሆኖ አመልካች ስም እንዲያዛውር የካፒታል ዕድገት ግብር ከነወለዱ ከስር 3ኛ መልስ ሰጪ ተከታትሎ ገቢ እንዲያደርግ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከክሱ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ተመርምሯል። በዚህም መሰረት ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ06/07/02 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አሻሽሎ ባቀረበው ክስም ሆነ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ የጠየቀው ዳኝነት የወለድ ክፍያ መሆኑን እና በይግባኝ ሰሚውፍርድ ቤት የተሰጠው ዳኝነት ደግሞ የስም ዝውውር እንዲፈፀም መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል።

ይሁን እንጂ ተጠሪ በከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ዳኝነት ለጠየቀበት የወለድ ክፍያ ዋንኛ መንስኤ የሆነው በስር ተከሳሾች (መልስ ሰጪዎች) ድርጊት ሳቢያ የስም ዝውውሩ ሊፈፀም አለመቻል መሆኑን በግልጽ ሲከራከርበት የነበረ በመሆኑ የድርጅቱ የስም ዝውውር ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ከጠየቁበት ጉዳይ ውጪ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም። በሌላ በኩል ግን የስም ዝውውሩን እና የካፒታል እድገት ግብሩን ክፍያ መፈፀም ቅደም ተከተል አስመልክቶ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑ መጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህም መሰረት ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ ማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው ሰው ግብሩ መከፈሉን ሳያረጋግጥ ዝውውሩን እንደማይቀበል እንደማይመዘግብ እና እንደማያፀድቅ በአዋጅ በአንቀጽ 37(7) ስር በግልጽና በአስገዳጅነት ተደንግጎ ይገኛል። የዚህ ዓይነቱ ግልጽ የሕግ ክልከላ ባለበት ሁኔታ ደግሞ የስም ዝውውሩ ከግብር ክፍያው አስቀድሞ ሊፈጸም የሚችልበት አግባብ ስለማይኖር በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው የአፈፃፀም ቅደም ተከተል ከአዋጁ ድንጋጌ አንፃር መስተካከል የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል።

አመልካች ከስር 3ኛ መልስ ሰጪ የካፒታል እድገት ግብሩን ተከትሎ ገቢ እስኪያስደርግ ድረስ የስም ዝውውሩ መዘግየት ጉዳት ያስከትልብኛል የሚል አቋም ኖሮት ተጠሪው ግብሩን ከፍሎ የስም ዝውውሩን የሚያስፈፅም ሆኖ ከተገኘም የከፈለውን የካፒታል ዕድገት ግብር ከስር 3ኛ መልስ ሰጪ የማስተካት መብት እንዲኖረው መደረጉን ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

## ውሳኔ...

1.የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመመለያ ቁጥር 69181 በ30/06/04 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤትበ ስነስርዓት ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።
2. አመልካች ካፒታል እድገት ግብሩን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሳኔው መሰረት ከስር 3ኛ መልስ ሰጪ ተከታትሎ ገቢ ካስደረገ በኋላ የስም ዝውውሩን ያስፈጽም በማለት ወስነናል።
3. ተጠሪ የጉዳዩ መዘግየት ሊያስከትልበት የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ያስችለው ዘንድ ግብሩን እራሱ ከፍሎ ከስር 3ኛ መልስ ሰጪ ለማስተካት የሚፈልግ ከሆነ የካፒታል እድገት ግብሩን ብር 803,997.33 (ስምንት መቶ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ከ33/100) ከፍሎ የስም ዝውውሩን እንዲያስፈፅም እና የስር 3ኛ መልስ ሰጪም ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወሰነው መሰረት ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲተካ ወስነናል ሲል ዳኞች ሃሳባቸውን ይቋጫሉ።።
4. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
5. በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው የወጪና ኪሳራ ውሳኔ አልተነካም።
6. የአፈፃፀም እግዱ ተነስቷል።
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል ሲል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻውን ውሳኔ በማሳለፍ መዝገቡ ዝግ ሆኗል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## አንድ ሆኖ ወደ ፊት

**ተገኝ ብሩ**

አንድ ሆኖ በመኖር ውስጥ አንድ አይነት መሆን ግድ አይደለም። አንድ ሆኖ በመቆም ግን የመለያየትን እና የመጣረስን ሳንካ ማስወገድ እጅጉን ይቀላል። ምድር በራስዋ አንድ ሆነው በትብብር ሲኖሩባት እንጂ አንድ አይነት ብቻ ሲሆኑባት ትሰለቻለች። አለያይቶ በተለያየ ቋንቋ የፈጠረን ለምክንያት አመለካከታችን የተሰበጣጠረው ለጥበቡ እርሱ ለሚፈልገው መሻቱ ይሆናል። ጣቶቻችን ተመሳስለው በእኩል ቁመትና እና ውፍረት በተመሳሳይ ቅርፅና መጠን ያልተሰሩ ለምን ይሆን? ብለን አስበን እናውቃለን?

አዎን! እያንዳንዱ ለእኛ አስፈላጊ ናቸውና አንድ አይነት ሳይሆን አንድ ሆነው መስራት እንዲያስችሉን፣ እንዲመቹን በዚያ መልኩ ተገኙ ወይም ተፈጠሩ፤ እናም አንዱ ካንዱ ጋር አብሮ በመሆን አንድ ተግባር በትክክል ይከውናል። ይህ አንድ ታላቅ ነገር ያሳየናል፤ እሱም አንድ የመሆን ልዩ ጥበብ አንድ አይነት ከመሆን ፍላጎት ጋር እጅጉን የተለያየ መሆኑን።

ወገን ትልቁ መረዳት ያለብን ቁም ነገር እዚህ ላይ ነው። አንድ ሆኖ ለመቆም አንድ አይነት ሆነን መገኘት የለብንም። አንድ አይነትነት በራሱ ስለሌለ መፍጠርም ይከብዳል። አንድ አገር በመገንባት ሂደት ውስጥ ብዝሀነት ማክበር ወሳኝ ጉዳይ ነው። የእኛን አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ ባህል እምነትና ወግ ከሌላው ጋር ፍፁም የተለየ ሊሆን ይችላል። ያ መለየት ተፈጥሯዊ ነው። ለምን ተለያየ የሚል ምላሽ የሌለው ማብራሪያም መጠየቅም ተገቢነት የለውም።

የእኛ ያልነውን እንደወደድነው ሁሉ ሌሎች የራሳቸው መውደዳቸው ግድ ነውና የእነርሱን ማክበር ይገባል። የእኛ ያልነው እንዲጠበቅ ስንገለገልበት የሌላውን በማይነካ መልክ መጠቀም፤ የሌሎችንም እንዳንነካ መጠንቀቅ እንዲያከብሩልን ክብር መስጠት ይገባናል። ያኔ አንድነቱ ይደረጃል፤ ያን ጊዜ አብሮነቱ ይጠነክራል። አገር በዚህ ውስጥ ሀያልነትዋ እውን ይሆናል።

በተለይ እንደኛ ብዝሃነት በተለያየ መልኩ በዝቶ ባለበት አገር ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብ አይደለም፤ተመሳሳይ የሆነ እምነት ባህልና ተቀራራቢ የሆነ ስልቦናዊ ስሪት ባለው ማህበረሰብ ውስጥ እንኳን የሀሳብ ልዩነት ገዝፎ ይታያል። ዋነኛው ጉዳይ የተለያየው ሀሳብ በምን መልክ ነው አስታርቆ በአንድነት መጓዝ የሚቻለው የሚለው ላይ ነው። የእኛ መሰረታዊ ችግርም ይሄው ነው።

አዎ! የችግራችን መነሻው ይህ ነው፤ ልዩነታችን ተቀብለን ተቻችሎ በአንድነት መቆም አለመቻል፤ የጋራ መግባባት ላይ የደረሰ ማህበረሰብ አለመገንባት።

ከማቅረብ ይልቅ የምንገፋው ይበዛል። በአንፃሩ ሲገፉን መገፋታችን ያንገፈግፈናል። አቤት የምንገፋው ነገር እኮ ነፍ ነው ጎበዝ፤ የማንገፋው ምን አለ ? የሌሎችን ሀሳብ፣ የተጠጉን መልካም እድሎች፣ የኖርንበት ባህል፣ የተሰጠን ኃላፊነት ብቻ ምኑ ቅጡን ዘርዝሬ እጨርሰዋለው ወዳጆች ገፊ ነን። መልካም ነው ብለን ያመንበት ሀሳብ በሌሎች ተቀባይነት ቢያገኝ እንወዳለን። ነገር ግን የእኛን ሀሳብ ሌሎች እንዲቀበሉን የምንወደውን ያህል የሌሎችን ሀሳብ ለማድመጥ ዝግጁ ያልሆን የሀሳብ ገፊዎች ነን።

የእኛ እምነትና እሳቤ የፈጠረውን ሀሳብ ለሌሎች ማሻገር ወይም መስጠት የመውደዳችን ያህል፤ የሰዎችን ሀሳብ ከመቀበል ይልቅ መግፋት ልምዳችን ሆኗል።

አዎ! ብዙ የገፊነታችን ማስረጃ ገፆቻችን ስንገላልጥ ጥንካሬ የሌለን ምክንያት አልባዎች መሆናችን ይለያል። በምክንያት የሚያምን ትውልድ፤ የመስጠትን ያህል መቀበል ያውቃል።

እኛ የምናምንበትና የምናከብረው በሌሎች ላይ እንዲጋባ የምንፈልገው ሀሳብ ሌሎች ጋር ምንም ቦታ የሌለው ብዙም የማይገዝፍ ምንአልባትም ጉዳዩ በሌላ አይን ከቁብ የማይቆጠር ሊሆን እንደሚችል አይገባንም። ልክ እኛ የሌሎች ሀሳብ ብዙ ጊዜ ቁብ እደማንሰጠው ሁሉ ማለት ነው። ይህን እውነታ መቀበል ይኖርብናል። ሁሉም የእኛ ያቀረብነው ሀሳብ ደጋፊ ላይሆን እኛ ደግሞ የሌሎችን ሀሳብ ተቀባይ ላንሆን እንችላለን። በመሰረቱ እኛም እነሱም ልክ ነን። እኛ የሌሎች ሀሳብ መቀበል የማንችልበትን ትልቅ ምክንያት ይኖረን ይሆናል። በአንፃሩ ደግሞ ሌሎች የእኛን ሀሳብ መቀበል የማይችሉበት ብዙ ምክንያት ሊኖራቸው እንደሚችል መረዳት ይገባል።

መግባባት ይቻል ዘንድ ጥበብ በተሞላበት መንገድ ሀሳብን ወደሌሎች ለማስረፅ መሞከር ከሰለጠነ ዜጋ የሚጠበቅ ነው። የያዝነው ሀሳብ ልክ ነው ብለን ካመንን የሀሳቡ ግዝፈትና የጉዳዩ እውነተኝነት ደግሞ ለማሳየት መሞከር ይገባል። ይሄኔ ግን ሌሎች የራሳቸው የሆነ ከኛ ሀሳብ ጋር የማይሄድና ተቃራኒ ሊሆን እንደሚችል ሀሳብ ሊኖራቸውና የእኛን ሊቀበሉ መረዳት ይኖርብናል።

በእርግጥ የያዝነው ሀሳብ ግዝፈት ብዙዎችን ወደኛ ሊጠራና የሀሳባችን ደጋፊ ብሎም ተሚጋች ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን ምንም ያህል ታላቅ እና አሸናፊ እንዲሁም ሀቀኛ እምነት የሚወልድ ሀሳብ ከእኛ ወደሌሎች እንካችሁ ስንል ከሌሎች የምናገኘው ምላሽ የተሟላ ላይሆን ይችላል። ምን አልባትም ጭራሽ ተቀባይነት ላናገኝም እንችል ይሆናል። ምን አልባትም አንዳንዴ ሀሳባችን የተሳሳተ መሆኑን በሌሎቹ ሀሳብ ውስጥ ሊገለጥልንም ይችላል።

ከሌሎች ጋር እየተናጋገርን አልያም እያወራን ሳለ፤ የተላመድነው የሀሳብ ገፊነት ልማዳችን ይቆጣጠረንና እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል በፍፁም ብለን እንደመድማለን። ነገር ግን ሀሳባችን በሌሎች ሀሳብ ውስጥ ጠልቆ ሊመረመር የሚችል እና በዚያኛው ወገን የጠነከረ ምክንያት ሊገጥመን እንደሚችል መረዳ ይገባል። ሀሳባችን አሳማኝ በሆነ መልኩ በሌላ ሀሳብ ሊረታ የሚችል መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

አንቀበልም ብለን የምንገፋው የሌሎች ሀሳብ የእኛ ሀሳብ ተቃራኒ በመሆኑ ምክንያት አልታይ ያለን ግን ደግሞ የገዘፈ ሊሆን ይችላል። ለእኛ የተሰወረው ነገር ግን ግዙፍ የሆነው ሀሳብ እኛ ከቆምንበት ሀሳብና እውነት ነው ብለን ካመንበት ጋር የሚጣረስ ቢሆን እንኳ መሆኑን መቀበል ይኖርብናል። በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ያቀረብነው ሀሳብ ምንም ያህል ሚዛን የሚደፋ እንኳን ቢሆን ወደሌሎች ስናሻግር ጥበብ በተሞላበት መንገድ ቢሆን ስኬታማ እንሆናለን።

አንድ ወደፊት አራምዶ ሁለት ወደ ኋላ የሚመልሰን ጉዳይ ምንነት ለማወቅ ያስችለን ዘንድ መነሻችን ላይ ቆም ብለን እንዴት መጓዝ እንዳለብን ማሰብ ይገባናል። የጉዟችን ገቺ ምክንያቶች ምንነት ስንመረምር ደግሞ አብሮ ለመጓዝ የሚያስችሉ ስንቆች ሁላችን አለመታጠቃችን እንገነዘባለን። የአብሮነት ጉዞ ስንቅ ከሆኑት መካከል ደግሞ ተደጋግፎ መሻገር፣ተነጋግሮ መግባባትና ለሌላው ክብር መስጠት ዋንኞቹ ናቸው። ላዛሬ አበቃሁ ቸር ይግጠመን።

# ዓለም አቀፍ



## ቱርክ ዓለም ላይ የረሃብ አደጋ ሥጋት ሳይባባስ የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት እልባት እንዲሰጠው ጠየቀች

አዲስ አበባ ፣ የሩሲያ – ዩክሬን ጦርነት በዓለም ላይ የተከሰተውን የረሃብ አደጋ እንዳያባብስ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በትብብር እንዲሠራ ተመድ ባካሄደው የከፍተኛ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ቱርክ ጠየቀች፡፡

ተመድ "በዓለም አቀፍ ደረጃ የምግብ ዋስትናን በድርጊት የማረጋገጥ ጥሪ " በሚል መሪ ቃል የከፍተኛ ሚኒስትሮች ስብሰባ በአሜሪካ አካሂዷል፡፡

በስብሰባው ላይ ንግግር ያደረጉት የቱርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሜቭሉት ካቩሶግሉ፥ አገራቱ ከጦርነቱ በፊት በምግብ አቅርቦት እና ምርት ላይ ከፍተኛ ድርሻ እንደነበራቸው አስታውሰዋል።

በመካከላቸው ከተከሰተው ግጭት ወዲህ ግን በቂ ምርት ማምረት እንዳልቻሉ ናብሎም በወጪ ንግድ ሲሸፍኑት የነበረውን የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ የምግብ አቅርቦት ፍላጎት መሸፈን እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሩሲያ በዩክሬን ላይ እየፈጸመች ያለችው ጥቃት ለአገራቱ ብሎም ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ትልቅ ፈተና ሆኗልም ነው ያሉት፡፡

በመሆኑም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በመተባበር ሁለቱ አገራት ከግጭት ወጥተው ሥምምነት ላይ የሚደርሱበትን የሠላም አማራጭ መፈለግ እንዳለበትና ረሃብ እንዳይባባስ እንዲሠራ ጠይቀዋል።

አያይዘውም በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ 800 ሚሊየን ህዝብ እንደተራበ የገለጹ ሲሆን ለረሃቡ ቀውስ ጦርነት እና ግጭቶች ዋነኛ አባባሽ ምክንያቶች ናቸው ብለዋል፡፡

ከዚህ ውስጥ ደግሞ 60 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የሚገኘው በግጭት ቀጠናዎች አቅራቢያ እንደሆነም ተጠቁሟል፡፡

ቱርክ ከተባበሩት መንግስታት ጎን በመቆም ማናቸውንም የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦት እና ተልዕኮዎች ለመፈጸም ዝግጁ ናት ማለታቸውን የዘገበው አናዱሉ ነው፡፡

## ባይደን የስዊድን እና ፊንላንድ ኔቶን የመቀላቀል ጥያቄን አሜሪካ ሙሉ ለሙሉ ትደግፋለች አሉ

ስዊድን እና ፊንላንድ ለሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅትን (ኔቶ) አባልነት ያቀረቡት ማመልከቻ በአሜሪካ "ሙሉ ድጋፍ" ይሰጠዋል ሲሉ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ገለጹ።

የአውሮፓን ጂኦፖለቲካ በሚቀይር መልኩ ሁለቱ አገራት በዚህ ሳምንት ነበር የጦር ቃል ኪዳን ድርጅቱን ለመቀላቀል ጥያቄ ያቀረቡት። ሁለቱ አገራት የጥምረቱ አባል ለመሆን የሰላሳውንም የኔቶ አባል አገራት ይሁንታን ማግኘት ይጠበቅባቸዋል።

የሁለቱ የኖርዲክ አገራት የአባልነት ጥያቄ ከቱርክ ተቃውሞ ገጥሞታል። ከስዊድን ጠቅላይ ሚንስትር ማግደሊና አንደርሰን እና ከፊንላንዱ ጠቅላይ ሚንስትር ሳውሊ ኒኒስቶ ጋር በኋይት ሃውስ መግለጫ የሰጡት ባይደን የአገራቱን ጥያቄ "ለአውሮፓ ደህንነት አዲስ ምዕራፍ ከፋች ነው" ሲሉ ገልጸዋል።

"አዳዲስ አገራት ኔቶን መቀላቀላቸው ለየትኛውም አገር ስጋት አይደለም" ብለዋል። ሁለት ተጨማሪ አገራትን "በሰሜን አቅጣጫ" ማግኘት "የአጋሮቻችንን ደህንነት ለማጠናከር እና በአካባቢው ያለንን የደኅንነት ትብብር ለማሳደግ ይጠቅማል" ብለዋል።

የኔቶን መስፋፋት ስጋት መሆኑን በተደጋጋሚ የምትገልጸው ሩሲያ በበኩሏ መስፋፋቱ ከቀጠለ "አጸፋ" እንደሚኖር ዝታለች።

ቱርክ በበኩሏ ስዊድን እና ፊንላንድ የኩርዲስታን ሠራተኞች ፓርቲ (ፒኬኬ) ታጣቂዎችን በመርዳት ትከሳለች። ቱርክ ፓርቲውን በአሸባሪነት ፈርጃለች።

የኔቶ ዋና ጸሐፊ የንስ ስቶለተንበርግ እና የዩናይትድ ኪንግደም መከላከያ ሚስትር ቤን ዋላስ ጉዳዩ እልባት እንደሚያገኝ ተስፋቸውን ገልጸዋል።

የባይደን አስተያየት የተሰማው የአገሪቱ ሴኔት ለዩክሬን አዲስ የ40 ቢሊዮን ዶላር የመከላከያ እና ሰብዓዊ ድጋፍ ለመስጠት የቀረበውን ሃሳብ መደገፉን ተከትሎ ነው። ይህም ለዩክሬን የተሰጠ ትልቁ የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ሆኗል።

ከቀናት በፊት በህዝብ እንደራሴዎች ድጋፍ አግኝቶ የነበረው ድጋፍ በሳምንቱ መጀመሪያ እንደሚጸድቅ ተጠብቆ ነበር። የኬንታኪው ሪፐብሊካን ራንድ ፖል ወጪውን በመቆጣጠር ጉዳይ ላይ ባነሱት ጥያቄ መጓተቱ ታውቋል።

የሴኔቱ የሪፐብሊካን መሪ ሚች ማክኮኔል ስጋቱን አጣጥለዋል። ለሪፖርተሮችም ኮንግረሱ "ሉዓላዊ ራስን መከላከልን" የመደገፍ "የሞራል ኃላፊነት አለበት" ብለዋል።

"ዩክሬንን አሸናፊ ለማድረግ የሚደረገውን የድጋፍ ዋጋ በተመለከተ ስጋት ያለበት ሁሉ ዩክሬን ብትሸነፍ ያለውን ኪሳራ ማጤን አለበት" ብለዋል።

ባለፈው ሳምንት የመከላከያ ሚኒስትሩ ልዮድ ኦስቲን እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አንቶኒ ብሊንከን ኮንግረሱ ድጋፉን እንዲያጸድቅ እና የአሜሪካ መከላከያ መላክ የሚችለው ለጥቂት ቀናት ብቻ የሚበቃ መሣሪያ ብቻ እንዳለው አስታውቀው ነበር።

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜለንስኪ ድጋፉን "አሜሪካ ለዩክሬን፣ ለአውሮፓ እና ለዓለም ሠላም መስፈን የምታደርገው ትልቅ እገዛ" ነው ሲሉ ገልጸውታል።

ለስልጠና፣ መሣሪያዎች እና ድጋፍ የሚደረገውን የስድስት ቢሊዮን ዶላር የደህንነት ድጋፍ ጨምሮ የአሁኑ አሜሪካ ለዩክሬን የሰጠችውን ድጋፍ ከ50 ቢሊዮን ያሳልፈዋል።

እስካሁን ለዩክሬን የተሰጠውን የአሜሪካ የመሣሪያ ድጋፍ ለማሟላት ደግሞ ተጨማሪ 8.7 ቢሊዮን ዶላር ተመድቧል።

**ምንጭ ቢቢሲ**

# ለተከሳሽ ፍርድ ሲሰጥ!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

ከሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በስፋት እየተሰራጨ ያለ አንድ አስተማሪ የችሎት ገጠመኝ አለ። ከተለመደው ልምድ ውጭ ፍርድ የሰጠ ዳኛ ያሳየው ሰብዓዊነትን በሚያወድሱ አስተያየቶች የተሞላ ጽሁፍ። ከሳሽ ተሰርቄያለሁ ሌባውም ይህነው ብሎ ለሚጠብቀው ፍትህ ዳኛው ተከሳሽን ከክሱ ነጻ አድርገው ከሳሽ ላይ ፍርድ ማሳለፋቸውን የሚያትት ትረካ። ታሪኩ በተጨባጭ የተከናወነ ትክክለኛ ታሪክ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማግኘት ባይቻልም ስለሰብዓዊነት ያለው አስተማሪነቱ ከፍተኛ ስለሆነ እንደ መንደርደሪያ እንጠቀምበት።

ከሳሽ ያቀረበው ክስ ፍሬ ነገሩ ታዳጊው ልጅ ዳቦ ከከሳሽ የንግድ ሱቁ እንደሰረቀ የሚያስረዳ ነው። ዳኛው እንደተለመደው እጅ ከፍንጅ የተያዘ ሌባ ላይ ከሚሰጠው ፍርድ መለስ ብሎ ልጁ ለምን ሊሰርቅ እንደቻለ ተከሳሹን በመጠየቁ ሂደት ውስጥ ትኩረትን ሳቢ ውሳኔ ላይ የደረሰው። ተከሳሽ ለምን እንደሰረቀ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው ምላሽ እርቦት እንደሆነ ነው። ቤተሰቦቹ ስለምን አልመገቡትም ብሎ ዳኛው ባስከተለው ጥያቄ ሌላ ገጽ ተገለጠ፤ የተከሳሽ እናት በህመም ምክንያት አልጋ ላይ መሆናቸውን የሚያስረዳ። በስተመጨረሻ ተከሳሽ ስርቆት የፈጸመው የራሱንም የእናቱንም ሕይወት ለማትረፍ እንደሆነ ችሎቱ ተረዳ። የዳኛው ፍርድ የነበረው ሌባውን ተከሳሽ ጥፋተኛ ማለት ሳይሆን የችሎቱን ታዳሚዎች፣ ራሱን ዳኛውንና ከሳሽን ጥፋተኛ ማድረግ ነበር። “እኛ እያለን እንዴት አንድ ታዳጊ ዳቦ መስረቅ ውስጥ ይገባል?” የሚል ጥያቄን በፍርድ አሰጣጡ ውስጥ ምላሽ ለመስጠት ዳኛው ይሞክራል። ከሳሽ ከተከሳሽ ሊከፈለው የሚገባ ነገር እንዳይጠብቅ ሆኖ በተቃራኒው ከሳሽ ለተከሳሽ መክፈል ያለበት ተነገረው፤ ችሎቱ ውስጥ የተሰበሰቡ እንዲሁ ለተከሳሽ መክፈል ያለባቸው ተነገራቸው፤ ዳኛውም አብነት ሆኖ የራሱን መዋጮ አስቀደመ መዝገቡም ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ታዘዘ። “እኛ እያለን እንዴት አንድ ታዳጊ ዳቦ መስረቅ ውስጥ ይገባል?” የሚለው ጥያቄን መልስ ይሰጡ ዘንድ በዳኛው ዙሪያ የተሰበሰቡ በተለያየ መጠሪያ የሚጠሩ አካላት ተጋበዙ። ሰዎች ዳቦ ወደ መስረቅ ከሄዱ ችግሩ የእነርሱ ሳይሆን የሁላችን ነው የሚል መልእክትም ተላለፈ።

ይህ ታሪክ በተጨባጭ የሆነ ታሪክ በመሆን ዙሪያ ላይ እርግጠኝነት ባይኖረንም አስተማሪነቱ ብዙ ስለሆነ እያሰላሰልነው እንዝለቅ። ራሳችንን በዳኛው ቦታ፣ በከሳሽ ቦታ፣ በተከሳሽ ቦታ፣ በችሎት ታዳሚያን ቦታ አድርገን የሚሰጠንን ትርጉም አውጥተን አውርደን እንየው።

በአገራችን ችሎቶች ድንገት እግር ጥሎን የምንመለከታቸው ጥቃቅን የሚመስሉ መዝገቦችን ባህሪ ስንመለከት ከታዳጊው ልጅ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን አያሌ መዝገቦች ማግኘት እንችላለን። ከተለመደው አልፎ በመሄድ ውስጥ በቀላሉ በቅኖች ሊፈቱ የሚችሉ መዝገቦች።

በዛሬው ቆይታችን በማህበረሰባችን ውስጥ ተከሳሽ አድርገን ስለምናቀርባቸው በማህበረሰብ ጤንነታችን ውስጥ ችግር ስለሆኑብን ጉዳዮች እንዲሁም የቅኝት ፍተሻ እናደርጋለን። “ከበሮ በሰው እጅ ሲያዩት ያምር፤ ሲይዙት ያደናግር”እንደተባለው በሰዎች እጅ ነገሮች የሚሆኑበትን ነገር ተመልክተን በብዙ ከሳሽ ሆነን ነገር ግን ራሳችንን በአግባቡ መመልከት ስንችል የሚኖረንን አተያይ እንፈትሻለን። ማህበረሰባዊ ለውጥን ከእሴት፣ እውቀት እና ተግባር ውስጥ ማግኘት እንችል ዘንድ የሚቀሰቅስ መልእክት። እዚህም እዚያም የበዙትን የክስ መዝገቦችን ቀጥሎ እንመልከት፤

## የክስ መዝገቦች በየመልካቸው

በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ጥናታቸውን የሚያደርጉ ባለሙያዎች እያረጋገጡ የመጡት አንዱ እውነት ማህበራዊ ሚዲያ ግነትን የሚፈልጉ፤ ትኩረት ሳቢ የሆኑ፤ ከተለመደው ወጣ ያሉ ነገሮችን ይዞ መቅረብን የሚገፋፋ መድረክ መሆኑን ነው። በአጭሩ ከሌላው ተለይቶ የመታየት በሽታ ሰለባ የሚያደርግ። ይህም ጭንቀት የመፍጠር አቅሙን እና ጭንቀትን የማጋራትና የማስፋት አሉታዊ ጎኑን ያሳያል። አንድ ሰው እንዴት ባለ ሁኔታ ቢያቀርብ ለየት ያለ ነገር ሊያቀርብ እንደሚችል እንዲያስብ የሚያነሳሳና ድፍረትን መጠቀምን የሚሰብክ ልንለውም እንችላለን። በዚሁም ምክንያት ግለሰቦች በብዙ ጉዳዮች ላይ ድፍረት በተሞላው መንገድ አቋማቸውን ሲያራምዱ ይስተዋላል። በአካላዊ ግንኙነት ደፍረው የማይሉትን ነገር በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ግን የሚሉበት እድል ያለ መሆኑን የሚያመላክት ነው። የክስ መዝገቦች በየመልካቸው የሚታየውም እዚያው ማህበራዊ ሚዲያዎች ገጽ ላይ ነው።

እግር ኳስ ተጫዋቹ፣ አርቲስቱ፣ የአገር መሪው፣ የአካባቢ አስተዳዳሪው፣ የማህበረሰብ አንቂው፣ የአገር ሽማግሌው ወዘተ ሁሉም የቀረበበት የክስ መዝገበው በማህበራዊ ሚዲያው ላይ በግልጽ ተሰጥቶ ይታያል። ክስ ያልቀረበበት አካልን ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ እስኪሆን ድረስ በየቀኑ የክስ መዝገብ በፌስቡክ፣ በዩቲዩብ፣ በቲውተር እና በሌሎችም መድረኮች ላይ ሲዘንብ እናገኛለን። ሁሉም ከሳሽ፤ ሁሉም ተከሳሽ ሆኖ የሚታይባቸው መድረኮች ብንላቸው እንችላለን። ለአንድ ጉዳይ ወደ አንድ ተቋም ባለጉዳይ ሆኖ የገባ ሰው ከእርሱ ጉዳይ በመነሳት ተቋሙ ላይ የቁጣ ዝናብ አዝንቦ ሊያልፍ ይችላል። ሁሉም ነገር ላይ በድምዳሜ ‘ይህ የሆነው፤ ይህን ለማድረግ ነው ወዘተ’ በማለት ደምድሞ አደባባይ ላይ ክስ ማስቀመጥ የማይቸግርበት ዘመን። እንዲህም ማድረግ እንደ ጀብዱ የሚቆጠርበት ጊዜ። ምናልባትም ወደፊት መደበኛው ፍርድ ቤት እየቀረ ሰው ሁሉ ማህበራዊ ሚዲያው ላይ ክስ አቅርቦ እዚያው ተከታዮቹ በአስተያየት መስጫ ሳጥን ውስጥ ድምጽ ሰጥተው ብይኑን አሳልፈው ይህን ወስነናል የሚሉበት ዘመን ይመጣም ይሆናል ብለን እንድናስብ የሚያደርግ።

እንዲህ ባለሁኔታ የክስ መዝገቦች በየመልካቸው ገበያ በወጡበት ዘመን ውስጥ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚመረምሩ፤ ነገሮችን በችኮላ ከማየት ይልቅ እርጋታን የሚመርጡ፤ ብልሃትን ልብስ አድርገው ለብሰው የሚንቀሳቀሱ ሰራተኛ የሆኑ ሰዎች አንሰው ይታያሉ። መከሩ ብዙ ነው፤ ሰራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው እንድንል የሚያደርገን የዘመን ገጽ። እሴት፣ እውቀት እና ተግባር ተገናኝተው ከአንድ ተከሳሽ ታሪክ ውስጥ ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ ፍርድን የመፈለግ አቅምን የሚፈትን ጊዜ።

## መከሩ ብዙ፤ ሰራተኞች ጥቂቶች

ለውጥ የሰዎች የተጋድሎ ውጤት ነው። በየዘረፉ ብቃት ያላቸው ሰዎችን ማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ ሲነገር እንሰማለን። በተለይ በአገራችን በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓቱ ጥያቄ ውስጥ በገባበት ሁኔታ ውስጥ ጥራት ያለው አምራች ሃይል ማግኘት አስቸጋሪ ነው። የክስ መዝገብ በአደባባይ ተሰጥቶ በምናይበት በዚህ ዘመን ውስጥ ሰዎች ወደ ኃላፊነት በተለይም ወደ ህዝብ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ከመምጣት እንዲሸሹ እየሆኑ ደግሞ የለውጥ አብነት የሚሆኑ ሰራተኞችን ቁጥር ያመነመነው ይመስላል። በተወሰነ ደረጃ የኢትዮጵያ ችግር አንዱ መንስኤ ይህ ሊሆን እንደሚችል ብናስብ የተሳሳትን አንሆንም።

የፈረሰው ነገር ብዙ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ለስራው የሚገኙ ሰራተኞች ጥቂት በሆኑበት ሁኔታ የከሳሽና ተከሳሽ መድረክ የራሱን ሌላ መልክ ይይዛል። ይህ ሲሆን ለመንደርደሪያ ታሪካችን የተጠቀምንበት የሌብነት መነሻ የሆነውን ጉዳይ ተረድቶ መፍትሔ መስጠት ሩቅ የተሰቀለ ሊሆንም ይችላል። እንደ አገር አንድ ሰው ስለሚበላው ምግብ ብሎ ወደ ስርቆት ከገባ ተጠያቂነቱ የሁላችንም ነው ብሎ ለማሰብ ከሚያጋፋው ሁሉ ወጣ ብሎ በሚዛን ማሰብ የሚችሉ የለውጥ አብነቶችን የሚፈልግ ስለሆነ።

የዘመኑ የቴክኖሎጂ እድገት፣ የተሰወሩ እውቀቶች መገለጥ እንዲሁም ከታሪክ ወይንም ከትላንት የሚወሰደው ትምህርት መብዛት ባለበት ሁኔታ ወደ አስደማሚ እድገት የሰው ልጅ መግባት ይኖርበት ነበር። በተጨባጭ ግን የሰው ልጅ በቴክኖሎጂ ውጤቶች ተከብቦ ግናግን የጋርዮሽ ኑሮን ይኖር እንደነበረው አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እየኖረ ይገኛል። የሰው ልጅ በብሔሩ ሆነ በኃይማኖቱ አግላይ ወይንም የሚገለል ሲሆን ወይንም አግላይ ሲሆን አንዳች የጎደለ ነገር ስለመኖሩና ከዘመኑ ጋር የሚሄድ አተያይ ላይ አለመገኘቱን ያሳየናል። ለዚህ የሚቀርበው ምክንያት በዘመኑ ውስጥ ያለው እድገት ማነስ ሳይሆን ያለው ሰዎች ቁጥር ማነስ ወይንም ጎልተው መታየት አለመቻላቸው ነው።

ለውጥን የሚፈልጉ ጉዳዮች ብዙ ናቸው፤ ነገር ግን ሰዎቹ በበቂ ሁኔታ የሉም። ስለሆነም የከሳሽና ተከሳሽ ባህላዊው መዝገብ ባለበት መንገድ ይቀጥላል። ሌባው ስለምን ብሎ ሌባ ሆነ? ሴተኛ አዳሪዋ ስለምን ብላ ሴተኛ አዳሪ ሆነች? ወዘተ ብሎ ጠይቆ ወደ ችግሩ ምንጭ ለዘላቂ ለውጥ ከመሄድ የሚመልስ ሆኖም እንረዳዋለን። የተከሳሽና ከሳሽ ቀመሩን መፈተሽ አለብን ብለን ስንነሳ ሊሰራ የሚገባውን ብዙ ስራ እናያለን። በእሴት ያደጉ ሰዎችን፤ በሌላኛው ጫማ ውስጥ ሆነው ነገሮችን የሚመለከቱ፤ ኃላፊነትን ከእኔ ተጠያቂነቱ ትርጉም ሰጥተው የሚኖሩ፤ የሥራ ውጤትን በመልኩ በመለካት ከዛሬ ነገ የተሻለ ማድረግን ግብ የሚያደርጉ ወዘተ መኖራቸው ለለውጡ ዋና ሃይል ናቸው።

አንባቢው እራሱን ይጠይቅ ሊሰሩ የሚገባቸው ብዙ ስራዎች እንዳሉበት ትውልድ አንድን ቀዳዳ ለመድፈን እየሰራ በመሆኑ የከሳሽና ተከሳሽ መዝገብን እየቀነሰ ያለ ወይንስ በተቃራኒው መዝገብ እያበዛ? ለጥያቄው የሰጠውን ምላሽ ለጊዜው ያዝ አድርጎ ሁሉ ከሳሽ፤ ሁሉ ዳኛ በሆነበት ወቅት ውስጥ ስለመሰረታዊ ለውጥ እናስብ።

## መሰረታዊ ለውጥ

መዳረሻችን በመነሻችን ውስጥ ያነበብነው ታሪክ ውስጥ እሴት፣ እውቀትና የተግባር እርምጃ የፈጠሩትን አዎንታዊ ተጽእኖን ማሳየት ነው። የዳኛው ልብ ከደረቅ ህጎች ባሻገር። መዝገብ በአደባባይ በተሰጣበት ሁሉ ከሳሽ ሁሉ ዳኛ በሆነበት ዘመን ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው አንድ የአዎንታዊ ለውጥ እርምጃ። እርምጃው ወደ ውጤት የሚያደርስ ይሆን ዘንድ ወደ ብሩህ ብርሃን የመመልከት። አስደናቂዋ ሴት ሔለን ኬለር “ወደ ፀሐይ ጮራው ተመልከት፤ ያንጊዜ ጥላውን አታይም” እንዳላቸው ሊታይ ወደሚገባው አቅጣጫ ማየትን በማስቀደም የተከሰተ ቢሆንም ሊታይ ያልተገባውን ያለማየት ማሳያ። የለውጥ መንገድ አተያይ።

በለውጥ መንገድ ውስጥ ሲሆን በለውጥ ውስጥ በመገኘት ውጤትን የራስ ለማድረግ ሲታሰብ የሚኖረው ፈተና ቀላል አይሆንም። ሁሉ ከሳሽ ሁሉ ዳኛ ሆኖ ሲመጣ ዳኛው የህግ ስርዓቱን አካሄድ አበላሽቶ እንዲህና እንዲያ ወስኗል ተብሎም ሊጠቀስ ይችላል። የከሳሽን መብት ረግጧል ወዘተ የሚሉ ድምጾች መሰማታቸውም እንዲሁ ሊሰማ ይችላል። የአስተሳሰብ ለውጥ በሌለበት ቦታ ሁሉም ነገር አነጋጋሪ ሆኖ በጎራ መሰለፍን የሚገባዝ በመሆኑ።

ስለ መሰረታዊ ችግሮች መፈታት ስናስብ መሰረታዊ አስተሳሰብ ለውጥ የግድ እንደሆነ ደጋግሞ በማስመር ማለፉ አስፈላጊ ነው። ለመሰረታዊ ለውጥ ከተለመደው ወጣ ብሎ ለመሄድ እይታን ሊታይ በተገባው ላይ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ፀሐይ ላይ። በእርግጥ ወደ ብርሃን ጉዳይን ይዞ መውጣት ቀላል አይደለም። ሁሉ ወደ ብርሃን ቢወጣ ሰው ሁሉ እውነትን ወደ መነጋገር ቢመጣ፤ ሰው ሁሉ ሊያየው የሚገባው ላይ ትኩረት ቢያደርግ የጨለማው ስራ በስፋት በተገለጠ እና የለውጥ መንገዶች አንድ ምእራፍ ብቻም ሳይሆን በእጥፉ ወደ ውጤት ባደረሱን ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምንዝርና የተያዘች ሴት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ቀረበች። በሙሴ ህግ



መሰረት ተወግራ ትገደል ዘንድ ህግ የሚደነግጋበት። የእርሷን ጉዳይ እንዴት እንደሚያየ የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ድንጋይ በእጃቸው አድርገው መውገር ከመጀመራቸው በፊት እርሱንም በፈተና ጠልፈው ለመጣል ወደ እርሱ ይዘዋት ቀረቡ። እርሱም ፈረዳ ፍርዱም ምንም ኃጢአት የሌለበት ሰው እርሱ የመጀመሪያውን ወጋሪ ይሁን የሚል ሆነ። ሁሉም ራሱን ሲመለከት ከጀርባው የተሸከመው ትዝ እያለው ድንጋዩ እያስቀመጠ ወደኋላ ተመለሰ። ከተለመደው ወጣ ብሎ ፍትሕ በመስጠት ውስጥ የተላለፈ ብይን። እሴት፣ እውቀት እና ተግባር ተገናኝተው የሚፈጥሩት የአስተሳሰብ ለውጥ ማሳያ።

## እሴት፤ እውቀት፤ ተግባር

የመነሻ ታሪካችን ዳኛን በእሴት፣ እውቀት እና ተግባር ውስጥ ተመልክተን ወደ መውጫችን እንድረስ። በዳኛው ውስጥ ያለው የእሴት ሕይወት ተጠርጣሪውን በተለየ መንገድ እንዲያይ የተጠርጣሪውን እውነት ለማየት ብዙ እርቀትን መራመድ እንዲችል ያደረገው ነበር። በእሴት የተገነባ ግለሰብ፣ ቤተሰብ እንዲሁም ማህበረሰብ በቀላሉ ለፈተናዎች እጅ የማይሰጥ ነው። ለፈተናዎች እጅ አለመስጠት ብቻም ሳይሆን በሌሎች ጫማ ሆኖ ነገሮችን ተመልክቶ በሚጠቀም መንገድ ውስጥ መራመድ የሚችል።

እውቀት ሌላው ዳኛውን መመልከቻ ነጥብ ነው። በህግ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለፈ ሰው ሊኖረው የሚገባውን እውቀት ይዞ በቦታው ላይ የተሰየመ መሆኑን ስናይ የምናገኘው። እውቀቱ ከእሴት ጋር ተዳምሮ ለሰጠው ውሳኔ አስተዋጽኦ ማድረጉም ግልጽ ነው። እውቀትን ለማህበረሰብ ጥቅም በሚውልበት ሁኔታ ላይ መጠቀም ለሚወድ አስተዋጽኦ ጉልህ ነው። እውቀት ምን ያደርጋል የሚያስፈልገው እሴት ያለው ሕይወት ነው ብለው የሚከራከሩ ሰዎች ገጥመውን ይሆናል። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበርንበት ጊዜ እውቀትና ገንዘብ ተብሎ ተከራክረንም እናውቅ እንደነበረው። እውቀት ለማህበረሰብ ለውጥ ያለውን ጥቅም ወደ ጎን አድርገን ልናይ የምንችልበት ምንም አይነት እድል የለም። እውቀትና እሴት ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው ነገር ግን በተግባር መሬት ላይ የሚውሉ ካልሆኑ ጥቅም የሌላቸው።

የተግባር ሕይወት ለእያንዳንዳችን በሚበዛበት ጊዜ የመልካም ተጽእኖ መዳረሻችን እየጨመረ ይሄዳል። የተግባር ሰው እውቀቱን እና እሴቱን ደምሮ በሌላው ጫማ ላይ ሆኖ ስለ ሰው አስቦ ሰው ሆኖ ሲገኝ ያ ትልቅ ነገር ነው። የለውጥ መንገድ። ከተለመደው መንገድ ወጣ ብሎ አስቦ ሁሉን አሸናፊ የሚያደርግ መንገድ። “ለውጥ የምቾት ቀጠና መጨረሻ ላይ የሚጀምር ነው” እንደሚባለው አባባል ግለሰቦች እሴትን፤ እውቀትን እና ተግባርን አወዳጅተው ሲኖሩ የምቾቶ ቀጣናቸውን ለቀው መኖር ይጀምራሉ። ያኔ ለተከሳሽ ፍርድ ይሰጣል። ከሳሽ ተደስቶ የሚቀበለው ፍርድ፤ በጋራ የማሸነፍ፤ ነገ ሌባ እንዳይኖር የሚያደርግ።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከማህበረሰቡ ወጥቶ ማህበረሰብን ማገልገል ያስገኘው እርካታ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የህክምና አገልግሎት ወሳኝ እና አስፈላጊ ስለመሆኑ አያጠያይቅም። በተለይም ተሽከርካሪ በማይገባበት፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በማይገኝበት፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎትም ቅንጦት በሆነበት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ህክምናን በቅርበት ማግኘት አስቸጋሪ ነው። አስቸጋሪነቱ የሚሰማው ደግሞ በህክምና እጦት የተቸገረው ሰው ወይም ደግሞ ብዙዎች በቅርበት የሚያውቃቸው ሲቸገሩ የተመለከተ ወይም ችግሩ የጠነባቸው አካባቢዎችን ሮሮ በመገናኛ ብዙሃንና በመሳሰሉት የተከታተለ ነው።

የህክምና ተቋም ፋይዳ የሚገባው በህክምና እጦት የእኔ የሚለውን ሰው የተነጠቀ ሰው ወይም የእኔ የሚለው ሰው የተሰቃየበት ብቻም አይደለም፤ ማንኛውም ሰው በህክምና እጦት መሞቱን፣ መሰቃየቱን የሰማ ሁሉ የህክምና ተቋማትን ፋይዳ ይረዳል። በህክምና ተቋም አለመኖር ሳቢያ አንዲት ወላድ ህይወቷን ብታጣ፣ በእዚህ ስሜቱ የማይነካ የለም። በህክምና እጦት ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንቶች ወዘተ ሲሰቃዩ የተመለከተም እንደዚያው።

የዛሬው የስኬት እንግዳችንም ወላጅ አባቱ በልብ ህመም ሲሰቃዩ የተሻለ ህክምና ሳያገኙ ከዚህ አለም በሞት ይለዩዋቸዋል። በዚህ ቁጭትም የህክምና ባለሙያ መሆንን ተመኝተዋል። ቀጥሎም በገጠሪቷ ኢትዮጵያ በቂ የህክምና ተቋማት በሌለበት የማገልገል ጥልቅ ፍላጎት ያድርባቸዋል። ይህ ምኞታቸው እንዲሰምርም ያለ አባት ያሳደጓቸው አርሶ አደር ወላጅ እናታቸው ብዙ ዋጋ ከፍለዋል።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ መሰረቱ የግብርና ዘርፍ ነው፤ እርሱ ከትምህርት ቤት ደጃፍ ሳይደርስ ልጆቹን አስተምሯል። አፈር ገፍቶ ፈጣሪውን ተማምኖ ለመሬት የሰጠው ዘር ፍሬያማ ሆኖ በሚያገኘው ውጤት ልጆቹን ጨምሮ አገሩን ይጠቅማል። አለፍ ሲልም ለአገር አለኝታ የሚሆኑ ልጆቹን በማስተማር የአገሪቱን ችግር ለማቅለል ይተጋል። ለዚህም ኢትዮጵያውያን ሴት አርሶ አደሮች ጉልህ ድርሻ አላቸው።

በርካታ ሴት አርሶ አደር እናቶች ሳይማሩ ልጆቻቸውን ማስተማር በመቻላቸው በማህበረሰብ ግንባታ ዘርፍ የጎላ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፤ እያበረከቱም ይገኛሉ። የዛሬው የስኬት እንግዳችንም ብዙ ሊያሳካቸው የሚችላቸው ዕቅዶች ቢኖሩትም አሁን ለደረሰበት ደረጃ ግን የወላጅ እናቱን የጎላ ድርሻ ተናግሮ አይጠግብም።

እንግዳችን ተወልዶ ባደገበት በሲዳማ ክልል ዳራ ወረዳ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአካባቢው በሚገኙ የገጠር ከተሞች ተከታትሏል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቅቆ የኮሌጅ ትምህርቱን ደግሞ በህክምናው ዘርፍ ማድረግ እንዲችል ወላጅ እናቱ ብዙ ዋጋ አስከፍሏል።

ይህ ለምን ሆነ? ይህ የሆነው ወላጅ አባቱ በህክምና እጦት ማጣቱ ነው። ‹‹አባቴ ህክምና ቢያገኝ በዚያ በሽታ አይሞትም ነበር›› የሚለው እንግዳችን፣ በዚህ ቁጭት ነው የህክምና ትምህርት የተከታተለው። ልጅን በግል ኮሌጅ ከፍሎ ማስተማር ለአርሶ አደር እናት ፈታኝ ቢሆንም፣ እናት ልጃቸውን የግል ኮሌጅ ከፍለው አስተምረዋል። ይህን ሲያደርጉ ደግሞ ከግብርና ሥራቸው በተጨማሪ ጨው፣ ዱቄትና የመሳሰሉትን መነገድ ውስጥ ጭምር ገብተው ነው። እንግዳችን በትምህርት ያገኘውን ዕውቀትም አባትም እናትም ሆነው ላሳደጉት ወላጅ እናቱና ለአካባቢው ነዋሪዎች መልሶ እየከፈለ ይገኛል።

‹‹በግል ኮሌጅ የጤና ትምህርቴን ተከታትዬ በህክምና ሙያ ማህበረሰቡን በማገልገል በአባቴ ህክምና እጦት ሳቢያ ያደረብኝን ቁጭት እንድወጣ አቅምና ብርታት የሆነችኝና ትልቅ ቦታ ያላት እናቴ ናት›› የሚለው እንግዳችን የጤና መኮንኑ አቶ ቦጋለ ጥላሁን ነው።

አቶ ቦጋለ በሲዳማ ክልል ዳራ ወረዳ የዳራ መካከለኛ ክሊኒክ ሥራ አስኪያጅና ባለቤት ነው። በተማረው የህክምና ሙያ ዘርፍ ሳይማሩ ያስተማሩትን ወላጅ እናቱን ጨምሮ እንደ ወላጅ በኃላፊነት ያሳደገውን የአካባቢውን ማህበረሰብ በሙያው የማገልገል ጥልቅ ፍላጎት ያድርበታል።

ይህን ፍላጎቱን እውን ለማድረግና ማህበረሰቡን ለማገልገልም ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በአካባቢው በሚገኝ ቀባዶ የሚባል የገጠር ከተማ በአንድ የግል ክሊኒክ ተቀጥሮ ያገለግላል። በክሊኒኩ ሲሰራም በሙያው የበለጠ ማገልገል የሚችሉበትን መንገድ ይፈልጋል።

በ2010 ዓ.ም የክልሉ መንግሥት ለሥራ ዕድል ፈጠራ



የጤና መኮንን አቶ ቦጋለ ጥላሁን

በሚል ያመቻቸውን ብድር ለመጠቀም የቀደመው አልነበረም። በወቅቱ አራት የሥራ ባልደረቦቹንና አብሮ አደጎቹን አስተባብሮ ወደ ሥራው ይገባል። ከመንግሥት ሁለት መቶ ሺ ብር ብድር በመውሰድ በትውልድ መንደሩ ዳራ ‹‹ዳራ መካከለኛ ክሊኒክ››ን ይከፍታል። በክሊኒኩም መሰረታዊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶችን ለአካባቢው ማህበረሰብ በመስጠት ሙያዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።

አቶ ቦጋለ በወቅቱ አራት የጤና ባለሙያዎች የሆኑ አብሮ አደጎቹን ይዞ ወደ ሥራ ቢገባም፣ በአሁኑ ወቅት ክሊኒኩ ሙሉ በሙሉ የራሱ ሆኗል። ለሌሎችም ባለሙያዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩበትን ሁኔታ ፈጥሯል። አሁን የሰራተኞቹ ቁጥር 22 ደርሷል። ከዚህም በተጨማሪ ክሊኒኩ ከክሊኒኩ የሚያገኙት ደምወዝ ባይኖርም በክሊኒኩ ውስጥና በዙሪያው የሻይ ቡና እንዲሁም የሱቅ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ወጣቶችን በማደራጀት ሠርተው ማደር እንዲችሉ አድርጓል።

ሳይማር ያስተማረን ማህበረሰብ በቅርበት ሆኖ ማገልገል ከፍተኛ እርካታ እንዳለው የጠቀሰው አቶ ቦጋለ፤ በተለይም ወላጅ እናቱ ሲያሳድጉዋቸው የከፈሉትን ዋጋ በማሰብ ለአካባቢው እናቶች ልዩ እንክብካቤ እንደሚያደርግም ነው ያጫወተን። አቅም የሌላቸውም እንዲሁ የነጻ ህክምና በመስጠት ጭምር ዳራ መካከለኛ ክሊኒክ በአሁኑ ወቅት በቀን ከ300 ለሚልቁ ተገልጋዮች የ24 ሰዓት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት መካከለኛ ክሊኒኩ አገልግሎት እየሰጠ ያለው በተከራየው ቤት ሲሆን፣ በቀጣይ ደረጃውን የጠበቀ መካከለኛ ክሊኒክ ለመገንባት በሲዳማ ክልል ቀባዶ ወረዳ ላይ በአንድ ሚሊዮን ብር ቦታ ገዝቷል። በዚህ ቦታ ታዲያ በቀጣይ ሁለት ዓመታት ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ መካከለኛ ክሊኒክ በመገንባት አገልግሎቱን በስፋት ለመስጠት አቅደው እየሰሩ መሆናቸውንና አሁን ካለው የሥራ ዕድል በተጨማሪ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚቻል አቶ ቦጋለ ያብራራል።

እንደ አቶ ቦጋለ ገለጻ፤ ክሊኒኩ መካከለኛ ክሊኒክ እንደመሆኑ ሙሉ ለሙሉ የላብራቶሪ አገልግሎትን ጨምሮ ማንኛውንም የህክምና አገልግሎ ይሰጣል፤ ተኝተው ለሚታከሙ ታካሚዎችም በቂ አልጋዎች አሉት። በህክምና ጉዞውም ስኬታማ መሆን ችሏል። ለዚህም የህክምና ባለሙያዎቻቸው በሙሉ ልምድ ያላቸውና ሥራቸውን ወደውና ፈልገውት የሚሠሩ መሆናቸው አስተዋጽኦ አድርጓል።

በመንግሥት ሆስፒታል የማዋለድ አገልግሎት በነጻ እንደሚሰጥ አቶ ቦጋለ ጠቅሶ፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች በድንገተኛ ለሚመጡ እናቶች ግን ክሊኒኩ አዋላጅ ነርስ ቀጥሮ አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት የማዋለድ አገልግሎት ይሰጣል ይላል። ለአገልግሎቱም ክፍያ እንደማይጠይቅ ተናግሮ፣ መጠቀሚያ ለሆኑ ቁሳቁስ ብቻ በጣም ትንሽ ክፍያ ማለት ከ100 እስከ 150 ብር ብቻ ክፍያ እንደሚጠየቅ ነው ያብራራው። ህክምናው ከክሊነኩ አቅም በላይ ሲሆን ደግሞ ወደ ሆስፒታል እንደሚልክ ተናግሯል።

ክሊኒኩ በአካባቢው ከሚገኝ የመንግሥት ሆስፒታል ጋርም መልካም የሥራ ግንኙነት አለው፤ ሙያዊ መደጋገፍ አላቸው የሚለው አቶ ቦጋለ፣ ሆስፒታሉ የተለያየ እገዛ ሲፈልግ ከባለሙያ ጀምሮ ማንኛውንም አይነት እገዛ ክሊኒኩ በተቻለ መጠን ያደርጋል። ሆስፒታሉም እንዲሁ ክሊኒኩ በሚፈልገው ሁሉ እገዛ የሚያደርግ ሲሆን፣ ተቋማቱ በመካከላቸው ጤናማ ግንኙነት መመስረት ችለዋል ሲል ያብራራል።

ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻርም ክሊኒኩ ለአቅመ ደካሞች ከመንግሥት ጋር በመተባበር የነጻ ህክምና አገልግሎት ይሰጣል። ለአገልግሎቱም በቀበሌና በወረዳ በኩል አቅመ ደካማ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይዘው ከመጡ በቀጥታ ክሊኒኩ የሚሰጠውን ማንኛውንም አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል። ችግረኞች የነጻ ፈቃድ ወረቀት ባይኖራቸው እንኳ አቶ ቦጋለ ከማህበረሰቡ የወጣ እንደመሆኑ የማህበረሰቡን ማንነት በሚገባ ያውቃልና ከወረቀት ውጭም ክሊኒኩ አገልግሎት እንዲሰጥ አርጓል።

ሁለት የጤና መኮንኖችን ሰባት የጤና ባለሙያዎችን፣ ሁለት ላብራቶሪስቶችን፣ አንድ ሚድዋይፍ ወይም ደግሞ አዋላጅ ነርስን እና ሌሎች ባለሙያዎችን ይዞ በገጠራማዋ ቀበሌ ዳራ ወረዳ ላይ የተከፈተው ዳራ መካከለኛ ክሊኒክ፣ ለአካባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ መሆን መቻሉንም አቶ ቦጋለ ይናገራል፤ በተለይም ባለሙያዎቹ በፈረቃ ሌትና ቀን ለ24 ሰዓት ሳይተኙ አገልግሎቱን የሚሰጡ እንደሆኑ ይገልጻል። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነትና ተቀባይነትን አትርፎለታል።

‹‹ጥሩ አገልግሎት መስጠት ሲቻል ውጤታማ መሆን ይቻላል›› የሚለው አቶ ቦጋለ፤ ሥራ ብለው የያዙትን ትኩረት ሰጥቶ ለለውጥና ለተሻለ አገልግሎት መሥራት ጠቃሚና አስፈላጊ እንደሆነም ነው የሚናገረው። አገልግሎት ሰጪ እንደመሆናቸውም አገልግሎቱን ፈልገው የሚመጡ ሰዎች ወደው ሳይሆን ተቸግረው ነውና ችግሩ ደግሞ መችና እንዴት እንደሚፈጠር አይታወቅም። ለዚህም ነው ክሊኒካችን በዓልን ጨምሮ ቀንና ለሊት በሩን ክፍት አድርጎ የሚጠብቀው ይላሉ።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ባለሙያዎችን በአግባቡ በመያዝ ተነሳሽነት ኖሯቸው እንዲሠሩ የተለያዩ ማበረታቻዎች አስፈላጊ እንደሆነ የሚያምነው አቶ ቦጋለ፤ በመጀመሪያ ቅጥር ሲፈጽሙም መንግሥት ከሚከፍለው ክፍያ በበለጠ ዋጋ ቅጥሩ እንደሚፈጸም ይናገራል። ለአንድ ባለሙያ ከ7500 እስከ 9000 ብር ክሊኒኩ ይከፍላል ይላል። በተመሳሳይ ደግሞ በመንግሥት ሆስፒታሎች የሚገኙ የተለያዩ ስልጠናዎች በግል ክሊኒክ ውስጥ የማይገኙ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምሳና ቁርስን ጨምሮ የሻይ ቡና አገልግሎት በክሊኒክ ውስጥ እንደሚሰጥ ነው የሚገልጸው። የሞባይል ካርድ በመሙላትም እንዲሁ የሥራ ተነሳሽነትን የሚጨምሩ ተግባራትን እያከናወኑ እንደሆነም አጫውቶናል።

እንደ እሱ ገለጻ፤ ሰዎች ከህመማቸው እንዲፈወሱና ጤናማ እንዲሆኑ 24 ሰዓት በሩን ክፍት አድርጎ የሚሠራው ዳራ መካከለኛ ክሊኒክ፣ ከሁሉ አስቀድሞ አገልግሎት የሚሰጠው ለማን እንደሆነ ማህበረሰቡን ጠንቅቆ የሚያውቅ በመሆኑ በርካታ ሙያዊ ድጋፎችን ያደርጋል። ለአብነትም አንድ እናት ራሴን ያዞረኛል ብላ ከመጣች ገንዘብ ከፍላ ግሉኮስ እንድትወስድ ከማድረግ ባሻገር በቀላሉ ሽንኩራ በልታ ጤናዋን ማስተካከል የምትችል መሆኑን በማስረዳት ክሊኒኩ ከሚያገኘው ገቢ ባለፈ ሙያዊ ምክሮችን በመለገስ የማህበረሰቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ እየሠራ ይገኛል።

ለህክምና አገልግሎት አስፈላጊ የተባሉ ቁሳቁስን በተለይም መድሃኒቶችን ክሊነኩ ከሶስተኛ ወገን የሚያገኝ መሆኑ ለሥራው ፈታኝ እንደሆነ ነው አቶ ቦጋለ የሚያመለክተው፤ የመንግሥት ሆስፒታሎችም ሆኑ የግል ክሊኒኮች ዓላማቸው አንድ በመሆኑና ሁሉም ህብረተሰቡን የሚያገለግል እንደመሆኑ መድሃኒት በቀጥታ ከመንግሥት ማግኘት ቢቻል መልካም እንደሆነም ያስገነዝባል። ይህ ሲሆን የተቀላጠፈ እና የማህበረሰቡን አቅም ያገናዘበ አገልግሎት መስጠት እንደሚቻል ነው የሚገልጸው። ይሁንና በአሁኑ ወቅት ማንኛውንም መድሃኒት ከመንግሥት ተቋማት ውጭ ነጋዴዎች ተጨማሪ ዋጋ ከፍለው ለራሳቸው ደግሞ ከሁለት እስከ ሶስት ብር ትርፍ ይዘው እየሠሩ መሆኑን ይናገራል። ይህ ስራውን ፈታኝ እንዳደረገው ይጠቁማል።

ወደፊት አቅመ ደካሞችን በተለይም በገጠር ውስጥ የሚኖሩትን የመንጎብኘትና በተለያዩ ዘርፎች የማገዝ ዕቅድ እንዳለው የጠቀሰው አቶ ቦጋለ፤ ከዕቅዱ አንዱም በከተሞች የሚገኙ ሰዎች የማይጠቀሟቸውን አልባሳትና መጫሚያዎች እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁስ በማሰባሰብ ለተቸገሩ ወገኖች ማድረስ መሆኑን ይናገራል። መኖሪያ ቤታቸው ለመኖሪያ ምቹ ያልሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለይቶ ቤት የመሥራት ዕቅድ ይዘው እየሰሩ መሆናቸውን ያብራራል።

ሰዎች በሚያውቁትና በሚያውቃቸው የማህበረሰብ ክፍል ውስጥ ሆነው የሚሰጡት አገልግሎት ትልቅ እርካታን እንደሚሰጥ የሚያስገነዝበው አቶ ቦጋለ፤ እርሱ በሙያቸው ማህበረሰቡን ማገልገል በመቻሉ ትልቅ ደስታና እርካታ ማግኘቱን ገልጾ፤ በተለይም ወደ ክሊኒኩ ሄደው መታከም ላልቻሉ ሰዎች ቤት ለቤት በመሄድ የሚሰጠው ህክምና ትልቅ እርካታ እንደሚሰጠው ይጠቁማል።

አቶ ቦጋለ እንዳለው የተለያዩ የህክምና ቁሳቁስን ይዞ እየሰራ ያለው ዳራ መካከለኛ ክሊኒክ በተለይም ራሳቸውን ችለው መንቀሳቀስ ለማይቹሉ ታካሚዎች ባሉት ሁለት ሞተር ሳይክሎች ታማሚው ቤት ድረስ በመሄድ ህክምና ይሰጣል። የህክምና አገልግሎት አግኝተው ወደ ቤታቸው መመለስ ካልቻሉም እንዲሁ ወደ ቤታቸው የመመለስ ሥራ ይሠራል።

አጠቃላይ በወላጅ አባቱ ህክምና አጥቶ መሞት በመቆጨት ለተገኘበት የማህበረሰብ ክፍል የህክምና አገልግሎት በመስጠት ለብዙዎች የተረፈው አቶ ቦጋለ፤ በአሁኑ ወቅት መካከለኛ ክሊኒኩ ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ ከሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር በላይ ካፒታል ማፍራት መቻሉን ተናግረዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የእውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር እያስገኘ ያለ ፕሮጀክት

መላኩ ኤርሴ



በኢትዮጵያ ሁለተኛው የፍጥነት መንገድ ከሞጆ ተነስቶ፣ መቂ፣ ባቱና አርሲ ነጌሌን ታኮ ሀዋሳ ይደርሳል። ይህ ፕሮጀክት በአገሪቱ የወጪና ገቢ ንግድ ላይ የራሱ የሆነ አወንታዊ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ የሚጠበቅ ትልቅ ፕሮጀክት ነው። 202 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው ግንባታ ከሞጆ - መቂ፣ ከመቂ - ባቱ፣ ከባቱ - አርሲ ነጌሌ፣ ከአርሲ ነጌሌ - ሀዋሳ በሚል በአራት ኮንትራቶች የተከፈለ ነው።

ግንባታው በ2008 ዓ.ም ህዳር ወር ላይ ሲጀመር በ2013 ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ግብ ተቀምጦለት ነበር። ነገር ግን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ሙሉ ለሙሉ ሊጠናቀቅ አልቻለም። የመንገዱ አካል የሆኑት ክፍል አንድ ሞጆ - መቂ እና ክፍል ሁለት መቂ - ባቱ ግንባታቸው ተጠናቅቆ ለትራንስፖርት አገልግሎት ክፍት መደረጋቸው ይታወቃል። ክፍል ሶስት ባቱ - አርሲ ነጌሌ 57 ኪሎ ሜትር እና ክፍል አራት የአርሲ ነጌሌ - ሀዋሳ 52 ኪሎ ሜትር መንገድ ግንባታ እየተካሄደ ይገኛል። የሞጆ ሀዋሳ የመንገድ ፕሮጀክት በአጠቃላይ እና አርሲ ነጌሌ ሀዋሳ ፕሮጀክት በተለይ ዘመኑ የደረሰበት የመንገድ ግንባታ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ የተደረገበት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

የፕሮጀክቱ አራተኛው ክፍል የሆነው የአርሲ ነጌሌ - ሀዋሳ የመንገድ ፕሮጀክት በቻይና ኮሙኒኬሽን ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን እየተገነባ ያለ ሲሆን፤ የማማከር ስራውን ደግሞ ቤጂንግ ኤክፕሬስዌይ ሱፐርቪዥን እና ውሃን ጂኦክ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልተንሲ የተሰኙ ድርጅቶች በጋራ እየተገበሩት ይገኛሉ።

መንገዱን ለመገንባት የሚውለው ወጪ በኢትዮጵያ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ የሚሸፈን ነው። ከመንገዱ አጠቃላይ ወጪ ውስጥ 85 በመቶ በቻይናው ኤግዚም ባንክ የሚሸፈን ሲሆን፣ 15 በመቶ በኢትዮጵያ መንግስት የሚሸፈን ነው። መንገዱ 31 ነጥብ 6 ሜትር የጎን ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ የሚገነባ ነው።

ግንባታው በቅርቡ በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የፕሮጀክት አመራሮችና ሠራተኞች ትምህርታዊ ጉብኝት ተደርጎበታል። የአርሲ ነጌሌ - ሀዋሳ የመንገድ ፕሮጀክት ከቅድመ ግንባታ ጀምሮ የመንገድ ግንባታው ዘርፍ አሁን የደረሰባቸው ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ የተደረገበት መሆኑን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ፕሮጀክቱን የጎበኙት የአስተዳደሩ ባለሙያዎች እና አመራሮች እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱን እየገነባ የሚገኘው ድርጅት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመንገድ ግንባታውን እያከናወነ መሆኑን ተመልክተዋል። ፕሮጀክቱ በሌሎች ፕሮጀክቶች ለተሰማሩት የፕሮጀክት አመራሮችና ሰራተኞች አዲስ እውቀት ያስጨብጣል።

ጉብኝቱ ላይ ከተሳተፉት መካከል ኢንጂነር ቤዛዊት ግርማ አንዷ ናት። ኢንጂነሯ በመንገድ አስተዳደሩ የጥናት ቡድን ውስጥ ትሰራለች፡፡ ፕሮጀክቱ በርካታ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የተተገበረበት መሆኑን መመልከቷን ትናገራለች። የአርሲ ነጌሌ ሀዋሳ የመንገድ ግንባታ በታላቁ የስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚካሄድ ነው። የሻላ እና ሀዋሳ-ሀይቆችን ጨምሮ በአካባቢው በርካታ ሀይቆች የሚገኙበት ነው። በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎች ለግንባታ አመቺ ያልሆኑ ጂኦሎጂካል ክስተቶች ይስተዋልባቸዋል። በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ አፈር ለመደርመስና ለመሰንጠቅ ተጋላጭ ነው። በዚህ አካባቢ የሚገኝ መሬት ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ሲያገኘው የመደርመስ ባህሪይ አለው።

እንዲህ አይነት አፈር ላይ የሚሰሩ ግንባታዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ይጠይቃሉ። ይህንን ችግር ለመለየት እና በቅድሚያ ለመከላከል ተቋራጩ የተጠቀመው ቴክኖሎጂ በመንገድ ግንባታው ዘርፍ ዓለም የደረሰበትን ደረጃ አመላካች መሆኑን መመልከቷን ነው ኢንጂነር ቤዛዊት ያመለከተችው።

የፕሮጀክቱ ትግበራ ከመጀመሩ አስቀድሞ መልክአ ምድራዊ ካርታ እና ሳይት ምርመራን መሰረት በማድረግ የፕሮጀክቱ ግንባታ በሚካሄድበት ክልል ውስጥ የሚገኙ አስቸጋሪ ቦታዎችን የመለየት ስራ ተሰርቷል። በልየታ ሂደት ረግረጋማ አካባቢዎች ተገኝተዋል፤ ተቋራጩ በእነዚህ ረግራጋማ እና ለግንባታ አመቺ ባልሆኑ አካባቢዎች በተገኙ መረጃዎች ዙሪያ ተጨማሪ ጥናቶች እንዲካሄዱ ቻይና ድረስ በመላክ በመረጃው ላይ ተጨማሪ ምርመራ መካሄዱን በትምህርታዊ ጉብኝቱ ወቅት ከተሰጠው ማብራሪያ ኢንጂነሯ ተረድታለች።

እንደ ቤዛዊት ገለጻ ኮንትራክተሩ የምርመራ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌክትሪክ እና የራዶን ፍተሻዎችን በማድረግ የጂኦሎጂካል ሁኔታዎችን በጥልቀት በመቃኘት ችግሩን ለይቷል። የተለየ ሁኔታ በሚታይባቸው አካባቢዎች ጥልቅ ቁፋሮ እና የጂኦሎጂካል ምርመራዎችን በማካሄድ ችግሮችን ለመለየት ጥረት አድርጓል። ከብዙ ምርመራዎች በኋላ ፕሮጀክቱ በሚገነባባቸው አካባቢዎች ውስጥ በርካታ ሊሰነጠቅ እና ሊደረመስ የሚችል አፈር ያለባቸው አካባቢዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። እነዚህን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የተሻለ የግንባታ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ እና አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ወስዷል።

ሊደረመስ የሚችል አፈር የራሱ የሆነ ባህሪያት ያሉት ሲሆን፣ እንደዚህ አይነት አፈር የተለያዩ አደጋዎችንም ሊያስከትል ይችላል፤ በተለይም ግንባታው ከተካሄደ በኋላ መንገዱ የመንሸራተት እድሉ ከፍተኛ ነው። እንዲህ አይነት አፈር ብዙ የተደከመበትን፣ ገንዘብና ጉልበት የወጣበትን ፕሮጀክት በአጭር ጊዜ ከጥቅም ውጪ ሊያደርግ ይችላል። ይህንን ችግር ለመከላከል ተቋራጩ የተለያዩ የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰዱን በጉብኝቱ ወቅት መረዳቷን ኢንጂነር ቤዛዊት ትናገራለች።

ከነዚህ የመፍትሄ እርምጃዎች አንዱ ሊደረመስ የሚችለውን አፈር ሙሉ በሙሉ እንዲወገድ በማድረግ ለግንባታ አመቺ በሆኑ ቁሳቁስ ተተክቷል። ሌላኛው እርምጃ ደግሞ ከላይ ያለውን የመደርመስ ባህሪይ ያለውን አፈር በማንሳት ከስር ያለውን አፈር በሀይል መጠቅጠቅ ነው። በዚህ ግንባታም ተጨማሪ የመፍትሄ እርምጃዎችን በመውሰድ ሊደረመስ የሚችል አፈር የማስተካከል ስራ ተሰርቷል።

የአፈር መሰንጠቅ መንገዱ በሚገነባበት አካባቢ ከሚስተዋሉ ችግሮች አንዱ ነው። በተለይም አርሲ ነጌሌ አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ የመሬት መሰንጠቆች በስፋት ይስተዋላሉ። እነዚህ ችግሮች በቀጣይ በመንገዱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ አመላካች ነበርናም ችግሩን ለመቀነስ የሚያስችል የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ያስፈልግ ነበር።

እንደነዚህ አይነት ችግሮችን በቅድሚያ ለመከላከል ተቋራጩ የተጠቀማቸው ቴክኖሎጂዎች በቀጣይ በአገራችን በሚካሄዱ የመንገድ ግንባታዎች ጥቅም ላይ ቢውሉ መሰል ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል መሆኑን ኢንጂነር ቤዛዊት አብራርታለች። ዘመኑ የደረሰባቸው እንዲህ አይነት ቴክኖሎጂዎች ወደ አገሪቱ መግባታቸው በስራ ላይ ያሉ እና በቀጣይ ወደ ስራ የሚገቡ ተቋራጮች ጥሩ እውቀት እንዲቀስሙ እድል ይፈጥራል።

ግንባታው በሚካሄድበት ገጸ ምድር ላይ ብቻ ሳይሆን ከርሰ ምድር ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮችን ተቋራጩ በቅድሚያ በመለየት ችግሩን ለመቀነስ ከግንባታው አስቀድሞ የመፍትሄ እርምጃ መውሰዱ ለአገር በቀል ተቋራጮች ትልቅ ትምህርት የሚሆን ነው የምትለው ደግሞ ትምህርታዊ ጉብኝቱ ላይ የተሳተፈችው ሌላኛዋ ኢንጂነር ሀያት አለማ ናት። ኢንጂነሯ በከርሰ ምድር ውስጥ የሚከሰቱ ክስተቶችን ለማስቆም ምንም እንኳ ሰው ሰራሽ የምህንድስና እርምጃ ሊወሰድ ባይችልም የአደጋን ኪሳራ ለመቀነስ የመከላከያ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚቻል ተቋራጩ በተግባር አሳይቷል ትላለች።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተለመዱ ቴክኖሎጂዎች በስራ ላይ ውለው ማየቷን የምትናገረው ሀያት፤ በአገራችን ለመንገድ ስራዎች ትልቁ እንቅፋት እየሆነ ያለው የመሬት መንሸራተት መሆኑን ትጠቅሳለች። ይህ ችግር በሚገነቡ መንገዶች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ተቋራጩ በቅድሚያ ጥናት በማካሄድ ቀድሞ ለችግር ተጋላጭ ሊሆን ይችላሉ ብሎ ባሰባቸው ቦታዎች ላይ ጥናቶችን በማካሄድ መሬት መንሸራተት እና መሰንጠቅ ሊከሰት የሚችልባቸውን ቦታዎች ለመለየት የተጠቀመው ቴክኖሎጂ ለሌሎች ተመሳሳይ ችግር ለሚስተዋልባቸው የመንገድ ግንባታዎችም የሚጠቅም ትልቅ ተሞክሮ ነው። ቴክኖሎጂው መንገዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመሬት መንሸራተት ምክንያት ከጥቅም ውጪ እንዳይሆን ይረዳል።

ሀያት እንደምትለው ተቋራጩ የሚደረመስ መሬት ለማከም ከተጠቀማቸው ቴክኖሎጂዎች ባሻገር በመንገዱ ላይ የሚገነቡ ድልድዮችን ለመገንባት ዘመኑ የደረሰባቸውን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞባቸዋል። ለድልድይ ግንባታዎችም እንዲሁ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀሙ ባሻገር በዝናብ ወቅት ከድልድዮቹ ወደ ውሃ ማፋሰሻዎች የሚገባው ውሃ አካባቢውን በማይበክል እና የድልድዩን ደህንነት በማይጎዳ መልኩ እንዲወገድ የሚያስችል ስራ አከናውኗል። የተለመደው የውሃ ማፍሰሻ ዘዴ ቀጥ ያለ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴ ሲሆን፤ ይህም ለአካባቢ ብክለት መንስኤ ሲሆን ነበር።

እንዲህ አይነት ማፋሰሻዎች የሞጆ ሀዋሳ አይነት የጽዳት ሰራተኞች በሌሉባቸው ረጃጅም መንገዶች ላይ ሲገነቡ ማፋሰሻው በቀላሉ በቆሻሻ ይዘጋል። በድልድዮቹ ላይ ውሃ በመሰብሰብ የድልድዩ ደህንነት ላይ ችግር የሚያስከትል ነው። አሁን የአርሲ ነጌሌ ሀዋሳ ፕሮጀክት ላይ ተግባራዊ የተደረገው ግን ውሃ እንዳይሰበሰብ ብሎም በዚህ ምክንያት ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመቀነስ የውሃ ማስወገጃ አቅጣጫ ወደ አግድም እንዲሆን መደረጉን ታነሳለች።

በአጠቃላይ የመንገድ ፕሮጀክቱ በአይነቱ ልዩ ከመሆኑ ባሻገር ከቅድመ ግንባታ ጀምሮ እስከ ፕሮጀክት ትግበራ ድረስ ዓለም የደረሰበት ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የዋለበት እንደመሆኑ በዘርፉ ለተሰማሩ የፕሮጀክት አመራሮችና ሰራተኞች የእውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያስገኝ መሆኑን ያብራሩት የአስተዳደሩ አመራሮችና ሰራተኞች፤ ይህ ፕሮጀክት በሌሎች ፕሮጀክቶች ለተመደቡ አመራሮችና ሰራተኞች አዳዲስ እውቀት፣ ልምድና ተሞክሮ የሚያስገኝ መሆኑንም ተናግረዋል። በጉብኝቱ ወቅት ያገኙትን እውቀት፣ ልምድ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ በመጠቀም በቀጣይ በሚሰሯቸው አገራዊ ፕሮጀክቶች ላይ በመተግበር የራሳቸውን አሻራ ለማሳረፍ እንደሚሰሩ ጠቁመዋል።

በአገራችን በድልድይ ግንባታና አስተዳደር ዘርፍ የእውቀት ሽግግር በማምጣት በቀጣይ ሌሎች የዓለም አገሮች የደረሱበት የእድገት ደረጃ ለመድረስ በር የሚከፍት መሆኑን ያስረዱት ባለሙያዎቹ ከተሰማሩት ባሻገር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ወደ ግንባታው አካባቢ በመሄድ እውቀት፣ ልምድና ክህሎት እንዲቀስሙ ሊደረግ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አሸባሪው ሕወሓት - ከጦረኝነት አዙሪት ነጻ ያልወጣው ነጻ አውጪ

ኢትዮጵያ ታሪኳ በእጅጉ ከጦርነት ጋር የተቆራኘ ነው፤ እንደ አገር ጸንታ ለመቆየቷም ይሄው ታሪኳ እንደ አንድ ማጽናኛ ተደርጎ የሚነሳባቸው አጋጣሚዎችም በርካታ ናቸው። በውስጥ ሊያፈርሷትና ሊከፋፍሏት የተነሱ ተላላኪ ኃይሎችን ቆንጥጣ አደብ የምታስይዘው፤ ከውጭ ሊወርሯት ቋምጠው ሉዓላዊነቷን ደፍረውና ድንበሯን አቋርጠው ለመግባት የሞከሩ ወራሪና ጠላት ኃይሎችንም ድባቅ መትታ የመለሰችው በጦርነት መሆኑ ይሄን ብሂል ከፍ ያደርገዋል።

ለዚህ የጦር አውድ ድል አድራጊነቷ ደግሞ የውስጥ አንድነቷ፤ የሕዝቦቿ በጋራ ቆሞ ለጋራ አገራቸው መታገልና አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ የመክፈል ከፍ ያለ የአርበኝነት ስሜት ተኪ የሌለው ነው። ለዚህም ነው የውስጥ ተላላኪዎችም ሆኑ የውጭ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለማዳከም፤ አንድነቷን ለመከፋፈል፣ ሕዝቦቿን ለመነጣጠል በጋራም፣ በተናጥልም ሲደክሙ የሚታየው።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያን ለመበተን፤ ሕዝቦቿን ለማዋረድ ተልዕኮ ተቀብለው ከሚሰሩ የውጭ ተላላኪ ባንዳዎች መካከል ሕወሓትና መሪዎቹ ተጠቃሽ ናቸው። ሕወሓት በነጻ አውጪ ስም ተመስርቶ ነጻ አወጣዋለሁ ያለውን የትግራይ ሕዝብ ነጻ ወጥተሃል ባለው ማግስትም ሆነ 27 ዓመት ሙሉ የትግራይን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላውን ኢትዮጵያ ሲያስተዳድር በቆየበት ጊዜ ሁሉ የነጻ አውጪነት ስያሜውን መቀየር ያልቻለ ድርጅት ነው። ይህ ደግሞ ያለምክንያት አልነበረም። ይልቁኑ ቡድኑ ሕዝብን ነጻ አውጥቻለሁ ብሎ ቢያምንም፤ እርሱ ግን ነጻ ባለመውጣቱ እና የተሰጠውን የአፍራሽነት ተልዕኮ ባለመፈጸሙ ነጻ ያልወጣ ነጻ አውጪ ስለሆነ እንጂ።

ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ(ሕወሓት) ወይም የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር(ትህነግ) በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ ስያሜውን ተሸክሞ ወደ ጫካ ሲወጣ፤ ተልዕኮው የትግራይን ሕዝብ ነጻ በማውጣት ስም የትግራይን ወጣት ለጦርነት አሰልፎ የኢትዮጵያን ጠላቶች ጉዳይ ማስፈጸም ነበር። ለዚህ ተልዕኮው ማስፈጸሚያ ዘርፈ ብዙ ድጋፍና ጥቅማጥቅም እየተሰጠው በትግራይ ሕዝብ መስዋዕትነት ላይ እየተረማመደ ለሥልጣን በቃ። ይህ ሲሆን የትግራይ ሕዝብ በመስዋዕትነቱ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር በቅቷል ተብሎ ስለሚታሰብ ነጻ ወጥቷል ማለት ይቻላል። ነጻ ያወጣ ድርጅት ደግሞ ከነጻነት ማግስት ስለ ልማትና ዴሞክራሲ እንጂ ስለ ሌላ ነጻ መውጣት እያሰበ ጦር




ማደራጀት፤ የጦርነት አታሞ መደለቅ አይጠበቅበትም ነበር።

አሸባሪው ሕወሓት ግን እንደ ትናንቱ ሁሉ የትግራይን ሕዝብ በሌላ ገጹ ነጻነቱን ነፍጎ ነጻ የመውጣት ምስል እየሳለበት፤ ለራሱ ነጻ የሚወጣበትን ፕሮጀክት ወደመተግባር ገባ። ምክንያቱም ነጻ የሚወጣው በትግራይ ሕዝብ ነጻነት ስም የተሰጠውን አገር የመበታተን ተልዕኮውን ሲፈጽም ስለሆነ ነው። ለዚህም ነው፣ ብዙ ሊደረግለት የሚገባውን የትግራይን ሕዝብ የኢኮኖሚ ነጻነቱን ነፍጎ እና ዴሞክራሲያዊ መብቱን አፍኖ ለችግር ጊዜ መሸሸጊያ በሚሆነው መልኩ እያዘጋጀው፤ በሌላ በኩል ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ለመበተን የሚያስችለውን ሴራ ሲጎነጉን 27 ዓመታትን ያሳለፈው።

ሆኖም ይሄን ሴራ የተረዱት ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ከመፍረሷ በፊት ቡድኑን ቀድመው አስወገዱ፤ ቡድኑም የሴራው ድርሰት መቋጫ ባለማግኘቱ እየተብሰለሰለ ለችግር ጊዜ ወዳመቻቸው የትግራይ ሕዝብ "ላለማህ መጣሁ" በሚል ምክንያት ሄዶ ተወሸቀበት። አካሄዱም ትግራይን ለማልማት ሳይሆን ነጻ ያልወጣበትን አገር የማፍረስ ተልዕኮውን ለመፈጸም ነበርና፤ ሌላ ነጻ እወጣበታለሁ ብሎ ያሰበውን ጦርነት ማስነሳትን የመጨረሻው አማራጭ አደረገ።

እናም የሰሜን እዝ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ላይ ጥቃት በመፈጸም ጦርነት እንዲቀሰቀስ አደረገ። ይሄ በሽንፈት ሲደመደምበት፤ ሌላ አማራጭ ያለውን ወረራ ወደ አፋርና አማራ ክልል አደረገ። ይሄም በተመሳሳይ አንገቱን የደፋበት ሆነ።

አሁንም በሕይወት እያለ የበላው የጥፋት ተልዕኮ ማዕድ እንቅልፍ አይሰጠውምና ሌላ ዙር ጦርነትን እየተመኘ፤ ሕዝቡንም ነጻ የምትወጣውም ሆነ ሕልውናህ እውን የሚሆነው በጦርነት ብቻ ነው እያለ አሳሩን እያበላው ይገኛል።

በነጻዋ ምድር ኢትዮጵያ የነጻ አውጪን ለምድ ደርቦ ነጻ ለማውጣት ሳይሆን ነጻ ለመውጣት እየጣረ ያለው አሸባሪው ሕወሓት፤ እነሆ ዛሬም ድረስ ከጦርነት እሳቤ ነጻ ሳይወጣ ለነጻነቱ እየተውተረተረ ነው፤ ኢትዮጵያውያንም ለአንድነትና ክብራቸው እየታገሉት ይገኛሉ። ሆኖም ነጻ ያልወጣው ማንነቱን ነጻ ለማውጣት የሚያደርገው መንፈራገጥ ሕዝቦችን ለባሰ ሰቆቃ እና እልቂት የሚያጋልጥ እንደመሆኑ አሁንም ቆም ብሎ ሊያስብ፤ ለጥፋት ተልዕኮው ሲል የትግራይን ሕዝብም ሆነ ታላቋን አገር ኢትዮጵያ ወደሌላ ቀውስ ከመገፋፋትም ሊቆጠብ ይገባል።

---


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


---

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# አሁንም መፍትሔን የሚሻው የኑሮ ውድነት

በእምነት

በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየጨመረ የሚገኘው የሸቀጦች ዋጋ መናርና የኑሮ ውድነት ለብዙዎች ፈተና እየሆነ መምጣቱ እየተነገረም እየታየም ያለ ሃቅ ነው። የእያንዳንዱ ሸቀጥ ዋጋም አይን ጨፍኖ ሲነቃ ያህል ሽቅብ እየወጣ ነው። የኑሮ ውድነቱን አባባሽ ምክንያቶች እንዳሉት ሁሉ አርተፊሻል የኑሮ ውድነት የሚፈጥሩ እንዳሉም መዘንጋት የለበትም። የኑሮ ውድነት እንዲባባስ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል ደግሞ በአገሪቱ ያለው የሰላም እጦት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተስተዋሉ ያሉ የሸቀጦች ዋጋ መናር እንዲሁም በዩክሪንና ሩስያ መካከል ያለው ጦርነት ተጠቃሽ ነው። ይሁን እንጂ ይሄንን ዓለም አቀፍም ሆነ አገራዊ ምክንያት የሚያባብሱ፣ እጥረት እንዲፈጠር ምርት የሚደብቁ፣ ዋጋ ሲተምኑና ሲያስተምኑ የሚውሉ ደላሎችና ነጋዴዎች ደግሞ መኖራቸው ይታወቃል።

አዎ ዛሬ ላይ ኑሮ ከብዷል አይንን ጨፍኖ እስኪገለጥ ድረስ የኑሮው ሁኔታ የማይደረስበት ደረጃ ላይ እየደረሰ የእቃዎችም ዋጋ እያሻቀበ ነው። ትላንት አንድን እቃ ለመግዛት ያወጣነው ገንዘብ ዛሬ ላይ ምንም የማይገዛ እየሆነ የመጣበት ሁኔታ እየተስተዋለ ነው። ይህ ደግሞ ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ራስ ምታት ሆኗል። የዋጋ ጭማሪው በተለይ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ሸማች በሆነባቸው የከተሞች አካባቢ የዜጎች እለታዊ ኑሮ እንዲከብድ አድርጓል።

ድሮ ድሮ ኑሮ ከባድ የሚሆነው ዝቅተኛ ገቢ ላለው የመንግስት ሰራተኛ እንዲሁም ከዛ በታች ላሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ይባል ነበር፣ ዛሬ ላይ ግን የመንግስት ሰራተኛውም ሌላውም የእለት ስራ የሚሰራውም ብቻ በአጠቃላይ ሁሉንም እየፈተነና እየተፈታተነ ነው። በቅርቡ በልቶ ማደር ብርቅ የሚሆን እስኪመስል ድረስ አስፈሪ ሆኗል።

ዛሬ ላይ የሚገኘው ገቢና ወጪ ፍጹም አይገናኝም "ገቢ በማንኪያ ወጪ ባካፋ" ይሉት አይነት ሆኗል። እና ወጪና ገቢ ካልተመጣጠነ ደግሞ ነገ ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመቱ ቀላል ነው። የቤት ኪራይ፣ ቀለብ፣ የልጆች ትምህርት ቤት፣ ልጆች ትምህርት ቤት ሲሄዱ የሚይዙት ምሳ፣ ትራንስፖርት፣ ልብስ፣ ጫማ፣ የቤት ሰራተኛ፣ ውሃና መብራት ኧረ ምኑ ቅጡ የወጪው አይነት ተዘርዝሮ አያልቅም። ምን አለፋችሁ ሰው ሁሉ ወረድ ብዬ ልኑር ቢል እንኳን እነዚህ ወጪዎች እጅግ የናሩ በመሆናቸው በፍጹም ከወር ገቢ ጋር ተመጣጥነው ማኖር አያስችሉም። እዚህ ላይ አንድ የሚያስማማን ነገር እንዳለ አምናለሁ። የኑሮ ውድነቱ ዓለም አቀፍ ነው የሚለው። ከውጭ የምናስገባው እቃ የዶላር እጥረት አጋጠሞታል የሚለው። ይሄ በሁሉም መልኩ ተቀባይነት ያለው ነው። ነገር ግን በአገራችን መሬት በወንዛችን መስኖ የለማው ሽንኩርት በኪሎ 50 ብር የደረሰው ለምንድነው የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት ያስገድዳል። ሀይባይ ተቆጣጣሪስ አለ ብለን እንድንጠይቅም ያደርጋል። ለነገሩማ በቅናሽ ዋጋ ምርቶችን የሚያቀርብልን የሸማቾች ማህበር ነበረን፣ የሸማቾችን መብት የሚያስከብር መንግስታዊ ተቃሚም ተቋቁሞ ነበር አሁን ግን የት ይሆን ያሉት ከማለት አገልግሎት ሲሰጡ አይታዩም። መንግስትም ክትትል ቁጥጥር ቅጣትና እርምጃ የሚባሉ ቃላቶች የታከቱት ይመስላል፤ ሁሉም እንዳሻቸው ሆነዋል ልበል?

ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ መንግሥት በቅርቡ ያደረገው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖ በኑሮ ውድነቱ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳረፈ ነው። ይህንን ደግሞ ነዋሪዎች እና የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች የሚናገሩት ሀቅ ነው።

የበርካታ አገራት ፈተና የሆነው የኑሮ ውድነት በያዝነው አውሮፓውያኑ 2022 በርካታ የዓለማችን አገራት ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት አጋጥሟቸዋል። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ባለፈው ወር በዩናትድ ኪንግደም በ30 ዓመታት ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የኑሮ ውድነት በ7 በመቶ ጨምሮ ተመዝግቧል። ኬንያውያንም በምግብ ዘይት፣ በእህል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ጭማሪ እጅጉን እየተማረሩ ስለመሆኑ ያትታል። የእኛን ሁኔታ ግን ለየት የሚያደርገው ኢኮኖሚያችን ዓለም አቀፉን ጫና በአገር ውስጥ ያለው ጦርነት ወደኋላም ሳብ ካልን ኮሮና ቫይረስ እያደረሰበት ያለውን ተጽዕኖ መቋቋም አለመቻሉ ነው። ህብረተሰቡ ቀድሞም ቢሆን ሕይወቱን ይገፋ የነበረው ከእጅ ወደአፍ በሚባል አይነት ሁኔታ ስለነበር አሁን ላይ እንደዚህ ያለውን መዓት መሸከም የሚችልበት ጫንቃ አጣ።

ከቀናት በፊት የብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ምክር ቤት ባወጣው መግለጫ፤ አሁንም በኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ፈተና እየገጠመን እንደሆነ አትቷል። ይህ የሆነው ደግሞ ከዋጋ ግሽበት ጋር በተገናኘ ሲሆን፥ ከአምናው የሚያዝያ ወር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ግሽበቱ 36 ነጥብ 6 በመቶ መድረሱንም ምክር ቤቱ መናገሩ የሚታወስ ነው። ነገሩን ይበልጥ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እየተመዘገበ ያለው የምግብ ነክ ሸቀጦች ላይ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምን ያህሉን ሰው ፈተና ውስጥ እንደሚጨምረን ቤት ይቁጠረው።

የኑሮ ውድነቱን ለመቆጣጠር ምን እርምጃ መወሰድ አለበት? የሚለው ደግሞ የሁሉም የሁላችንም ጥያቄ ነው፤ አዎ የዋጋ ግሽበቱን ተከትሎ እየመጣ ያለው የኑሮ ውድነት በዚሁ ከቀጠለ ምናልባት እንደ ህዝብ መቀጠላችን ጥያቄ ምልክት ውስጥ ሊገባ ይችላል።

መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ አልያም ለመቆጣጠር፤ በተለይም ምርት በማከማቸት ዋጋ እንዲንር ምክንያት በሚሆኑ ነጋዴዎች ላይ በሚወሰድ እርምጃ፣ በሸማች እና አምራች መካከል በመግባት የኑሮ ውድነት የሚያስከትሉ ነጋዴዎች ላይ በቂ እርምጃ አልተወሰደም የሚሉ ቅሬታዎች ይነሱበታል።

በመሆኑም መንግስት በአሁኑ ወቅት ሊወስድ ይገባል ብዬ የማምነው ምንልባትም ባለሙያዎችም የሚያምኑበት መንገድ የምርት ዋጋ ከፍ የሚለው ፍላጎት ከአቅርቦት ሲያንስ በመሆኑ መሠረታዊ አቅርቦቶች በገበያ እንዲኖሩ መደገፍ፤ ተጨባጭ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በአንድ ሌሊት የምርቶች ዋጋ የሚጨምርበት አጋጣሚ መቆጣጠር ፤ ትላንት የነበረ ዕቃ በአንድ ሌሊት ጠፍቶ አደረ ሲባል ምርቱን ደበቀው ዋጋውን ከፍ አድርገው መሸጥ የሚፈልጉ ሰዎች መኖራቸውን በመገንዘብ ከፍ ያለ እርምጃ መውሰድ፤ በሌላ በኩል በምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች የሚነሳውን የአገሪቱ የወጪና የገቢ ንግድን ማጣጣሚያ መንገድን በጥሞና ሰምቶ ተግባራዊ ማድረግ።

ከዚያ ባለፈ ግን እንደ አንድ አገር ህዝቦች እርስ በእርሳችን መረዳዳት ነጋዴውም ቢሆን ነግዶ አትርፎ የሚበላው ሰው ሲኖር መሆኑን ተገንዝቦ በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋን ማቅረብ። በክልሎች መካከልም ያለው ግንኙነት የመረዳዳት እርስ በእርስ የመደጋገፍ አንዱ የሌለውን ሌላው ካለው በመረዳዳት ይህንን ጊዜ ተባብሮ ማለፍና በተለይም እንድንወድቅ የሚመኙልንን ጠላቶቻችንን ማሳፈር ከሁላችንም የሚጠበቅ ነው። አበቃሁ!

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የህይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆአስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## በፈተናዎች የጸና- በጥንካሬ የበረታ ማንነት

መልካምሥራ አፈወርቅ

1983 ዓ.ም በመላው ኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ ታውጇል። ዛሬ እንደትናንትናው አይደለም። ነገሮች ተቀይረዋል። ሁኔታዎች ተለውጠዋል። በደብረዘይት (ቢሾፍቱ) ከተማ በአንዱ ጣራ ስር የቤቱ አባወራ በሞት መነጠል ደግሞ መላውን ቤተሰብ ለድንገቴ ፈተና እያጋፈጠ ነው። ወይዘሮዋ የትዳር አጋራቸውን በሞት እንዳጡ የልጆቻቸው ዕጣ ፈንታ፣ የራሳቸውም ቀጣይ ሕይወት ያሳስባቸው ይዟል።

ወታደሩ አባወራ ለእሳቸው መልካም ባል፣ ለልጆቻቸው ታላቅ አባት ነበሩ። አሁን በዚህ ክፉ ቀን የማለፋቸው እውነት ግራ አጋብቷቸዋል። ለጊዜው ለኑሮ መደጎሚያ፣ ለልጆች ማሳደጊያ አይጠፋም። የቤትን ራስ፣ የጎጆን ዋልታ፣ ከናካቴው ማጣት ግን በእጅጉ ይሰብራል።

ውሎ አድሮ የቤተሰቡ ሀላፊነት በወይዘሮዋ ትከሻ ወደቀ። በወቅቱ አምስቱን ወንዶች ልጆች ያለአባት ማሳደጉ፣ ቤትን፣ጎጆን ያለአጋር ማቅናቱ ቀላል አልነበረም። ይህ ብቻ አይደለም። በወቅቱ ከባንክ ዕዳና ከቤት ሽያጭ ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ችግሮችን አሸንፎ በጽናት መቆም፣ እማወራዋን በእጅጉ ፈተናቸው፣ አንገዳገዳቸው።

### አምስተኛው ልጅ...

የአባወራን ሞት ተከትሎ በቤተሰቡ ላይ የተጋረጠው ችግር መላውን ቤተሰብ በፈተነ ጊዜ የትንሹ ልጅ ብርታት ከሌሎች ልቆ መታየት ያዘ። ሌኒን ደምሴ ለቤቱ አምስተኛና የመጨረሻ ልጅ ነው። እሱ ጥቃት ይሉትን አይወድም፤ ለሽንፈት፣ለውድቀት ፈጽሞ እጅ አይሰጥም። ሁሌም ለችግሮች መፍትሄ መጣር፣ መፍጠን መለያው ሆኗል።

ሌኒን ወታደር አባቱን በሞት ካጣ በኋላ ወላጅ እናቱን ለመርዳት ያልሆነው የለም። ቆሎ ይዞ በባቡር መስኮት አዙሯል። ጀብሎ ተሸክሞ ሲጋራ፣ ሶፍትና ማስቲካ ሸጧል። የዛኔ በቤቱ ያገጠመን ፈተና ተጋፍጦ ከእናቱ ጎን ለመቆም የቀደመው አልተገኘም። መኖሪያ ቤታቸውን ጠበቃ አቁሞ፣ በፍርድ ቤት ተከራክሮ አስመልሷል። ቤተሰቡን ለማስተዳደር የልጅነት ጉልበቱን ገብሮ የእናቱ ቀኝ እጅ ሆኗል።

ትናንት ብዙ የለመደ ጎጆ ዛሬ ጎዶሎው ቢበዛ ትንሹ ሌኒን አብሮ እየተከዘ ማዘን ምርጫው አልሆነም። ጊዜ ወስዶ ጥቂት ቆም ብሎ አሰበ። ያለበት ዕድሜ ትምህርት ቤት የሚሄድበት፣ ዕውቀትን በወጉ የሚሸምትበት ነው። ያም ቢሆን እናቱን ማገዝና መደገፍ ግዴታው ሆኗል። በአቅሙ የቤተሰቡን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ ካሰበው ቦታ መገኘት ይኖርበታል።

የሌኒን ቤተሰቦች መኖሪያ ደብረዘይት (ቢሾፍቱ) ከተማ ነው። እሱም በዚህ ስፍራ ተወልዶ ከእኩዮቹ ቦርቆ አድጓል። በየቀኑ ከተማውን አልፎ የሚሄደው የመንገደኞች ባቡር ለብዙዎች መተዳደሪያቸው መሆኑን አሳምሮ ያውቃል። ትንሹ ሌኒን እናቱን በተሻለ ለመርዳት የመጀመሪያ ምርጫው የባቡር ላይ ሕይወት ሆነ።

ሌኒንና ባልንጀሮቹ ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ የሚያልፈውን ባቡር በመንደራቸው ሲያገኙት በዓይናቸው አይሸኙትም። አሁን ባቡሩ ለእነሱ የዕለት እንጀራቸው ሆኗል። መምጣታቸውን የሚሹ በርካቶች በፍቅር ተሻምተው ይቀበሏቸዋል። ጓደኞሞቹ በየጉዞው ከሚያገኟቸው መንገደኞች ተዛምደውና በጥቅም ተዋውለው የላባቸውን ይቀበላሉ።

የዛኔ የባቡር ላይ ጉዞ በኮንትሮባንድ ንግድ የጦፈ ነበር። አብዛኛው ነጋዴ ለትርፍ፣ ጥቂቱ ደግሞ ለድንገቴ ኪሳራ መጋለጡ ተለምዷል። ይህን የሚያውቁ ተመላላሽ ነጋዴዎች የያዙትን ዕቃ በዘዴ ለሚያሳልፉላቸው ሁሉ መልካም ክፍያን ይሰጣሉ። ሌኒንና ባልንጀሮቹም ይህ አይነቱን ስራ ቋሚ መተዳደሪያ አድርገዋል። በየኬላው በሚደራርቡት የልብስ ቁጥር አንድ ብር እየታሰበ ይከፈላቸዋል።

እነ ሌኒን ከመንገደኞች ተቀላቅለው ድሬዳዋ ደርሶ ለመመለስ ለወንበር መክፈል አይጠበቅባቸውም። ለእነሱ የባቡሩ ፉርጎና ጣራዎች ከመቀመጫ በላይ ናቸው።



ፎቶ - በናኦል አየለ

**አቶ ሌኒን ደምሴ**

እንዳሻቸው እየወጡ እየወረዱ ይጓዙባቸዋል። ሌኒን በዚህ መልኩ የሚያገኘውን ገንዘብ ፈጽሞ አያባክንም። ለቁም ነገር አውሎ፣ ለእናቱ ቆጥሮ፣ ቋጥሮ ያስረክባል። እናት በገንዘቡ ጎዶሎውን ሞልተው ከልብ ያመሰግኑታል፣ ይመርቁታል።

### ግራጋዶስ ሴላው መንገድ ...

ሌኒን በየባቡሩ ጉዞ የሚያገኘውን ገቢ በሌላ አማራጭ መተካት ፈለገ። በወቅቱ ለዚህ ፍላጎቱ የተገኘለት ምላሽ ከአዲስ አበባ ሀዋሳ የሚሰራው የመንገድ ግንባታ ሆነ። በ1991 ዓ.ም ግራጋዶስና ጠንካራው ሌኒን ደብረዘይት ላይ ሲገናኙ አብረው ለመዝለቅ ጊዜ አልፈጁም። አብረው በስራ ተጣመሩ።

አንድ ቀን አንድ ጓደኛው ከስራ ቦታው ዘልቆ ውሎውን አስተዋለ። አማራጭ እያለው ሲሚንቶ ሲያቦን መዋሉ አልተመቸውም። ሀሳቡን የተቀበለው ሌኒን ዕለቱን ሥራ ለማቋም አላቅማማም። ግራጋዶስን ተሰናብቶ የባቡር ላይ ስራውን ሊቀጥል ወሰነ።

እነ ሌኒን በባቡር ጉዞ የጀመሩትን የንግድ ስራ ማሳደግ ፈልገው አዲስ ዕቅድ ነደፉ። ለውጥ ፈላጊ ባልንጀሮቹ ‹‹ለሌሎች መስራቱ ይብቃን›› አሉና ነጋዴ መሆን ተመኙ። ሀሳባቸው በምኞት አልቀረም። በቂ ገንዘብ ይዘው ንግዱን ጀመሩት። ሌኒን በልጅነቱ የወጠነውን ጉዞ ዳር ለማድረስ ለተከታዩ እርምጃ ተዘጋጀ። ከዚህ በኋላ ከመንገዱ፣ የሚመልሰው፣ ከሀሳቡ የሚያደናቅፈው አይኖርም። ራሱን ለውጦ የእናቱን ሕይወት ይቀይራል። ዛሬን አሸንፎ ለነገው ታሪክ ይተጋል።

ሌኒን ለራሱ የንግድ ስራ በመጀመሪያው ቀን ከባቡሩ በተገኘ ጊዜ ስለወደፊቱ አሻግሮ አሰበ። አሁን ጥሩ ዕቃዎች ይዞ በደህና ትርፍ ይመለሳል። ትርፉን አስቀምጦም ለተሻለ ነገ ይዘጋጃል። እሱና ባልንጀሮቹ መንገዳቸውን ቀጠሉ። ለስራው እንጂ ለእንዲህ አይነቱ መንገድ አዲስ አይደሉም።

### በመጀመሪያው ቀን የመጀመሪያው ስራ

‹‹ቢኬ›› ከተባለ የኮንትሮባንድ ቦታ ቦንዳ ጨርቅ የገዙት እነሌኒን የያዙትን ዕቃ ያለስጋት ማሻገር አለባቸው። አዋሽ ወርደው ሜኤሶን እንዳለፉ ግን የሚጠብቁት ባቡር እንዳመለጣቸው አወቁ። ዕቃውን ወደ መተሀራ በመኪና አሳልፈው ቀጣዩን ባቡር መጠበቅ ያዙ። ሳይዘገይ በሰዓቱ ደረሰ።

በነጻነት ከባቡሩ አናት መቀመጥ የለመዱት ባልንጀሮች እንደልማደቸው ሆነው ጉዞ ጀመሩ። ባቡሩ ረጅሙን መንገድ በሀዲዱ እያዘገመ፣ ከሩቁ ድምጹን እያሰማ ወደ ወለንጪቲ ጣቢያ ተጠጋ። ሌኒን ስፍራው ላይ ሲደርስ ከባቡሩ ዘሎ ለመውረድ ተዘጋጀ። ይህ አይነቱ ልምድ ለእሱ አዲስ አይደለም። የዛሬው ጉዞ ግን ራሱን ችሎ ንግዱን የጀመረበት የመጀመሪያ ቀኑ ነው። ንብረቱን እያሰበ፣ ነገውን እያለመ፣ ከባቡሩ እመር ብሎ ዘለለ። ሌኒን እንዳሰበው አልሆነም። እግሮቹ መንገዳቸውን ስተው ወደፊት ተሸንራተቱ። ድንገቴው ማዳለጥ ከመሬቱ አስቀድሞ ከሀዲዱ መሀል አሳረፈው። በመጣበት መስመር የሚሽከረከረው ባቡር አልማረውም ። በፍጥነት ቀኝ እግሩን ረግጦ፣ ገጭቶት አለፈ።

ሀዲዱ ላይ የወደቀው ሌኒን ጥርሱን ነክሶ ስቃዩን ችሎ እየተሳበ ወጣ። በርካቶች ሊረዱት፣ ሊያነሱት ተረባረቡ። ክፉኛ የተጎዳው ቀኝ እግሩ ሊያዩት ያሰፈራል። ከሰዓታት በኋላ ሌኒን ራሱን ናዝሬት ሀይለማርያም ማሞ ሆስፒታል አገኘው። ትናንት ሲሮጥበት የነበረው እግሩ ዛሬ ታሪኩ ተቀይሯል። አብሮት የቆየው አዲስ ተስፋ ከጎኑ ርቋል። ደጋግሞ እናቱን አሰበ፣ ራሱን ተመለከተ። ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ከበበው።

### ከዓመታት በኋላ...

ሌኒን ደምሴን ሳገኘው በአጋጣሚ ነበር። ቁመተ ረጅም፣ መለሎ ይሉት ሎጋ ነው። በአንድ እጁ የያዘው ክራንች ከጉልበቱ ከፍ ብሎ ለተቆረጠው ቀኝ እግሩ አጋዥ ሆኖታል። ከሚያሽከረክራት ዘመናዊ መኪና ወርዶ ሰላምታ አቀረበልኝ። ለጨዋታ አይከብድም። ጥቂት አውርተን በቀላሉ ተግባባን። ቅልጥፍናው፣ በራስ መተማመኑ እያስገረመኝ ነው።

አካል ጉዳተኝነቱን ያዩ አንዳንዶች መኪናውን አቁሞ ሲወርድ በአድናቆት ሲቃኙት አስተዋልኩ። በውስጣቸው ‹‹እንዲህም አለ ለካ›› የሚሉ ይመስላል። ቦታ ይዘን አሁን ስላለበት ሕይወትና ኑሮ፣ እንዲያጫውተኝ ጋበዝኩት። አልደበቀኝም።

ሌኒን ደምሴ ዛሬ ትልቅ ሰው ሆኗል። ከዓመታት በፊት ቀኝ እግሩን በአደጋው እንዳጣ በአስቸጋሪ መንገዶችን ተሻግሯል። የዛኔ አብዛኞች ሱቅ ተቀምጦ እንዲውል ይመኙለት ነበር። ከእኩለ ሌሊት በኋላ ዓይኖቹ የማይከደኑት ብርቱ ግን ሰፊ ዕቅድ እየነደፈ ከራሱ ሲመክር ያድራል። ሌኒን አሁንም ብርታቱ አልተለየውም። ዛሬም ስለነገው ያስባል። እግሩን እንጂ ወኔውን እንዳላጣ ደጋግሞ ለራሱ ይነግረዋል።

የመጀመሪያ ስራውን በኤልፎራ ቄራ ላይ ወጠነ። ፈጥኖ ለመድረስ በአንድ እግሩ ብስክሌት እየነዳ ይጓዛል። ለድመቶች ሳንባ እየወሰደ ይሸጣል። አጋጣሚው ጨጓራ እየገዙ ከሚሸጡ ሰዎች አገናኘው። ከእነሱ ተግባብቶ ሊሰራላቸው ተስማማ። ሙያውን ሲለምደው ገበያው ደራለት። ደንበኞቹ ሲበራከቱ ጨጓራ ማከፋፈሉን ገፋበት። የድመቶቹን ሳንባ ጨምሮ ለውሾች የተፈጨ ቀንድና አጥንት መሸጡ አዋጣው። በየቤቱ ያሉ ውሻና ድመቶች ፉጨቱን ለምደው እጁን ናፈቁ።

ሌኒን ገቢው ሲጨምር ስለነገ ማንነቱ ማሰቡን ቀጠለ። በቂ ገንዘብ ይዞ የዕቃ ባጃጅ በዘጠኝ ሺህ ብር ገዛ፣ ከቀኝ መሪ ወደ ግራ አቅጣጫ አዙሮ ከሁለት አመት በላይ ሰራበትና በሀያ ስድስት ሺህ ብር ሸጠው። በገንዘቡ ሌላ ባጃጅ ገዝቶም መንገደኞችን ያመላልስ ያዘ። በዓመቱ ባጃጁን በትርፍ ሸጦ ሌላ እየተካና እየሸጠ በቂ ገንዘብ ያዘ። ይህ አይነቱ መንገድ የታክሲ መሪን ሲያስጨብጠው አልዘገየም። ታክሲውን እያሽከረከረ ሌሎች ስራዎችን ዳሰሰ። ጣራ ላይ ዲሽ በመግጠም ሙያ ዝና ማትረፉን ተከትሎ እጁን የሚሹ ደንበኞቹ በረከቱ። የዲሽ ገጠማው በተሻለ ገቢ ወደ ለውጥ ጎዳና አንደረደረው። ታክሲውን ለሾፌር ሰጥቶ በሙያው ገፋበት። ጥረቱ በዚህ አልተቋጨም። በየጊዜው የታክሲዎቹን ሞዴል ቀያየረ። ስኬት ከጉኑ ቆማ አብራው ተጓዘች።

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሌኒን በአይሱዙ ጋቢና ተቀምጦ ያዩ እጃቸውን በአፋቸው ጫኑ። ‹‹ለካ !እንዲህም ይኖራል›› ያሉ በርካቶች ስለማንነቱ እያወጉ በበጎ ተምሳሌት ሰየሙት። ጠንካራው ሾፌር በአይሱዙው ከፍ ያለ ጭነት አስሮ መቀሌ፣ ጅግጅጋ፣ ሀረር ተጓዘ። ጥቂት ቆይቶ በተሻሉ ሞዴሎች መኪኖቹን ቀያየረ። እንዲህ በሆነ ቁጥር የገቢ መጠኑ ጨመረ፣ የኑሮ መልኩ ተለወጠ።

አሁንም ቆም ብሎ ያስባል። በእጁ ያለውን መኪና ሸጦ የተሻለ ከባድ መኪና መግዛት ፈልጓል። ያሰበው አልቀረም። የዕቅዱን አሳክቶ ባለ አስር ጎማ ‹‹ካሶኒ›› የጭነት መኪናን ከእጁ አስገባ። ጠንካራው ሰው እንደሱ ብርቱ ለሆኑት ሁሉ ልቡ ቅርብ ነው። እጅ ያጠራቸውን እያገዘ ከፍላጎታቸው ያገናኛል። መማር ያለባቸውን ቀርቦ ያበረታል። ከእሱ ሆነው በሙያቸው ያደጉ ታታሪዎች ዛሬ ስለነጋቸው መሰረት ጥለዋል። እሱም ይህን በማድረጉ ደስተኛ ነው።

ሌኒን በውጣ ውረድ ዋጋ ለከፈለበት ንብረቱ የሚሰጠው ግምት የተለየ ነው። መኪኖቹን ለሌሎች አሳልፎ ከመስጠት በጥንቃቄ መያዝን ይመርጣል። ንብረቶቹ ትናንት ላለፈበት ፈታኝ መንገድ ማሳያዎች ናቸው። እሱን ከልመና በዘለለ ለማያስቡት አንዳንዶችም ምስክር ሆነውታል። ንብረቱ አካሉ ከተጎዳ፣ በኋላ የተገኘ ነው። ይህ እውነታ እሱን ለመሰሉ ወገኖች ብርታትና ጥንካሬ ሆኗል።

አንዳንዴ አንዳንዶች የሌኒንን ችሎታና ለውጥ አምነው መቀበል ይሳናቸዋል። ቀረብ ብለው ካዩት በኋላ ባለው አቋም መኪና ማሽከርከሩን አይቀበሉትም። እንዲህ አይነቶቹ ከአድናቆት ይልቅ ወቀሳ ይቀናቸዋል። ሌኒን በአንድ ወቅት ለህግ አካላት ጠቁመው የከሰሱትን ሰዎች ድርጊት አይረሳም። በአጋጣሚው ግን አልተከፋም። ከሳሾቹን በበጎነት አስተምሮ መልሷል። ጠንካራው ሾፌር በመንገዱ ላይ ብዙዎችን ለመርዳት የፈጠነ ነው። ችሎታና ልምድ አንሷቸው ግራ ለሚጋቡና መንገድ ለሚስቱ የከባድ መኪና ሾፌሮች መፍትሄያቸው ነው። ከመኪናው ወርዶ መሪያቸውን ይገራል። የጉዞ አቅጣጫን አመላክቶ አረጋግቶ ይሸኛል።

እሱ ለዓመታት የተጓዘባቸውን መስመሮች አሳምሮ ያውቃቸዋል። ኩርባ ቁልቁለቱ፣ ዳገትና ሜዳው ከእሱ እይታ የተሰወረ አይደለም። ሁሌም ከረጅሙ መንገድ ተግባብቶ፣ ከጥንቃቄ ተዛምዶ ፈተናውን ሲሻገር ከታላቅ ስኬት ጋር ነው።

### እንዲህም ይኖራል!

የዓመታት ውጣውረድ የፈተነው ሌኒን ደምሴ የዛሬ ኑሮው ተወልዶ ባደገበት የቢሾፍቱ ከተማ ነው። ትናንት ቦርቆ ባደገበት ቀዬ፣ ሰርቶ በኖረበት አገር ሙሉ አካሉን ቢያጣም ከበርካታ ፈተናዎች ብዙ ተምሯል። አካል ጉዳቱ ሳይበግረውና እጁን ሳይሰጥም ለዚህ አይነቱ መልካም ሕይወት ደርሷል።

ዛሬ ትዳር ይዞ ሁለት ሴቶች ልጆችን በሚያሳድግበት ጎጆው ለችግር እጅ አይሰጥም። ልክ እንደሱ ልጆቹን ጠንካራ ለማድረግ ይተጋል።

ሌኒን ከአካል ጉዳቱ በኋላ ራሱን በተስፋ መቁረጥ አልደፋም። በርካታ ስራዎችን ሞክሮ ስኬትን ተጎናጽፏል። በእሱ ዘንድ ‹‹አልችልም›› ይሉት ቃል ቦታ የለውም። ይህ ጥንካሬ ለበርካቶች ማሳያ ሆኖም አድናቆት ተችሮታል። እሱ በተለይ አካል ጉዳተኞች በፈተናዎች ባህር ተሻግረው ለስኬት እንደሚደርሱ ታላቅ ምስክር መሆን ይሻል።

እነዚህ ወገኖች ልመና ብቻ መገለጫቸው አይደለም። እንደማንኛውም ሰው በርካታ ምርጫዎች አላቸው። ሌኒን በአካል ጉዳት ምክንያት ተስፋ በመቁረጥ፣ ባልተገባ አመለካከት መቃኘት ጠንቅ ስለመሆኑ ያምናል። መስራት እየቻሉ ልመናን የመጀመሪያ ምርጫ ያደረጉ ጉዳተኞች ልማድ ያናድደዋል።

እሱ ሰርቶ መቀየር እንደሚቻል፣ በጥረትና ልፋት ከስኬት ጫፍ መድረስ እንደሚኖር አስመስክሯል። በተስፋ መቁረጥ ብቻ ሳይሆን በስኬትም ‹‹እንዲህ ይኖራል›› የሚለው ሌኒን ልክ እንደትናቱ ዛሬን ተሻግሮ ነገን ብሩህ ለማድረግ መታተሩን ቀጥሏል። ከአካል ጉዳት ተያይዞ በአጉል አመለካከት ለተቃኙ ወገኖችም የራሱ ድንቅ ታሪክ ምሳሌ ይሆን ዘንድ ‹‹እነሆኝ›› ብሏል።

# ስፖርት





## “ተገቢ ባልሆነ እድሜ ዛሬ ውጤት አምጥተን ነገ ተተኪዎችን ማጣት አንፈልግም”

- ወ/ሮ ሳሚያ አብደላ፣ የኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከግንቦት 21 እስከ ሰኔ 4 ቀን 2014 ዓ.ም በሐዋሳ ከተማ ይካሄዳል። የኦሊምፒክ ስፖርት በሆኑና ባልሆኑ በርካታ የውድድር አይነቶች ስድስት ሺህ ወጣቶች ይሳተፉበታል ተብሎ በሚጠበቀው በዚህ የመጀመሪያው የወጣቶች ኦሊምፒክ ላይ ለመሳተፍ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የውስጥ ውድድሮቻቸውን በማካሄድ የሚወክሏቸውን ስፖርተኞች መርጠዋል፤ እየመረጡም ይገኛሉ።

የኦሮሚያ ክልል በሐዋሳው የወጣቶች ኦሊምፒክ ውጤታማ ሆኖ ለማጠናቀቅ ከወዲሁ ዝግጅቱን የጀመረ ሲሆን፤ የሚወክሉትን ስፖርተኞችም ባለፉት አስር ቀናት በሻሸመኔ ከተማ አካሂዶ ከትናንት በስቲያ ባጠናቀቀው የኦሮሚያ ወጣቶች ኦሊምፒክ መርጧል። ክልሉ፣ በሐዋሳው የወጣቶች ኦሊምፒክ ትልቅ ውጤት ለማስመዝገብ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዳደረገ መሆኑን የገለጸ ሲሆን፤ ለዚህም ሰሞኑን በሻሸመኔ ከተማ ሰፊ ውድድር በማካሄድ ክልሉን በተለያዩ ስፖርቶች የሚወክሉትን ወጣቶች በብዛት መምረጡን አሳውቋል።

የኦሮሚያ ክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሳሚያ አብደላ፣ በተለይ ለአዲስ ዘመን በሰጡት አስተያየት፤ ክልሉ በሻሸመኔ ከተማ ለአስር ቀናት የዘለቀ ሰፊ ውድድር በማካሄድ በተለያዩ ስፖርቶች ተስፋ ያላቸው ተተኪ ወጣቶችን እንዳገኘ ተናግረዋል። በሻሸመኔው ውድድር ከሶስት ሺህ በላይ ስፖርተኞች መሳተፋቸውን የጠቆሙት ወይዘሮ ሳሚያ፤ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ ከሶስት መቶ በላይ የተሻለ ብቃት ያሳዩ ስፖርተኞች ተመርጠው በቀሪዎቹ ጥቂት ቀናት ክልሉን ለመወከል እንደሚዘጋጁ አስረድተዋል።

እነዚህ ወጣቶች በሻሸመኔው ውድድር በተለያዩ ስፖርቶች ተስፋ ሰጪ እምቅ አቅም እንዳላቸው ያሳዩ ሲሆን፤ ለክልሉም ይሁን አጠቃላይ እንደ አገር ተተኪ ሆነው እንደሚወጡ ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል። በቀጣይ አስር ቀናትም ዝግጅታቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ኃላፊዋ አክለዋል።

ባለፉት ጥቂት አመታት በተለያዩ አገር አቀፍ ውድድሮች የኦሮሚያ ክልል ስፖርት መቀዛቀዝ ያሳየ መሆኑን ያስታወሱት ኃላፊዋ፤ ዘንድሮ ጥሩ የመነቃቃት ጅምር እንዳለ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ ክልሉ እንዳለው እምቅ የስፖርት አቅም አሁን ያለበት ደረጃ በቂ ነው ተብሎ ስለማይታመን አበረታች ጅምሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ቢሮው ጥረት እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

እንደ አገር ብዙ ጊዜ በወጣቶች መካከል በሚካሄዱ ውድድሮች ከእድሜ ማጭበርበር ጋር የተያያዙ ችግሮች ጎልተው ይታያሉ። ይህም ክልሎችን ውጤት ከማሳጣት ባሻገር የማይገባቸውን ውጤት ፍትሃዊ ባልሆነ መልኩ ሲያጎናጽፋቸው ይስተዋላል። የኦሮሚያ ክልል ይህ የተለመደ ችግር እንዳይገጥመው ወጣቶቹን በተገቢው እድሜ ለመመልመል የተለያዩ ጥንቃቄዎችን እንዳደረገ ተገልጿል።



“እድሜን በተመለከተ ጥብቅ ቁጥጥር ያደረግነው በአገር አቀፍ ደረጃ ስንወዳደር ውጤት ላይ ብቻ ትኩረት ስለማናደርግ ነው፣ ዛሬ ውጤት አምጥተን ነገ ተተኪዎችን ማጣት አንፈልግም፣ ከተገቢው የእድሜ ክልል ውጭ ስፖርተኞችን አሳትፈን የክልላችንን አንገት ማስደፋት አንፈልግም፣ ለነገ ተስፋ የሚሆኑ ጠንካራ ወጣቶችን አሰልፈን ዛሬ ውጤት ብናጣ ከሁለትና ሶስት አመታት በኋላ እነዚህ ወጣቶች በአዋቂዎች ውድድር ጠንካራ ተፎካካሪና ውጤታማ ሆነው ይክሱናል” በማለት ከእድሜ ጋር የተያያዘውን ጉዳይ የቢሮው ኃላፊዋ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ ይካሄዳል ተብሎ ከታሰበበት ወቅት ዘግይቶ ከፊታችን ግንቦት 21/2014 ጀምሮ እንደሚካሄድ ሲገለጽ፤ በርካታ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የዝግጅት ጊዜ ማጠሩን ቅሬታ ያነሳሉ። በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ክልል ከዝግጅት ጊዜ ማጠር በተጨማሪ የውድድሮች መደራረብ ጫና ሊኖረው እንደሚችል ቢገምትም ይህን ጫና ተቋቁሞ ውጤታማ ለመሆን ጥረት ማድረግ እንጂ እንቅፋት አድርጎ መቁጠር እንደማይፈልግ ኃላፊዋ ተናግረዋል።

በሻሸመኔው ውድድር ከሰላሳ በላይ ዞኖች፣ ከተሞችና የተለያዩ የወጣቶች ስፖርት ማሰልጠኛ ማእከላት የተውጣጡ ከሶስት ሺ በላይ ስፖርተኞች ተሳትፈዋል። አዘጋጁ ሻሸመኔ ከተማ አስራ ሁለት ወርቅና አስር ብር በመሰብሰብ አጠቃላይ የዋንጫ አሸናፊ ሆኗል። በተመሳሳይ አስራ ሁለት የወርቅና ስድስት የብር ሜዳሊያ በመሰብሰብ የቅርብ ተፎካካሪ የሆነው የአርሲ ዞን ሁለተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ ቢሾፍቱ ከተማ የሰበሰባቸው አስራ አንድ የወርቅ ሜዳሊያዎች ሶስተኛ ሆኖ እንዲያጠናቅቅ አስችለውታል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

በጋም/ህ/ብ/ክ/መንግስት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አገልግሎት በጋምቤላ ከተማ የቢሮ እድሳት ስራ ለማሰራት በደረጃ BC/GC-6 እና ከዚያ በላይ ያሉትን የሥራ ተቋራጮችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል።

**ስለሆነም ተጫራቾች ከዚህ በታች የተረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።**

1. ለበጀት ዓመቱ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያለው
2. ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያለው
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ
4. የ2013 ዓ/ም ውዝፍ ግብር ነፃ ሠርተፍኬት ማቅረብ የሚችል
5. የግብር መከፈያ መለያ ቁጥር ቲን ነምበር ያለው
6. ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ14 ተከታታይ ቀናት ተጫራቾች ለዚሁ የተዘጋጀውን የጨረታ ሠነድ የማይመለስ 300.00 (ሶስት መቶ) ብር በመክፈል በቢሮው ግዥ/ፋይ ንብ/አስ/ቡድን መሪ በመቅረብ መግዛት ትችላላችሁ ።
7. ተጫራቾች የጨረታውን ዋስትና ማስከበሪያ 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) ብር በሲፒኦ ወይም በባንክ ጋራንቲ ብቻ ከጨረታ ሠነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል
8. ተጫራቾች ጥገናውን የሚያከናውኑበትን ዋጋ ዋናውንና ኮፒ ሁለት /2/ እና ካምፓኒ ፕሮፋይል ዋናውንና ኮፒ ሁለት/2/ ለየብቻ በሰም የታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ በ15ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡30-4፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ አስገብተው በዚሁ ቀን በ4:30 ሰዓት ላይ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት በቢሮው ግዥ/ፋይ/ንብ/አስ/ቡድን መሪ ክፍል ይከፈታል፣
9. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው:
10. ለተጨማሪ መረጃ ስልክ ቁጥር 047-551-22 48 / 25 09 11 33 12 94 ይጠቀሙ

**የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አገልግሎት**

**ጋምቤላ**



## የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል
## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ ጨረታ ቁጥር
## EEP/ST/NCB/38/2014

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከዚህ በፊት ተቋሙ ባስገነባቸው የዳታ ማዕከል ውስጥ የሚገኙ ለማዕከሉ ግልጋሎት የሚጠቀምባቸውን የአይ.ሲ.ቲ. እና ተጓዳኝ መሳሪያዎች SLA Software License Renewal እና Virtual machine service migration በዘርፉ ከተሰማሩና ፍቃድ ካላቸው ድርጅቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ የአገልግሎት ግዥውን መፈፀም ይፈልጋል፡፡

**ስለሆነም ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መወዳደር ይችላሉ፡፡**

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩና የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ፣ በግዥ ኤጀንሲ ድህረ-ገፅ ላይ ስለመመዝገባቸው የሚያስረዳ ምስክር ወረቀት እና ታክስ ክሊራንስ የሚያቀርቡ መሆን አለባቸው፡፡
2. በዚህ ጨረታ ለመሳተፍ ከላይ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች በማያያዝ መወዳደር የሚችሉ ሲሆን ዝርዝር ሁኔታው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ይገኛል፡፡
3. ተጫራቾች ማስታወቂያው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ቀንና ሰዓት ሜክሲኮ ወደ ቄራ በሚወስደው መንገድ ላይ ኬኬር ሴንተር አዲሱ ህንፃ 12ኛ ፎቅ በሚገኘው ዋናው መ/ቤት ገንዘብ ተቀባይ ቢሮ የማይመለስ ብር 300.00 (ሶስት መቶ) በመክፈል እና የጨረታ ሰነዱን 1ኛ ፎቅ ግዥ ክፍል በመምጣት መውሰድ ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከቱትን ዕቃዎች እና አገልግሎት የቴክኒካል እና የፋይናንሽያል ሰነዳቸውን ለየብቻው በማድረግ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማሸግ እና ሁለቱንም በሌላ አንድ ትልቅ ፖስታ ውስጥ በማስገባት የጨረታ ቁጥር EEP/ST/NCB/38/2014 ሎት-1 እና ሎት-2 ቴክኒካል እና ፋይናንሽያል የሚል ምልክት በማድረግ ከታች በተቀመጠው መሠረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

| No. | Description | የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ | የጨረታው መዝጊያ ቀንና ሰዓት | የጨረታው መከፈቻ ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|
| Lot-1 | SLA Software License Renewal | ብር 200,000.00 | ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 8:00 ሰዓት | ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡30 ሰዓት |
| Lot-2 | Virtual machine service migration | ብር 140,000.00 | | |

5. ተጫራቾች ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 011-558-06-27/558-15-22 መደወል ይችላሉ፡፡
6. ገዥው የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል**